# እንድረስላቸው

## ሙስሊሞችን በወንጌል የመድረስ ዘዴ

## (በተለይ ለሥልጠና የተዘጋጀ)

በገርሃርድ ኔልስና

ዎልተር ኤሪክ

**ማስታወሻ፤-** ከቁርዓን የተወሰዱት ጥቅሶች ሁሉ ከ1961 ዓ.ም. የአማርኛው ቁርዓን ትርጉም የተወሰዱ ናቸው።

የሕይወት በር መ.ሣ.ቁ. 4937

አዲስ አበባ

«የእግዚአብሔር ቃል ቀኑን ሁሉ ስድብና ዋዛ ሆኖብኛልና። እኔም፦ የእግዚአብሔርን ስም አላነሣም፥ ከእንግዲህ ወዲህም በስሙ አልናገርም ብል፥ በአጥንቶቼ ውስጥ እንደ ገባ እንደሚነድድ እሳት ያለ በልቤ ሆነብኝ፤ ደከምሁ፥ መሸከምም አልቻልሁም» (ኤርምያስ 20፡8-9)።

ውድ ተማሪ ሆይ፥

ክርስቲያን በመሆንህ ስለ እምነትህ የሚናገረውን የመጽሐፍ ቅዱስን የምሥራቹን ቃል ለሙስሊም ጓደኛህ እንድታካፍል ትፈልጋለህ። በቅድሚያ ግን እነዚህን ማስታወሻዎች ብታጠናቸው እጅግ ይጠቅሙሃል። ይህን በማድረግህም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ «ታላቁን ተልእኮ» ከዳር እንዲደርስ የበኩልህን ድርሻ ታበረክታለህ ማለት ነው። «ታላቁ ተልእኮም» የሚከተለው ነው፤

> «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም፥ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» (ማቴዎስ 28፡18-20)።

ነገር ግን ሁሉም ሰው አንድ ዓይነት አይደለም። በተለያየ መንገድ ያስባሉ፤ በተለያየ መንገድ ነገሮችን ይፈጽማሉ፤ በተለያየ መንገድ ያምናሉ፤ የተለያየምስሜት አላቸው። ወንጌሉን ለማካፈል ስንነሣ ይህን መዘንጋት የለብንም።

እነዚህም ማስታወሻዎች እንደሚከተለው ይጠቅሙሃል፡-

1. በክርስትናና በእስልምና እምነቶች መካከል ያለውን ልዩነት ያስረዱሃል። ሙስሊሞች የሚሰማቸውን፥ የሚያምኑትንና የሚያደርጉትን ሁኔታ ያስረዱሃል። ሙስሊሞች «እኔ ሙስሊም ሆኜ ተወልጃለሁ፤ ሙስሊም ሆኜም እሞታለሁ፤ ይህንን የሚቀይረው ምንም የለም» ለሚለው እስላማዊ የሕይወት መመሪያ የተገዙ ናቸው። ስለዚህም ከእንዲህ ያለው ሙስሊም መነጋገር ለስሙ ክርስቲያን ከሚባለው ሰው ጋር እንደምንነጋገር አይደለም። ይኸውም መቀያየም እንጂ ፋይዳ አይኖረውም። ምክንያቱም በእንዲህ ያለ መንገድ ብንናገራቸው አብዛኞቹ ሙስሊሞች ልናካፍላቸው የፈለግነው ምን እንደ ሆነ አይገባቸውም።

2. ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲረዱ እንዴት እንደ ተማሩና፥ ይህ መጽሐፍ በጌታችን በኢየሱስ ላይ ያላቸውን ጥላቻ ለሚሰነዝሩት

ጥቃት እንዴት በታማኝነትና በጸጋ ምላሽ ለመስጠት እንደምትችል መላውን ያሳይሃል።

3. ለሙስሊሞች የወንጌል አገልግሎት ለመስጠት እንድትችል ከተለመደው አሠራር በጣም ልዩ የሆነ ዘዴን ያስታጥቁሃል።

ጌታችን ጥናትህን እንደሚባርከውና ለሙስሊም ጓደኞችህም ሆነ ጎረቤቶችህ ብቁ ምስክርነት እንድትሰጥ እንደሚያበቃህ እምነታችን ነው።

## ከአረብኛ የተወሰዱ ቃላት

| | |
|---|---|
| አል-መሢሕ .... | መሢሑ |
| አያት ... | የቁርዓን አንቀጽ |
| ደሃር-ኡል-ሃራብ ... | የጦርነት ቤት (በእስልምና በማስማረክ ሊዘመትበት የሚገባ) |
| ደሃር-ኡል-ኢስላም ... | የእስላም ቤት ወይንም እስላማዊው ዓለም |
| ሐዲት ... | የመሐመድ ወግና ልማዶች የተሰባሰቡበት ጥራዝ |
| ሐጂ ... | ቅዱስ ጉዞ- ወደ መካ |
| ሐላል ... | የተባረከ፥ ለሙስሊሞች የተፈቀደ (ለምሳሌ የበሬ ሉካንዳ፥ የበግ ሥጋ) |
| ሐራም ... | ያልተባረከ ወይም ርኩስ፥ ለሙስሊሞች የተከለከለ (ለምሳሌ የአሣማ ሥጋ) |
| ሒጂራ ... | የመሐመድና የተከታዮቹ ከመካ ወደ መዲና መሰደድ |
| ኢንጂል ... | ወንጌል |
| ጂሃድ ... | ቅዱሱ ጦርነት (እስልምናን ማስፋፋት) |
| ካባ ... | መካ የሚገኘው ቅዱስ መስገጃ |

ከሃላፊ/ካሊፍ ... የመሐመድን ሹመት ወራሽ

ማንሱክ ... የቀድሞውን ለመተካት
ኋላ የመጣ መገለጥ

ሚሽካት ... የሐዲት ስብስቦች

ናሲክ ... ጥንታዊ መገለጥ
(በማንሹክ የተተካ)

ቁርዓን ... የእስልምና ቅዱስ መጽሐፍ

ሪዳ ... ከመሐመድ በኋላ በአረብ አገር
በእስልምና ላይ የተቀሰቀሰ ዓመፅ

ሶላት ... የእስልምና የጸሎት ደንብ
- በቀን 5 ጊዜ የሚፈጸም

ስዋም ... የረመዳን ጾም

ሸሃደሀ ... የእምነት መግለጫ

ሼሪያ ... የእስላም ሕግ

ሽርካ ... የአላህ እኩያ ማብጀት
(ይቅር የማይባል ኃጢአት)

ሲሃሁ ሲታ ... የሐዲት 6 ትክክለኛ መጻሕፍት

ሱና ... የመሐመድን ሕይወት ምሳሌነት
መከተል

ታፍሲር ... የቁርዓን መተርጎሚያ መጻሕፍት

ታውሂድ ... የአላህ ውህድነት (አንድነት)

ታውራት ... የሙሴ መጻሕፍት
(ወይም ብሉይ ኪዳን)

ዛቡር ... የዳዊት መዝሙር

ዛካት ... ምጽዋት ስጦታ

## ማውጫ

ገጽ


1. እስልምና ምንድነው? . . . . . . . . 1
- እስልምና ምን ያህል ዘመን ሆኖታል? . . . . . 1
- እስልምና ክርስትናን ይቀድማልን? . . . . . . 1
- ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች በሚከተሉት ነጥቦች ይስማማሉ . . . . . . . . . . . . 2
- እስልምና መጽሐፍ ቅዱስን ቀጥሎ ባሉት ነጥቦች ይጻረራል . . . . . . . . . . . . 2
- ወሳኙ ነጥብ . . . . . . . . . . . 3
- ትክክለኛው ማነው? . . . . . . . . . 3
- ጥቂት የታሪኩ አሰሳ . . . . . . . . . 4
2. መሐመድ - የእስልምና ነቢይ . . . . . . 5
- እስልምና እንዴት ተጀመረ? . . . . . . 5
- የመሐመድ አነሣስ . . . . . . . . . 7
- የመሐመድ የመጀመሪያ ራእዮች . . . . . . 7
- የመሐመድ ወደ መዲና መሰደድ . . . . . . 9
- የመሐመድ ሕይወት መለወጥ . . . . . . . 9
- ቅዱሱ ጦርነት . . . . . . . . . . . 10
- የዛሬው እስላማዊው መሳምዣት ስለ አፍሪካ . . 11
- ክርስቲያኖችስ ምን ማድረግ ይገባናል? . . . 12
- መሐመድ በመዲና . . . . . . . . . . 14
- የመሐመድ ራእዮች ብዙ ጥቅሞች አስገኙለታል 14
- የመሐመድ ሕይወት መጨረሻ . . . . . . . 15
- የእስልምና መስፋፋት . . . . . . . . . 16

3. ቁርዓን - የእስልምና መጽሐፍ . . . . . . . 17
- ቁርዓን እንደምን ወረደ? . . . . . . . 17
- የቁርዓን አወቃቀር . . . . . . . . . 18
- ቁርዓን መጽሐፍ ቅዱስን ይጻረራል . . . . . 19
- የቁርዓን ምንጮች . . . . . . . . . 20
- ሌላስ ስለ ቁርዓን ማወቅ ያለብን ምንድነው? . 21
4. የእስልምና ባህላዊ ወጎች . . . . . . . 24
- ቁርዓንን ለመተርጎም የእስልምና ወጎች ያስፈልጉ ነበር . . . . . . . . 24
- ወጎቹ እንዴት እንደተሰበሰቡ . . . . . . 25
- የሐዲት ትምህርት . . . . . . . . . 26
- ሱና - የመሐመድ የአኗኗር ስልት . . . . 27
5. የእስልምና እምነትና ምግባሩ . . . . . . 28
- የእስልምና እምነት . . . . . . . 28
- የእስልምና ምግባር . . . . . . . 29
6. የእስልምና ግንዛቤ . . . . . . . . . 29
- አላህ . . . . . . . . . . . . 29
- ቀድሞ ስለ ተወሰነ ዕጣ ፈንታ . . . . . . 30
- ፍርድ በእስልምና እምነት . . . . . . . 34
- ከሞት በኋላ ሕይወት በእስልምና . . . . . . 39
- የደኅንነት ምሥጢር በእስልምና . . . . . 40
7. የእስልምና ተቃውሞ በክርስትና ላይ . . . . . 41
- ለሙስሊሞች ተቃውሞ መልስ እንዴት ይሰጣል? 44
- ተደጋግመው የሚነሡት የእስልምና መከራከሪያዎች 44

- የሐቁ ማረጋገጫ . . . . . . . . . . . . . 54

8. ለሙስሊሞች መመስከር . . . . . . . . . . 59

- የዛሬው ሁኔታ . . . . . . . . . . . . . . 59

- የተለመደ ሁኔታ የሚባል ነገር አለን? . . . . . 60

- የወንጌል ስርጭት ስንል ምን ማለታችን ነው? . . 60

- ቅድመ - ወንጌል . . . . . . . . . . . . . 66

- የወዳጅነት ወንጌል ስርጭት . . . . . . . . 66

- ለመስማማት ወይስ ለመጋፈጥ? . . . . . . . . 68

9. እንደ እግዚአብሔር ኃይል መጠን መልእክቱን ማስተላለፍ . . . . . . . . . . . . . 69

- እውነትና ኃይል በወንጌል አገልግሎት ውስጥ . . 69

- የእግዚአብሔር ወይስ የሰው ኃይል? . . . . . 70

- ኃይል በድካም ውስጥ . . . . . . . . . 70

- የሰይጣን ኃይል . . . . . . . . . . . . 72

- ተገዳዳሪ ኃይል . . . . . . . . . . . . 72

- ተገቢ የሆነ ግንኙነት . . . . . . . . . . 73

- መንፈሳዊ ውጊያ . . . . . . . . . . . . . 74

10. ተግባራዊው ገጽታ - ሙስሊሞችን በወንጌል ለመድረስ . . . . . . . . . . . 79

- ዝግጅትና ልምምድ . . . . . . . . . . . 79

- ውይይት ስንጀምር . . . . . . . . . . . 80

- የተለወጠው ሙስሊም - ጎዳናውን ሲያጠራ . . . 85

- ከሙስሊሞች ጋር ለሚኖሩን ግንኙነት ጠቃሚ መመሪያዎች . . . . . . . . . . . . . 88

-አጭር ማጠቃለያ . . . . . . . . . . . . 93

11. ወደ ተግባራዊው እርምጃ . . . . . . . . 95

- ሙስሊሞችን እንዴት እንድረሳቸው? . . . 95

- ዘዴ ቀይስ . . . . . . . . . . . 96

- ቀጥሎስ? . . . . . . . . . . . 98

12. መግለጫ . . . . . . . . . . . 99

- የክለሳ ጥያቄዎች . . . . . . . . . 99


- «የሕይወት በር» የሕትመት ውጤቶች . . . 104

- ለሙስሊሞች ወንጌልን ለመመስከር የሚረዱ ጠቃሚ መግለጫዎች . . . . . . . . . . 110

- የአብርሃም ወንጌል . . . . . . . . . 123

# 1 እስልምና ምንድነው?

## እስልምና ምን ያህል ዘመን ሆኖታል?



የአውሮፓውያን ዓመት 1994 ዓመተ ምሕረትን አይተን ወደ እስላማዊው የዘመን አቆጣጠር መለስ ብንል የምናገኘው የዘመን ቁጥር 1416 ኤ. ኤች. ነው። የእንግሊዝኛው ምህጻረ ቃል ተተንትኖ ሲተረጐም «ከሒጂራ በኋላ» ማለት ነው። የእስልምና ሃይማኖት መሥራች የሆነው መሐመድ ከሚኖሩበት ከተማ ከመካ በእምነቱ ምክንያት ተሰድዶ ወደ መዲና ከተማ የአደረገው ጉዞ በአረብኛ «ሒጂራ» በመባል ይታወቃል። ይህም ጊዜ የእስልምና ሃይማኖት የተጀመረበት ጊዜ ተደርጎ ተወስዷል።

## እስልምና ክርስትናን ይቀድማልን?

አይቀድምም። እንዲያውም ክርስትና እስልምናን በ600 ዓመታት ይቀድመዋል! ለዚህ ነው ሙስሊሞች በእግዚአብሔር (አላህ)፥ በኖኅ፥ በአብርሃም፥ በሙሴ፥ በዳዊት፥ በሰሎሞን፥ በዮናስና ኢየሱስን ጨምሮ በሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት እንደሚያምኑ የሚናገሩት።

በኢየሱስና በእነዚህ ነቢያት ማመኑን የተናገረው እስልምና ስለ ምን ታዲያ አዲስ ሃይማኖት መመሥረት አስፈለገው? በቁርዓን ውስጥ የተገለጠው «ያህዌ ኤሎሂም» እኛ በመጽሐፍ ቅዱስ የተረዳነውን

እግዚአብሔርንና ኢየሱስን ከቶ አይመስልም። የእስልምናና የክርስትና እምነት ተመሳሳይ የሚመስሉን ላይ ላዩን ስንመለከት ብቻ ነው።

## ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች በሚከተሉት ነጥቦች ይስማማሉ፡-

* እግዚአብሔር ዓለምንና በውስጧ ያሉትን እንዲሁም መንግሥተ ሰማይንና ሲዖልን ፈጥሯል።
* እግዚአብሔር ፍጹም ኃያል፥ ሁሉን የሚያውቅ፥ በማንኛውም ቦታ ምን ጊዜም የሚገኝ ነው።
* እግዚአብሔር ፈቃዱን በአንዳንድ ነቢያት በኩል ለሰው ልጅ ገልጿል።
* እግዚአብሔር ሕይወታቸውን እንዲመሩበትና በደል ከመፈጸምም እንዲከለከሉበት ለሰው ልጆች ሕግጋትን ሰጥቷል።
* እግዚአብሔር በሁሉም ሰው ላይ ይፈርዳል። በፍርድ ቀን እኩሌቶቹን መንግሥተ ሰማይ ሲያገባቸው ቀሪዎቹን ወደ ሲዖል ይሰዳቸዋል።

## ነገር ግን እስልምና መጽሐፍ ቅዱስን ቀጥሎ ባሉት ነጥቦች ይጻረራል፡-

* ኢየሱስ ከነቢይ በላይ አልነበረም፤ የአምላክ ልጅም አልነበረም (ሱረቱ 5፡78)።
* ኢየሱስ መልካም ሰው ነበር፤ መለኮታዊነት ግን የለውም (ሱረቱ 5፡19)።
* እግዚአብሔር «ሥላሴ» (አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ) አይደለም፤ እንዲህ ማለት የእግዚአብሔርን ስም መሳደብ ነው (ሱረቱ 4፡171፤ 5፡75-78፥ 119)።
* ኢየሱስ ለኃጢአተኞች ሲል በመስቀል ላይ አልሞተም (ሱረቱ 4፡157)።
* በኢየሱስ መሥዋዕትነትም ሆነ በሌላ ተተኪ መሥዋዕት የኃጢአት ሥርየትም ሆነ ኃጢአተኛው ከእግዚአብሔር ጋር የሚታረቅበት መንገድ የለም (ሱረቱ 22፡36፥ 37) (ሱረቱ ማለት የቁርዓን ምዕራፍ ማለት ነው)።

## ወሳኙ ነጥብ፡-

ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ሳይሆን ነቢይ ብቻ ከሆነ፥ የሥላሴ ማለትም የእግዚአብሔር አካል ካልሆነና ኃጢአተኞችን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ በመስቀል ላይ ካልሞተ፥ እንግዲያውስ ክርስቲያኖች ሁሉ የሚያምኑት ውሸት ነው። እንደዚሁም መጽሐፍ ቅዱስ ሙስሊሞች እንደሚሉት የእግዚአብሔር ቃል አይደለም፤ እውነትነትም የለውም፤ የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ በሰዎች ተለውጧልና! እኛም እግዚአብሔር ባልተናገረው ነገር ስላመንን ያልዳንንና ገሃነም የሚጠብቀን ነን!

ነገር ግን ኢየሱስ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ልጅ ከሆነ፥ መጽሐፍ ቅዱስ የማይለወጥ የእግዚአብሔር ቃል እውነት ከሆነና ኢየሱስም ለእኛ ሲል በመስቀል ላይ ከሞተ፥ ሙስሊሞች ሁሉ አልዳኑም፤ የገሃነም ፍርድ ይጠብቃቸዋል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚያቀርብላቸውን ደኅንነት ለመቀበል አልፈለጉም።

ሙስሊሞች እንዲህ ይላሉ፡-

«እኛ ፍጹም የሆነ እውነት አለን። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ተለወጠ እውነትነት የለውም፤ ለዚህም ነው እግዚአብሔር ቁርዓንን የላከው፤ ስለ ሆነም ሰዎች ሁሉ ትክክለኛውን መንገድ ለማመን ይችላሉ!»

ክርስቲያኖችም እንዲህ ይላሉ፡-

«የያዝነው መጽሐፍ ቅዱስ የማይለወጥ የእግዚአብሔር ቃል ነው። የሚናገረውንም ሙሉ በሙሉ እናምናለን።»

## እንግዲህ ትክክለኛው ማነው?

- ሙስሊሞች «እኛ ነን!» ይላሉ።
- ክርስቲያኖችም በበኩላቸው «እኛ ነን!» ይላሉ።

የምናምነው የእግዚአብሔር እውነት እንደ ሆነ እንዴት ልንረዳና እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን? ዘላለማዊ ፍጻሜያችን በዚህ ላይ ስለሚደገፍ፥ እነዚህን ጥያቄዎች በጥንቃቄ መመርመር አለብን!

## ጥቂት የታሪክ አሰሳ፡-

ጌታ ኢየሱስ የተወለደው በእስራኤል አገር ነበር። ሕይወቱን ሁሉ እዚያ ኖሮ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ። ከዚያም ከመቃብሩ ተነሣ፤ ወደ ሰማይም ዐረገ። እስራኤል የሦስት ክፍለ ዓለማት መጋጠሚያ ማዕከል ናት፤ እነዚህም አውሮፓ፥ እስያና አፍሪካ ናቸው።

ሐዋርያትና ወንጌላውያን የምስራቹን ቃል (ወንጌልን) ለሰዎች ሁሉ ማካፈል እንደ ጀመሩ፥ በተለይም አዲስ ኪዳን ተዘጋጅቶ ባለቀበት ወቅት ወንጌል በፍጥነት ተሰራጨ። መጀመሪያ ለእስራኤል ቅርብ በሆኑ አገሮች፥ እንዲሁም በኢትዮጵያና በሰሜን አፍሪካ፥ በኋላም በአውሮፓና በመጨረሻም በሌሎች አገሮች ሊዳረስ በቅቷል። ስለዚህም ነው እናንተ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ጌታ ኢየሱስ ለእናንተም ስለ አደረገላችሁ ነገር የሰማችሁት - የተማራችሁትም። ይሁንና ብዙዎች ጎረቤቶቻችሁና ጓደኞቻችሁ ይህን አያውቁም! እንዴትስ ሊያውቁ ይችላሉ?

በዚያን ጊዜ (በአዲስ ኪዳን ዘመን) ሐዋርያትና ወንጌላውያን በቀላሉ ሊሄዱባቸው ያልቻሉ በርካታ አገሮች ነበሩ። ከእነዚህም አንዱ ሰፊው እና የአሸዋማው በረሀ አገር ዐረቢያ ነበር። ምንም እንኳን ጌታ ኢየሱስን ከልብ መውደዳቸውን ወይም አለመውደዳቸውን በትክክል ባናረጋግጥም ጥቂት ክርስቲያኖች በዚያ ነበሩ። ምናልባት መጽሐፍ ቅዱስ እንኳን አልነበራቸው ይሆናል። በዐረቢያ የሚኖሩ አይሁዶችም ደግሞ ነበሩ። እነርሱም የሚያምኑት በብሉይ ኪዳን ነው፤ ነገር ግን አጥብቀው አልያዙም።

የዐረቢያ ሰዎች ከብት አርቢዎች ነበሩ። ፍየሎች፥ በጎች፥ ፈረሶችና ግመሎች ያረቡ ነበር። በተጨማሪም ነጋዴዎችም ነበሩ። በዚያን ዘመን መኪናዎችና ባቡሮች ስላልነበሩ በየብስ ላይ የሚከናወነው ጉዞ ሁሉ የሚደረገው በግመሎች ነበር። ከአፍሪካ ወደ አውሮፓና እስያ ከሚያደርሱት ዋነኛ መተላለፊያዎች አንዱ በዐረቢያ በኩል ነበር። ስለ

ሆነም ነጋዴዎች ከአፍሪካ ዕቃዎችን አምጥተው ወደ [illegible] ወስደው ይሸጣሉ፤ እንዲሁም ለአፍሪካ ሌሎች ዕቃዎችን ያመጣሉ።

# 2. መሐመድ - የእስልምና ነቢይ

## እስልምና እንዴት ተጀመረ?

አብዛኛው የዐረቢያ ሕዝብ አረማውያን ነበሩ። የሚያመልኩት በብዙ አማልክት ነበር፤ አማልክታቸውን የሚያመልኩበትንም መቅደስ «ካባ» ይሉት ነበር። በዐረብኛ «ካባ» «ኪዩብ» የሚለውን የእንግሊዝኛን ቃል ይተካዋል። በዚህ መቅደስ ውስጥ «ሑባል» የሚባል ጣዖትም ነበር። የተወሰደውም ከእስራኤል በስተምሥራቅ ካለው ከሞዓብ አገር ነበር። «ሃበዓል» የተባለውም ጣዖት የሚመለከው በዚያው በሞዓብ አገር ነበር። በብሉይ ኪዳን ስንመለከት የአብርሃም፥ የይስሐቅ፥ የያዕቆብ፥ የእስራኤል አምላክ ይህን የባዕድ አምላክ እንዳያመልኩ ለሕዝቡ ያስጠነቅቃቸዋል (ዘዳግም 25፡1-3፤ ዘሌዋውያን 18፡1-5፤ መሳፍንት 2፡10-13፤ 1ኛ ነገሥት 18፡16-40)። በሑባልና በሃበዓል መካከል ያለውን ተመሳሳይነት ለመገንዘብ የሚያዳግት አይሆንም።

> ስለ መሐመድና ቤተሰቡ፥ ስለ ጓደኞቹ፥ ስለ ጥንቱ የእስልምና ታሪክ የምናውቀው ሁሉ፥ ከእስልምና ምንጮች የተገኘ ነው። እነዚህ ምንጮች ባይኖሩ ኑሮ ምንም ልናውቅ አንችልም ነበር።

ከእነዚህ ምንጮች የተገኘው መረጃ እንደሚያስረዳው፥ የመሐመድ ወንድ አያት ወንዶች ልጆች አልነበሯቸውም። ስለዚህም ወንዶች ልጆች እንዲሰጣቸው ለመጸለይ ወደ ካባ ይሄዳሉ። በሑባል ሐውልት ላይ እጃቸውን በማኖር «አላህ፥ እባክህ ወንዶች ልጆች ስጠኝ» ሲሉ ይማጸናሉ። አሥር ወንዶች ልጆች ከሰጣቸውም አንዱን ለሑባል /አላህ መሥዋዕት አድርገው እንደሚያቀርቡ ይሳላሉ። እነሆ አሥር ወንድ ልጆችም አገኙ። ወደ ሑባል ጣዖትም ሄዱ (ያ ጣዖትም «የከተማይቱ ጌታ» ይባል ነበር)፤ ለአላህም መሥዋዕት ለማቅረብ ወደዚያ ሲደርሱ፥ ዐብደላ በተባለው ልጃቸው ላይ ምርጫው አረፈ። (የስሙ ትርጉም የአላህ አገልጋይ ማለት ነው።) ይህም ዐብደላ የመሐመድ አባት ለመሆን

በቃ። ለሑባል ከመሠዋት ያተረፈውም በምትኩ 100 ግመሎችን እንዲያቀርቡ ጣዖቱ በአንድ ጠንቋይ በኩል ተጠይቆ ስጦታውን በመቀበሉ ነው። ስለዚህም ዐብደላ በሕይወት ለመኖር ታደለ።


እነዚህ ሁኔታዎች ሁሉ የሚያሳዩት የመሐመድ ዘመን በጥንቆላና በጣዖታት አምልኮ ምን ያህል እንደ ተገዛ ነው። ይህም በሕይወቱ ላይ ተጽዕና እንደሚያሳድር ጥርጥር የለውም። በቁርዓን ውስጥ «የታዘዝኩት የዚህችን አገር ጌታ እንድንገዛ ነው . . .» የሚለውን የመሐመድን ቃል እናነባለን (ሱረቱ 27፡91)።

በእርግጥ ይህ ማለት «አላህን» እንደ ሆነ ሙስሊሞች ሁሉ ይስማማሉ። ምናልባትም ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ! በዚያን ጊዜ ግን ሑባል ነበር የመካ ከተማ ጌታ። በተጨማሪም አላህ የሚለው ቃል ለሌሎችም «አማልክት» ሁሉ እንደ መጠሪያ ያገለገለ ስም ነበር። እንዲሁም በወቅቱ ዐዐረቢያ የሚመለኩት የሦስቱ ሴቶች አማልክት (የ«ላት»፥ የ«ኡዛ» እና የ«መናት») አባት ተብሎም ይጠራ ነበር።

ይህን ምትሐታዊ ተጽዕኖ ግምት ውስጥ ስናስገባ፥ የመሐመድ ኃይለኛ ገልፍተኛ መሆን ብዙም አያስደንቀንም። (ግልፍተኝነቱ በግልጽ እየታወቀ የመጣው ከሒጂራ በኋላ ነው።) ጨለማን አጥብቆ ስለሚፈራም በምሽት ወደ አንድ ክፍል ከገባ በኋላ ፋኖስ እስኪበራለት ድረስ አይቀመጥም ነበር። አል-ቫቂዲ የተባለው የመሐመድ የሕይወት ታሪክና የእስልምና ታሪክ ጸሐፊ እንደዘገበው መሐመድ የመስቀል ቅርጽ ላላቸው ነገሮች ከፍተኛ ጥላቻ ስለ ነበረው የዚያ ዓይነት ምስል ይዞ ወደ ቤቱ የሚገባውን ዕቃ ይሰባብር ነበር («የመሐመድ ሕይወት ታሪክ» በሰር ውሊየም ምዩር ገጽ 200)።

ሌላም አነጋገር በሙስሊሞች ዘንድ አለ፤ ይኸውም ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣና እንደሚፈርድ፥ በዚያን ጊዜም «መስቀሎችን ይሰባብራል፤ አሣማዎችንም ይገድላል» (ሳሂህ ሙስሊም 1፥ ገጽ 92) የሚል ነው።

## የመሐመድ አነሣስ




መሐመድ የተወለደው ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ከ570 ዓመታት ያህል በኋላ የዐረቢያ የንግድ ማዕከል በሆነችው በመካ ነው። መሐመድ ሲወለድ አባቱ በሕይወት አልነበሩም። እናቱም ገና የ6 ዓመት ልጅ ሳለ በሞት ተለዩት። ከዚያም ያሳድጉት ዘንድ የተረከቡት ወንድ አያቱ ናቸው። እርሳቸውም ሲሞቱ ከአጎቱ ጋር ኖረ።

መሐመድ ሃያ አምስት ዓመት ሲሞላው ቀጣሪው የነበረችውን ከዲጃ የምትባል ሴት አገባ። እሷም ሁለት ጊዜ አግብታ ሁለቱም ባሎችዋ የሞቱባት ሴት ነበረች። መሐመድ በሰላም የሚኖር ጭምት ወጣት ነበር። በ15 ዓመታት ከምትበልጠው ከከዲጃ ጋር የነበራቸውም ትዳር ከ25 ዓመታት በኋላ በከዲጃ ሞት አበቃ። ስለ መሐመድ የምንረዳው ነገር ቢኖር በንጽሕና የሚኖርና ጭምት ወጣት እንደ ነበረ ነው። በመሐመድና በከዲጃ መካከል ጥሩ ግንኙነት የነበረ ይመስላል። ብዙ ልጆች ቢኖሯቸውም፥ ብቸኛው ወንድ ልጃቸው በሕፃንነቱ ስለ ሞተባቸው መሐመድ እጅግ አዝኗል።

### የመሐመድ የመጀመሪያ ራእዮች

በተወለደ በ40 ዓመት ዕድሜው፥ ባለቤቱ ከዲጃ ከመሞቷ ከ10 ዓመት ቀደም ብሎ መሐመድ ድምፆችን መስማት ጀመረ። የሚሰማውንም በጥሞና ለማሰላሰል በተደጋጋሚ ከከተማ በመውጣት ሂራ በተባለ ተራራ ወደሚገኝ ዋሻ እየሄደ አንዳንዴ ብዙ ቀናት እዚያ ያሳልፍ ነበር። በዚያም ዋሻ ውስጥ በኋላ የሙስሊሞች «ቅዱስ

መጽሐፍ» የሆነውን ቁርዓንን ተቀበለ። ይህንንም ከመልአኩ ገብርኤል እንደ ተቀበለ ተናግሮአል። በመጀመሪያ እጅግ ፈራ። ከዚያም በኋላ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ ለ22 ወይም ለ23 ዓመታት ያህል መልእክቶቹን ሲቀበል ቆይቷል። በእስልምና ባህላዊ ወጎች ዘንድ እንደሚታወቀው መሐመድ በመጀመሪያ በዚህ ነገር ይጨነቅ ነበር። አንዳንዴ አረፋ ይደፍቅና እንደ ግመልም ያስካካ ነበር። አንዳንድ ጊዜም የሞተ ይመስልና እንደ ሰከረ ሰውም ይሆን ነበር።

በመጀመሪያ መልእክቱ «አንድ አምላክ ብቻ አለ፤ እሱም አላህ ነው» ይልና ሌሎች አማልክት መውደም እንዳለባቸው አጥብቆ ያመለክታል። በማያያዝም ስለሚመጣው የፍርድ ቀን፥ ስለ መልካም ምግባር አስፈላጊነት፥ እንዲሁም በመንግሥተ ሰማይ ወይንም በሲዖል ስለሚኖረው ዘላለማዊ ሕይወት ያስጠነቅቅ ነበር። ሲዖልንና መንግሥተ ሰማይን እጅግ ሥዕላዊ በሆነ ሁኔታ ይገልጻቸዋል። በሰማይ የሚኖሩ በመልካም ነገሮች ሁሉ ይረካሉ፤ እነዚህም ድንቅ ምግብ፥ ፍራፍሬና ወይን፥ እንዲሁም እንደ ዕንቁ የሚያንጸባርቁ ዓይኖች ያሉአቸው ልጃገረዶች ናቸው። በሲዖል ውስጥ ለመታደስ ቢሆን ለሐሴት የሚሆን ምንም ነገር የለም። በዚያ ያሉትም የፈላ ውኃ፥ መግልና የመረሩ ፍሬዎች ለዘላለም መጠጣት ይኖርባቸዋል (ሱረቱ 56፡ 1-56)።

ይሁን እንጂ መሐመድ በመጀመሪያ ስብከቱ ምንም ያህል አልተሳካለትም ነበር። የመካ ነዋሪዎችም ያላግጡበት ነበር። እንዲያም ሆኖ ሚስቱ የመጀመሪያ ተከታዩ ሆነችለት። ከዓመታት በኋላ ግን ሌሎች ሁለት መቶ ተከታዮቹን አፍርቷል።

አንድ ቀን መሐመድ የመካን ሰዎች ያስደሰተ ራእይ አየ። «ላት፥ ኡዛና መናት እነዚህን ሦስቱን አስተውለህ ታውቃለህ? የእነርሱ ምልጃ ተስፋ የሚጣልበት ነው።» ባዕድ አምላኪዎቹ ለሃይማኖታዊ በዓላቸው ወደ ካባ በመጡ ጊዜ እነዚህኑ ቃላት እየደጋገሙ በመዘመር ሰባት ጊዜ ዙሪያውን እየዞሩ «ላት፥ ኡዛና መናት እነዚህን ሦስቱን አስተውለህ ታውቃለህን? የእነርሱ ምልጃ ተስፋ የሚጣልበት ነው» ብለው ይዘምሩ ነበር። ይህን ራእይ ከአየ በኋላ ብዙ የመካ ሰዎች ወደ እስልምና ተለወጡ፤ የመሐመድና የተባባሪዎቹም ስደት ለትንሽ ጊዜ ተገታ። ይሁንና ታሪኩን በመቀጠል፥ እነዚህ አነጋገሮች ወይም ጥቅሶች (ሱረቱ

53፡19፥ 20) በሰይጣን ምሪት እንደ መጡና በኋላም መልአኩ ገብርኤል «ምልጃቸው ተስፋ የሚጣልበት ነው» የሚለውን የመጨረሻውን ክፍል እንዳስወገደ ይናገራል። በዚህ ዓይነት አንዳንድ ጥቅሶች ከቁርዓን የተወገዱ ሲሆን ሌሎችም ተጨምረዋል።

## የመሐመድ ወደ መዲና መሰደድ

ይህ የመሐመድ የራእይ ለውጥ የመካን ሰዎች የበለጠ እንዲጻረሩት ስለ አደረጋቸው፥ መሐመድ ጥሪን ተቀብሎ ወደ መዲና ለመሄድ ወሰነ። መዲና ከመካ በስተ ሰሜን 250 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ትገኛለች። በዚህን ጊዜ ከዲጃ በሞት ተለይታው ነበር። በዚያች በመዲና ከተማ ሙስሊሞች፥ ሦስት የአይሁድ ነገዶች እና አረመኔዎችም ነበሩ። እነርሱም እየመራቸው ብያኔን የሚሰጠውን ሰው ፈለጉ። መሐመድም በላያቸው ላይ አለቃ ሆኖ በኋላ «መዲና» ወደ ተባለችው ያትሪብ ከተማ ሸሸ። (መዲና የነቢዩ ከተማ እንደ ማለት ነው።) ወደ በኋላ ላይ እንደምናገኘው ይህ የስደት ጉዞ ሒጂራ በመባል ይታወቃል። ይህም ሒጂራ የእስልምና ዘመን አቆጣጠር መነሻ ሆነ። ጊዜውም በ622 ዓ.ም. ነበር።

## የመሐመድ ሕይወት መለወጥ

አሁን በ52 ዓመቱ በመሐመድና እርሱ በመሠረተው የእስልምና እምነት ላይ ፍጹም አዲስና ልዩ የሆነ ለውጥ የተከተለበት ወቅት መጣ፤ ትሑት፥ ዝምተኛና ታማኝ የነበረው ሰው ቀስ በቀስ ኃይለኛና ወንዳወንድ ሆነ። 13 ሚስቶችንም አገባ፤ ይህም ዛሬ ሙስሊሞች እንደሚያስቡት ባሎቻቸውን ላጡ ምስኪኖች መጠለያና ክብካቤ ለመለገስ የታቀደ አልነበረም። የተጠቀሰው ጉዳይ በቀድሞውም የእስልምና ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ተመዝግቧል።

ከሁሉም በዕድሜዋ ወጣት የነበረችው ሚስቱ አይሻ ትባላለች። መሐመድ አይሻን ሲያገባት ዕድሜዋ ሰባት ዓመት ቢሆንም፥ በሴት ልጅ ወግ የደረሰባት ግን በዘጠኝ ዓመቷ ነበር። የመሐመድ ሚስት ለመሆን ስትገባ አይሻ «የመጫወቻ አሻንጉሊቶች ይዛ ነበር» የሚለውን ማንበብ ልብን የሚነካ ነው (ሳሂህ ሙስሊም ቅጽ 3 ገጽ 716)።



መ ሐ መ ድ ለራሱ፥ ለቤተሰቡ፥ ከእርሱ ጋር ወደ መዲና ለመጡ 100 ለሚሆኑ ተባባሪዎቹና ለቤተሰቦቻቸው መ ተ ዳ ደ ሪ ያ የሚሆን ነገር መፈለግ ነበረበት። ስለዚህ ዕቃ የጫኑ ባለ ግመሎች መካውያን በደፈጣ ተወጉ። የተዘረፉት ዕቃዎች ሁሉ ሲወሰዱ የተማረኩ ባለ ንብረቶችም መካ ለሚገኙ ቤተሰቦቻቸው ቤዛ እየተከፈለ ተመለሱ። ዛሬ እንዲህ ያለ ተግባር የሚፈጽሙትን ሰዎች ሽፍቶች ወይም ወንበዴዎች እንላቸዋለን። በእስልምና ግን «ቅዱስ ጦርነት» (ጂሀድ) ለመባል በቃ።

በእስልምና ታሪክ ውስጥ የሚቀጥለውን ሃሳብ እናገኛለን፤ «ይህ መንፈሳዊ ሽልማትና ጊዜያዊ ገቢ ለማግኘት ከሁሉም የተሻለ ዘዴ ነው። ድል ከነሣን፥ በሌላ በምንም ዓይነት መንገድ ሊገኝ የማይችለውን በርካታ የአገር ሀብት ማግኘት እንችላለን። ሽንፈት ወይም ሞት ቢያጋጥመንም ወደ ዘለዓለማዊ መንግሥተ ሰማይ እንገባለን . . .» (ሚሽካት 2፥ ገጽ 253)።

ከዚያም የመካ ሰዎች ለበቀል ተነሡና የባድር ጦርነት ተካሄደ። ሙስሊሞቹ አመቺ ቦታ በመያዛቸው ከሺህ የሚበልጡ የመካ ሰዎችን በ300 ሰዎቻቸው ለማሸነፍ ቻሉ። ይህም ድል በጦርነቶች ሁሉ እንደሚደረገው «የአላህ እገዛ ነው» ተብሎ ተወሰደ። ሌሎችም ውጊያዎች ተካሄዱ፤ ከአንዱ በቀር በሁሉም ውጊያዎች በቁጥሩ እያደገ የመጣው የሙስሊሞች ወገን አሸነፈ። በዚህ ጊዜ ነበር መሐመድ የሚከተለውን ራእይ ያየው:-

> «አጋሪዎቹን በአገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሉዋቸው፤ ያዙዋቸውም፤ ከበቡዋቸውም፤ ለነሱም (መጠባበቅ) በየመንገዱ ተቀመጡ . . .

እነዚያንም የካዱትን (በጦር ላይ) ባገኛችሁ ጊዜ ጫንቃዎችን በኃይል ምቱ ... በአላህና በመጨረሻው ቀን የማያምኑትን አላህና መልክተኛው (ሙሐመድ) እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትን ... ግብርን እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉዋቸው ... እውከትም እስከማትገኝ ሃይማኖትም ሁሉ ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ተጋደሉዋቸው» (ሱረቱ 9፡5፤ 47፡4፤ 9፡29፤ 8፡39)።

በዚህ መመሪያ ላይ በመንተራስ፥ እስልምና ዓለምን ለሁለት ከፍሏል። ይኸውም «ዳር-ኡል-እስላም» እና «ዳር-ኡል-ዓረብ» ማለትም «የእስልምና ግዛት» እና «የጦርነት ግዛት» ብሎ በመለየት ነው። የዚህም ጥረት ዓላማ ፍጹም ዓለም-አቀፍ አምባገነን ግዛት ለመመሥረትና በእስላማዊው ሕግ (ሼሪያ) የሚመራ እስላማዊ መንግሥት በሌለበት አገር ሁሉ፥ ክልሉን በእስልምና አገዛዝ ሥር ለማድረግ የሚቻለው ጥረት ሁሉ መደረግ አለበት።

## የዛሬው እስላማዊው መንምዣት ስለ አፍሪካ


የመሐመድን ነገር ለጊዜው ተወት እናርግና እስልምና በአሁኑ ጊዜ በአፍሪካ ላይ ምን እያደረገ እንደ ሆነ እስቲ በጥቂቱ እንመልከት። አፍሪካን የመጀመሪያዋ እስላማዊት ክፍለ ዓለም ለማድረግ የሚቻለው ጥረት ሁሉ እየተደረገ መሆኑ ምሥጢር አይደለም።

* በ1989 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) ከ24 የአፍሪካ መንግሥታት የመጡ የእስልምና ተወካዮች «የእስልምና ድርጅት በአፍሪካ» የተሰኘ ማዕከል ለመመሥረት በናይጂሪያ እንደ ተሰበሰቡ ታውቅ ኖሯል? በተዘጋጀውም መግለጫ ላይ እስልምናን በየሥፍራው ለመመሥረትና ሁሉንም የእስልምና ኮሚቴዎች ማጠናከርና በ24ቱ አባል መንግሥታትም ውስጥ ቁልፍ ቁልፍ ሥልጣኖች ለሙስሊሞች ብቻ እንዲሰጡ በግልጽ ተብራርቷል።

* በቁጥር ከሌላው ሕዝብ ይልቅ አናሳ በሆኑበት አገር እንኳን ሳይቀር መስጊዶችንና የቁርዓን ትምህርት ቤቶችን በየሥፍራው ለማቋቋም ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ እንደ ተመደበ ታውቅ ኖሯል? ማላዊ ውስጥ በየ15 ኪሎ ሜትሩ መስጊድ እየተሠራ መሆኑን፥ አንዳንድ ሰዎች ኢትዮጵያ ውስጥ የሙስሊሞቹ ቁጥር ከኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ልቆ መገኘቱን ሲናገሩ ሰምተህ ይሆን? ከጥቂት ዓመታት በፊት እስላም

ባልነበረበት በትስዋና እንኳ ብዙ መስጊዶች ተሠርተዋል። የከፍተኛ ትምህርት ሳይቀር በነፃ የሚሰጥባቸው ትምህርት ቤቶች ከመስጊዶቹ ጎን ለጎን ተሠርተዋል። የእስልምና ዩኒቨርስቲዎች በሚገኙባቸው የባሕር ማዶ አገሮች የሚማሩበት ሁኔታም እየተመቻቸ ነው።

* በእነርሱ ላይ ብቻ እንዲደገፉ ያሉበትን አገር ምጣኔ ሀብት እንዲቆጣጠሩ መንግሥትንም እንዲያደክሙበት በአፍሪካ ለሚገኙ ሙስሊሞች ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ መመደቡን ታውቅ ኖሯል?



ቁርዓንና ትምህርቱን ለተመለከተ ሰው ይህ እንግዳ ነገር ሊሆንበት አይችልም። የዐረቡን ዓለም የዘይት ሀብታቸው የማያልቅ ብልጥግና ስለ ሰጣቸው እስልምናቸውን ለማስፋፋት በከፍተኛ ደረጃ ጠቅሞአቸዋል። ከሁሉም በላይ ጠንካራ ተፎካካሪያቸው የሆነውን የክርስትናን እምነት ለማጥቃት ረድቷቸዋል። ይህ ጉዳይ በመላው አፍሪካ እየታየ ነው። የአፍሪካን «ነፍስ» ለመማረክ በሚደረገው ትግል ማን ያሸንፍ ይሆን? ክርስቲያኖች የሆንን ሁሉ አንድ ሆነን በመተባበር የምንችለውን ሁሉ በማድረግ ወንጌልን እንሰብክላቸው፥ እናስተምራቸውና፥ ደቀ መዛሙርት እናደርጋቸው ይሆን? ለሙስሊሞቹስ የዘላለም ሕይወት ብቸኛውን ተስፋቸው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሆነ ለመግለጽ እንጣጣር ይሆን? ወይስ ይህን ሕዝብ ለእስልምና አሳልፈን እንሰጣለን?

## ክርስቲያኖችስ ምን ማድረግ ይገባናል?

ጌታ ኢየሱስ «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ» ብሏል (ዮሐንስ 14፡15)። በዚህ ቃል ታላቁን ትዕዛዝና ታላቁን ተልዕኮ ሰጥቶናል።

«ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፥ በፍጹም ነፍስህም፥ አሳብህም ውደድ፤ ...ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ፤ ... (ማቴዎስ 22፡37፥39)። «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» (አሕዛብ ሲል፥ ሙስሊም የሆነውን ሱማሌ፥ ቱዋሬግ፥ ሐውሳ፥ ስዋሂሊ፥ ዐረብ፥ ፓኪስታኒ ማለት አይደለምን?) (ማቴዎስ 28፡18-20)።

## ልብ በል! አስተውል

ጌታ ኢየሱስን ለመከተል ስንወስን ፈቃዱንም ለማከናወን መወሰናችን ነው። በመንፈሳዊ ሕይወታችን በሚገባ ለመጠንከር የእግዚአብሔርን ቃል በየዕለቱ ማንበብ አለብን። አለዚያማ እኛ የማናውቀውን እምነት እንዴት አድርገን ለሌሎች ማካፈል እንቃጣለን? የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዕቅድ መሥሪያ ቤታችንን ብትጠይቅ ልታገኝ ትችላለህ። ከዚህም ሌላ የሙስሊሞችን ስሜትና አስተሳሰብ ተረድተን በሚገባቸው አቀራረብ የክርስቶስን ወንጌል ልንመሰክርላቸው እንዲያስችለንም ስለ እስልምና መማር እንዳለብን አትዘንጋ።

## የማንዘነጋውስ ጉዳይ!

ሙስሊም ወገኖቻችንን እንድንወጋ እግዚአብሔር አልጠራንም። ጠላቶቻችንን መታገሥ ብቻ ሳይሆን ምንም እንኳን ለፍቅራችን ወረታውን ባይመልሱና ወደ አዳኙ መምጣትን እምቢ ቢሉም ልንወዳቸው ግን ይገባል።

> የእስልምና ሃይማኖት በአሠራሩ የክርስትና እምነት ጠላት ነው። ሙስሊሞቹ ግን ለእግዚአብሔር የተወደዱ ናቸው። ለእነርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቶላቸዋል! እኛንም የምስራቹን ቃል እንድንናገር አዞናል።

## መሐመድ በመዲና

እንደገናም ወደ መዲና ስንመለስ የምንረዳው፥ ሦስቱ የአይሁድ ነገዶች መሐመድን እንደ እግዚአብሔር ነቢይ አለመቀበላቸውን ነው። ስለዚህም ከባድ ጉዳት በአይሁዶቹ ላይ አድርሶባቸዋል። አንዳንዶቹ ተሰደዋል፤ የቀሩትም አንገታቸውን በሰይፍ ተቀልተዋል። በአንድ ወቅት መሐመድ ከአይሁድ ነገዶች የአንዱን ወገን ወንዶች በሙሉ ለየት ያለ ትዕዛዝ አዘዛቸው። በትእዛዙም መሠረት በመዲና ገበያ መሐል ለመሐል ምሽግ የሚመስል ጉድጓድ እንዲቆፍሩ አደረገ። ከተቆፈረም በኋላ ከ600 እስከ 800 የሚሆኑ አይሁዶች ራሳቸው እየተቀላ ተቀበሩበት። ሴቶቻቸውም ለሙስሊሞች በቁባትነት ተከፋፈሉ። መሐመድም ለራሱ «ሪሃና» የተባለች ሴት ወሰደ። ቁባቱ ግን እርሷ ብቻ አልነበረችም።

መሐመድ የበለጠ ኃያል እየሆነ በሄደ ቁጥር ጠባዩም እንዲሁ እጅግ እየተለወጠ መጣ። «የአላህና የመልእክተኛው ጠላቶች» ያላቸውን በርካታ ሰዎች እንዲገደሉ አዘዘ። በዚህም ዓይነት ሃያ ሰባት ሰዎች እንደ ተገደሉ ተዘግቦአል።

## የመሐመድ ራእዮች ብዙ ጥቅሞች አስገኝተውለታል

የመሐመድ ራእዮች ብዙዎቹ ለራሱ ጥቅም ነው የዋሉት። ለምሳሌ ቁርዓን ለሙስሊም ወንዶች አራት ሚስቶችን ይፈቅዳል። (ለሴቶቹ ግን ይህ የማይታሰብ መሆኑን ልብ በል።) መሐመድ ግን ደስ ያለውን ያህል ሚስቶች ሊኖሩት ይችላሉ።

> «አንተ ነቢዩ ሆይ! እኛ እነዚያን መህርቻቸውን የሰጠሃቸውን ሚስቶችህን፥ አላህ ባንተ ላይ ከመለሰልህም እነዚያን እጅህ የጨበጠቻቸውን ምርኮኞች፥ ... ለአንተ ፈቅደንልሃል። የአመነችንም ሴት ነፍሷን (ራሷን) ለነቢዩ ብትሰጥ ነቢዩ ሊያገባት የፈለገ እንደ ኾነ፥ ከምእመናን ሌላ ላንተ ብቻ የጠራች ስትኾን (ፈቀድንልህ)፤ ... ከነሱ የምትሻትን ታቆያለህ፤ የምትሻትንም ወደ አንተ ታስጠጋለህ፤ (በመፍታት) ከአራቅሃትም የፈለግሃትን (በመመለስ ብታስጠጋ) በአንተ ላይ ኃጢአት የለብህም» (ሱረቱ 33፡50-51)።

ከዚህ በላይ የተነበበው ሁኔታ እንደምን እንደ ተፈጸመ የእስልምና ልማዳዊ መረጃዎች ያስረዱናል። ተወዳጁ የመሐመድ ሚስት አይሻ የሚከተለውን እንዳለች ተመዝግቧል፤

«እነዚያ ራሳቸውን ለአላህ መልእክተኛ ያቀረቡትን ሴቶች እነቅፋቸው ነበር። ‹ለመሆኑ ሴት ራሷን አሳልፋ ትሰጣለችን?› ብዬም ጠየቅሁኝ። ከዚያም ሁሉን የሚችለው አላህ ‹የምትፈልገውን መተው፥ የምትወደውን ለራስህ መውሰድ ትችላለህ› ብሎ ተናገረ ... እኔም ‹ምኞትህን ለመሙላት ጌታህ የቸኮለ ይመስላል› አልሁት» (ሚሽካት 1 ገጽ 210)።

የመሐመድ ሥልጣን የሚጋፋት ዓይነት አልነበረም፤

«አላህና መልክተኛው ነገርን በፈረዱ ጊዜ ለምእመናንና ለምእመናት ከነገራቸው ለነርሱ ምርጫ ሊኖራቸው አይገባም!» (ሱረቱ 33፡36)።

ይህ ውሳኔ የተላለፈው የቀድሞዎቹን ሕግጋት በመጣስ የማደጎ ልጁን ሚስት አፍቅሮ ከማግባቱ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ነበር። እርሷንም ለማግባት ሲል በእጅ አዙር ልጁን በመገፋፋት እንዲፈታት አደረገ።

መሐመድ ከሚስቶቹ በአንዷ ላይ በደል በፈጸመበት ጊዜ ገመናውን የሸሸጉለት እንደ ሆነ ለእርሷና ለሌላዋ ሚስቱ መልካም ነገር እንደሚያደርግላቸው ቃል ገባ። ዳሩ ግን እነርሱ እሺ አላሉም። ወዲያውም ይህ መገለጥ መጣለት።

«ሚስቶችህን ማስወደድን የምትፈልግ ስትኾን ... አላህ ለናንተ የመሐሎቻችሁን መፍቻ ደነገገላችሁ፤ አላህም ረዳታችሁ ነው ...» (ሱረቱ 66፡1-2)።

በዚህ ቃል መኃላውን ለማፍረስ ደፈረ። ስለሆነም በሕይወቱ መጨረሻ ላይ እንዲህ ማለቱ አያስደንቀንም፡-

«ማንም ትእዛዜን የሚቀበል ሁሉ ወደ ገነት ይገባል፤ የማይታዘዘኝ ግን እርሱ ወደ ገነት ለመግባት አልፈለገም» (ሚሽካት 1 ገጽ 173)።


## የመሐመድ ሕይወት መጨረሻ

መሐመድ ዱሮ ይኖር የነበረበትን የመካ ከተማ በጦር ኃይል ካሸነፈ በኋላ በ632 ዓ.ም. ሞተ። ወደ ከተማይቱ የመጣው ከ10000 ጦረኞች

ጋር ሲሆን፥ መካውያን ያለ አንዳች መከላከል ነው እጃቸውን የሰጡት። ከዚያም ጣዖታቱን ሁሉ አወደመ፤ ነገር ግን በካባ አካባቢ ይካሄዱ የነበሩትን የአምልኮ ሥርዓቶች እንደ ነበሩ ተቀበላቸው።

## የእስልምና መስፋፋት

መሐመድ የዐረቡን መንግሥት የተሰናበተው ጠንካራና የተነቃቃ ሠራዊት ትቶለት ነው። ከእርሱ ሞት በኋላ «ሪዳ» በመባል የሚታወቅ



ዓመፅ በተከታዮቹ መካከል ተነሣ። አስቀያሚ የሆነ አድመኛነት፥ መመቀኛነትና አለመግባባት በቅርብ ተከታዮቹ መካከል ተፈጠረ። ዓመፁም በመሐመድ እግር በተተኩትና እጅግም ከሚቀርቡት ወዳጆቹ በዑስማንና በዓሊ መገደል አከትሟል። ወዲያውም እስላማዊው ጦር መላውን መካከለኛ ምሥራቅ፥ ሰሜን አፍሪካ፥ ከፊል ሕንድና እስፔይንን ለመውጋትና ለማሸነፍ በቅቷል።

በኋላ ግን ኃይል መጠቀሙን ባያቆምም በይበልጥ የተስፋፋው በነጋዴዎች ዝውውር አማካኝነት ነው። ሙስሊሞች የሰሐራን በረሃ ዘልቀው በመግባትና በመርከቦቻቸው ወደ ምሥራቃዊው የአፍሪካ ዳርቻ በመምጣት በብዙ ደሴቶች ላይ ሰፈሩ። ደሴቶችም ሞምባሳ፥ ዛንዚባር፥ ኮሞሮስ፥ ደግሞም ኢቦና ሌሎችም የሞዛምቢክ ደሴቶች ናቸው። በእነዚህም ሥፍራዎች ሆነው የአፍሪካ የባሕር ዳርቻዎችን በተጽዕኖአቸው ሥር ለማድረግ በቅተዋል።

ዛሬ በዓለም ከሚኖሩት ከ5 ሰዎች አንዱ ሙስሊም ነው። በዚህም በዓለም በትልቅነቱ ሁለተኛው ሃይማኖት ለመሆን ችሏል። ከእስልምናው የሚበልጠው የክርስትናው ማኅበረሰብ ብቻ ነው።

እባክህ፥ አሁኑኑ ከመጽሐፉ በስተጀርባ የሚገኙትን የጥናት ጥያቄዎች ሥራ።

# 3. ቁርዓን - የእስልምና መጽሐፍ


## ቁርዓን እንደ ምን ወረደ?

ቁርዓን ከ23 ዓመታት በላይ በሆነ ጊዜ ውስጥ ለመሐመድ ብቻ ተሰጥቷል። «ቁርዓን ሰማይ ቤት ካለው የአላህ ሰሌዳ ቀስ በቀስ እየተለቀቀ በመልአኩ ገብርኤል በኩል ለመሐመድ የተገለጠ ነው» ሲሉ ሙስሊሞች ያምናሉ። መሐመድም ደግሞ የተገለጠለትን ሁሉ በቃላቸው ሸምድደው የማስታወስ ኃላፊነት ላለባቸው ረዳቶቹ አካፈላቸው። አንዳንድ ክፍሎች ደግሞ ተጽፈዋል። ቁርዓን በይዘቱ በብዙ መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ መጽሐፍ ቅዱስን አጥብቆ ስለሚቃወም «ከሁለቱ የትኛው መጽሐፍ ትክክል ነው?» ብለን መጠየቅ አለብን። ምርጫውን ያላስተካከለ ሰው ወደ ዘለዓለማዊ ጥፋት ይሄዳል።

(«ያንንም፥ ይኸንንም አልማርገም» የሚል ቢኖር እርሱም ቢሆን ራሱን ከእግዚአብሔር የማግለል ምርጫ አድርጓል ማለት ነው።)

እንግዲህ ቁርዓን ምን ይመስላል? ወንጌልን ለሙስሊም ለማካፈል የሚፈልግ ማንም ክርስቲያን ስለ ሙስሊሞች አስተሳሰብ የበለጠ እንዲረዳ ቢያንስ የተወሰኑ የቁርዓን ክፍሎች ማንበብ አለበት።

## የቁርዓን አወቃቀር



ቁርዓን በመጠኑ ከአዲስ ኪዳን ትንሽ አጠር ያለ ሲሆን ልክ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ በምዕራፎችና በቁጥሮች የተከፋፈለ ነው። የአማርኛው ትርጉም 114 ምዕራፎችና በጠቅላላው 7436 ቁጥሮች (አንቀጾች) አሉት። አንዱ ምዕራፍ ሱራ ወይም ሱረቱ ሲባል ቁጥሩ ደግሞ አያት ይሰኛል። አያት ማለት «ምልክት» ማለት ነው። ጸሎት ከሚመስለው ከመጀመሪያው በቀር ምዕራፎቹ በርዝማኔያቸው ቅደም ተከተል ተቀምጠዋል። ከሁሉ የሚበልጠው ሁለተኛው ሱረቱ ሲሆን፥ ሦስተኛው ከሁለተኛው መለስ ያለ፥ አራተኛውም ከሦስተኛው አጠር ይላል፤ እንዲህም እያለ 114ኛው ሱረቱ ከሁሉም የአጠረ ነው። ታሪካዊ ቅደም ተከተል በፍጹም የለውም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ፍጥረት ለማወቅ ከፈለግን የመጀመሪያውን መጽሐፍ የመጀመሪያውን ምዕራፍ እንመለከታለን። ከዚያም ታሪካዊ የድርጊት ቅደም ተከተሎችን እንጠብቃለን። ከአዳም መፈጠር በኋላ ስለ ትውልዱ በተዋረድ እናነባለን፤ ከዚያም ስለ ኖኅ፥ አብርሃም፥ ይስሐቅ፥ ያዕቆብ፥ ዮሴፍ፥ ሙሴ፥ ኢያሱ፥ ሶምሶን፥ ሳሙኤል፥ ዳዊትና ሰሎሞን። ስለ ኢየሱስ የተጻፈውን ታሪክ ለማንበብ ከፈለግን ደግሞ ወደ ወንጌሎች እንመጣለን። እንዲህ ያለ ቅደም ተከተል በቁርዓን ውስጥ የለም። ብዙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሰዎችና ድርጊቶች የተጠቀሱበት ቢሆንም

የምናገኛቸው ግን በዘፈቀደ እዚያና እዚህ ተተራምሰው እንጂ በሥርዓት ተደርድረውና ተሳስበው አይደለም።

## ቁርዓን መጽሐፍ ቅዱስን ይጻረራል

ብዙ የቁርዓን ክፍል የተውጣጣው ከብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ነው። አገባባቸው ግን በአብዛኛው የተድበሰበሱና ግንዛቤ የጎደላቸው ናቸው። ለምሳሌም ያህል ጥቂቶቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፤

* ኖኅ አንድ ወንድ ልጅ ብቻ ነበረው፤ እርሱም በውኃ ውስጥ ሰጠመ (ሱረቱ 11፡42-43)። ለመሆኑ ኖኅ ስንት ወንዶች ልጆች እንዳሉት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራልን? እነርሱስ ሰጥመዋልን? (ዘፍጥረት 6 እና 7)።
* ቁርዓን የአብርሃም አባት ስም አዛር ነው ይላል (ሱረቱ 6፡74)። መጽሐፍ ቅዱስስ የአብርሃም አባት ስም ማን እንደሆነ ይናገራል? (ዘፍጥረት 11፡31)።
* እንደ ቁርዓን አገላለጽ ሙሴን የአሳደገችው የፈርዖን ሚስት ነች (ሱረቱ 28፡89)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሙሴን እንደ ልጅ የአሳደገችው ማን ናት? (ዘጸአት 1፡5-10)።
* ፈርዖን ወደ ሙሴ አምላክ ይሄድበት ዘንድ ከፍ ያለ ሕንፃ እንዲገነባ ለሐማን ነገረው። ይህ እንግዲህ የባቢሎን ግንብ መሆኑ ነው (ሱረቱ 28፡38)። ለመሆኑ የባቢሎንን ግንብ የሠራው ማነው? (ዘፍጥረት 10፡32-11፡4)። ለዚያውስ ሐማንና ፈርዖን በአንድ ዘመን ውስጥ ኖረዋልን? በጭራሽ አልኖሩም። ፈርዖን የነበረው የባቢሎን ግንብ ከተሠራ ከ800 ዓመታት በኋላ ነው። ሐማን ደግሞ የነበረው ፈርዖን ከአለፈ ከ900 ዓመታት በኋላ ነው።
* ቁርዓን እንደሚያስተምረው መሥዋዕቶች ለመብልነት ግሩም ናቸው። ይሁን እንጂ ሥጋቸውም ሆነ ደማቸው አላህ ዘንድ አይደርስም። ቁም ነገሩ ያለው በአቅራቢው ቅንነት ላይ ነው (ሱረቱ 22፡37)። መጽሐፍ ቅዱስ ለኃጢአታችን ስርየት ሊያስገኝ የሚችለው የመሥዋዕቱ ደም እንደ ሆነ በግልጽ ያስተምራል (ዘሌዋውያን 16፤ 17፡10)። እንዲሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ «አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋል»

(ዕብራውያን 10፡14)። እንዲሁም «በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጧል» (ዕብራውያን 9፡26)።

* የጌታ ኢየሱስ እናት ማርያም የአሮን እህት የኢምራን ልጅ እንደ ሆነች ቁርዓን ያስተምራል (ሱረቱ 19፡17-28)። ይኼስ እውነት ነውን? ኢምራን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሙሴና የአሮን አባት ነው። ሙሴ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አጎት ነበረን? የአሮን እህት የሆነችው ማርያም የኖረችው ኢየሱስ ከመወለዱ ከ1400 ዓመታት ቀደም ብላ አይደለምን?

> ይሄና ይህን የመሳሰለው ቁርዓንና መጽሐፍ ቅዱስ ሁለቱም ከእግዚአብሔር ሊመጡ እንደማይችሉ ሊያመለክተን ይችላል። መሐመድ ጥራዝ ነጠቅ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ስለ ነበረው ትክክል የመሰለውን ሁሉ አስተላልፏል።

## የቁርዓን ምንጮች

ብዙዎቹ የቁርዓን ታሪኮች ምንጮቻቸው በቀላሉ ሊደርስባቸው የሚችሉ ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ ታልሙድ፥ ሚሽናና የመሳሰሉት የአይሁድ መጽሐፎች ይጠቀሳሉ። ነገር ግን ስለ ኢየሱስ የተነገሩት አፈ ታሪኮች ሐዋርያዊ መልእክቶች አልነበሩምና በዚህ ምክንያት የአዲስ ኪዳን አካሎች ለመሆን አልበቁም።

ሌሎች የቁርዓን ክፍሎች ደግሞ ዞሮስትሪያን ከተባለው የፋርስ ሃይማኖት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። መሐመድ ሳልማን የሚባል ፋርሳዊ ጓደኛ ስለነበረው፥ ምናልባት ይህን መረዳት ከእርሱ አግኝቶ ሊሆን ይችላል የሚል አነጋገርም አለ።

ከዚህ በተጨማሪ ቁርዓን በመሐመድ ዘመን የተከናወኑ ታሪኮችና ትምህርቶችም አሉበት። እነዚህም በእርግጥ መሐመድንና የኑሮ ዘይቤውን የሚደግፉ፥ ተሰሚነቱን የሚያጎለብቱ በርካታ ትእዛዛቱንም ተገቢ ለማስመሰል የተጻፉ ምንባቦች ናቸው። ባመዛኙም የሚናገሩት ስለ ኋለኛው የመዲና ቆይታው ነው።

ለሙስሊሞች ቁርዓን መቅራት (መድገም) እንደ ጽድቅ ሥራ ይቆጠራል። አንዳንዶቹ ሙስሊሞች እንዲያውም ከቁርዓን ውስጥ አንድን ምዕራፍ በሙሉ ሸምድደው፥ መልእክቱ ቢገባቸውም

ባይገባቸውም በቃላቸው ይደግሙታል ያውም በዐረብኛ። ይህም «ሐፌዝ» የሚባል የክብር ስም ያሰጣቸዋል። አያሌ ሙስሊሞች ዐረብኛ ለማንበብ ቢችሉም፥ ትርጉሙን ግን አያውቁም። ጉዳዩም ይህን ያህል ዋጋ የሚሰጠው አይደለም! አስፈላጊው ነገር «ቅዱስን መጽሐፍ» ከመቅራቱ (ከመድገሙ) ላይ እንጂ፥ ከመረዳቱ ላይ አይደለምና! እዚህ ላይ እኛ ክርስቲያኖች ከእነርሱ እጅግ እንለያለን።

ከቁርዓን የተወሰነው ክፍል ለመሐመድ እንደ ተገለጠለት አንጠራጠርም። ይሁን እንጂ ይህ ራእዩ ከእግዚአብሔር መምጣቱን አናምንም፤ ምክንያቱም ቁርዓን መጽሐፍ ቅዱስን አጥብቆ ይቃወመናልና! መልእክቱን ከሰይጣን እንደ ተቀበለው ከመገመት ሌላ አማራጭ የለንም። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ግን እናምናለን፤ ማረጋገጫውንም ወደ ኋላ እናቀርባለን።

## ሌላስ ስለ ቁርዓን ማወቅ ያለብን ምንድነው?

## ሀ. ቁርዓን የተገለጸው በሰባት ዓይነት መንገድ ነበር

ገና መሐመድ በሕይወት ሳለ የቁርዓንን አንዳንድ ክፍሎች ሙስሊሞቹ በቃላቸው አጥንተው ይደግሙአቸው ነበር። በባህላዊ ወጋቸውም ውስጥ የሚያስገርም ነገር ሰፍሯል። እንዲህ ይላል፤

> «በኋላ የመሐመድ ወራሽ (ካሊፍ) የሆነው ዑመር ወደ መስጊድ ሲሄድ ሁለት ሌሎች ሙስሊሞች አንዱን ሱራ እርሱ ራሱ ከመሐመድ ከተማረው በተለየ መንገድ ሲደግሙ ሰማቸው። ዑመርም ተቆጥቶ ወደ ነቢያቸው ወደ መሐመድ ወሰዳቸውና ስለ ልዩ ቂርዓታቸው (አደጋገማቸው) ነገረው። መሐመድም ሁሉ በተለያየ መንገድ ሲደግሙት ሰማቸውና «እርግጥ ነው፤ ራእዩ የተገለጠው በዚህ ዓይነት ነው» አለ። ዑመርም በዚህ ምክንያት አለማመን ወደ አእምሮው እንደ ገባ ተናዘዘ። መሐመድም የካሊፉን ደረት መታ መታ በማድረግ «ይህ ቁርዓን የተገለጸው በሰባት ዓይነት መንገድ ነው፤ ስለ ሆነም ቀላል በሚመስልህ በማንኛውም መንገድ ቅራው (ድገመው)» አለ (ሚሽካት 3 ገጽ 702-704)።

## ለ. ከቁርዓን ክፍሎች አንዳንዶች ወጥተው በሌሎች ተተክተዋል

ሙስሊሞች ዛሬ ቁርዓን መቼም ቢሆን እንዳልተለወጠና አንዲትም «ነቁጥ» እንኳን እንዳልተቀየረች ሊያሳምኑን ይፈልጋሉ። ቁርዓን በሰማይ ከሚገኘው የዋናው ሰሌዳ ግልባጭ ነው ብለውም ይናገራሉ።

አባባሉ ምን ያህል ያልሰከነ መሆኑን ከሚከተሉት የቁርዓን ክፍሎች እንመለከታለን:-

> «ከአንቀጽ ብንለውጥ ወይም እርሷን ብናስረሳህ ከርሷ የሚበልጥን ወይም ብጤዋን እናመጣለን፤ አላህ በነገሩ ሁሉ ከሃሊ (ቻይ) መኾኑን አታውቅምን?» (ሱረቱ 2:106)።
>
> «በአንቀጽ ሥፍራ አንቀጽን በለወጥን ጊዜ፥ አላህም የሚያወርደውን ነገር ዐዋቂ ነው፤ አንተ ቀጣፊ እንጂ ሌላ አይደለህም ይላሉ፤ በውነቱ አብዛኞቻቸው አያውቁም» (ሱረቱ 16:101)።

መሐመድ ከቁርዓን ውስጥ በብዙ ቦታዎች ላይ ለውጥን አድርጓል። ከየሥፍራው አንድ ወይም ሁለት አባባሎችን እያወጣ በአዲስ አባባሎችና ሀሳቦች ሲተካቸው፥ የወጡትን ጥቅሶች «ማንሱክ» ብሎ ሲጠራቸው፥ የተጨመሩትን ደግሞ «ናሲክ» ብሎአቸዋል። ሂደቱም «የመሻር ደንብ» በመባል ታወቀ። ይህ የተፈጸመው ዛሬ ከምናየው የቁርዓን ጥራዝ መስተካከል በፊት በመሆኑ ምን ያህል ምንባቦች እንደ ተለዋወጡ ለማወቅ ያዳግተናል።

ዝነኛው የእስልምና ሃይማኖት ሊቅ ጁላሉድ ዲን ግን ከ5 እስከ 500 እንደሚሆኑ ገምቷል። እርግጠኛ ከሆኑባቸው መካከል ጥቂቱን ቀጥሎ ዘርዝረናቸዋል፤

| | |
|---|---|
| . የጸሎት አቅጣጫ ተለውጧል | (ሱረቱ 2:142-144)። |
| . የውርስ ክፍፍል ተለውጧል | (ስረቱ 4:7፥ 11)። |
| . የሌሊት ጸሎት ተለውጧል | (ሱረቱ 73:2፥20)። |

| | |
|---|---|
| . የአመንዝራነት ቅጣት ተለውጧል | (ሱረቱ 4፡15-16፤ 24፡2)። |
| . የቅዱስ ጦርነት ሕጎች ተለውጠዋል | (ሱረቱ 2፡256፤ 9፡3-5፤ 2፡217፤ 47፡4፤ 8፡39)። |
| . ወንጀል ሲፈጸም የሚሰጠው አጸፋ ተለውጧል | (ሱረቱ 2፡178፤ 5፡48፤ 17፡33)። |

ይህ ሁሉ ለውጥ የሚደረገው ግን ቀጥሎ የምናነባቸው ጥብቅ የቁርዓን ትዕዛዞች እንዳሉ ሆነው ነው፤

«የአላህንም ንግግሮች ለዋጭ የለም» (ሱረቱ 6፡34)።

«የአላህ ቃላት መለወጥ የላትም» (ሱረቱ 10፡64)።

እንዲያውም በጣም የሚያደናግር ሌላ ትእዛዝም አለ። እንዲህ ይላል፡-

«ብንሻም ያንን ወዳንተ ያወረድነውን በእርግጥ እናስወግዳለን፤ ከዚያም ላንተ በኛ ላይ በርሱ (ለማስመለስ) ተያዢን አታገኝም» (ሱረቱ 17፡86)።

ቁርዓን እንዲህ እርስ በእርሱ የተቃረነ የማይጣጣም ሆኖ ሳለ፥ የትኛው ሙስሊም ነው ስለ ሃይማኖቱ ግልጽና እርግጠኛ መልእክት ይዣለሁ ለማለት የሚደፍር?

## ሐ. የተለዩ ሌሎች የቁርዓን ቅጂዎች ነበሩ

በቁርዓን ውስጥ የተጨመሩ፥ ወይም የወጡ፥ ወይም ከቀደሙት ጽሑፎች የተለየ አባባል ያላቸው አንዳንድ ምንባቦችን እናውቃለን።

ከመሐመድ ሞት በኋላ የመጀመሪያው ካሊፍ የሆነው አቡ በከር የቁርዓን አባባሎች ሁሉ ተሰብስበው እንዲጻፉ ትእዛዝ የሰጠ የመጀመሪያው ሰው ነው። በርካታ ሙስሊሞችም ከመሐመድ በቃል የያዙትን ሁሉ ጻፉት። ብዛታቸውም 28 ያህል ነበር። በጣም የታወቁት የቁርዓን ጥንቅሮች የተዘጋጁት በኢብን ማንሱድ፥ በኡባይ ኢብን ከዓብ እና በአቡ ሙሳ ነበር።

### መ. ከመሐመድ ሞት በኋላ ቁርዓን ተከልሶ ነበር

ከጥቂት ጊዜ በኋላ፥ የተለመደ ነውና ለካሊፍ ዑስማን አንድ ነገር ተነገረው። የደረሰውም ወሬ በሠራዊቱ ውስጥ ያሉ ወታደሮች የተለየ ትርጉም ያሏቸው የቁርዓን ክፍሎች እንደሚደግሙ (እንደሚቀሩ) የሚያስረዳ ነበር። በዚህም ጊዜ የተለያዩ የቁርዓን ዝግጅቶችን በሙሉ እንዲያቀርቡለት አዘዘ። ከነዚያም ውስጥ የተከለሱት (የተሻሻሉት) ተመርጠው ተጠረዙ፤ ሌሎቹ ቀዳሚ ዝግጅቶች (ኦርጅናሎቹ) እንዲቃጠሉ አዘዘ። «የኡስማን መጽሐፍ» እየተባለም እስከ አሁን ድረስ የሚገለገሉበት ክፍሎች አሉ። ጥንታዊ የሥነ መለኮት ጽሑፎችን በመመርመር፥ ይህንን ከዚህ በበለጠ ዝርዝር ሁኔታ ልንረዳ እንችላለን (ሚሽካት 3 ገጽ 708)።

ይህ ሁሉ መሆኑ እየታወቀ ሙስሊሞች በቁርዓን ላይ አንድም ለውጥ እንዳልተደረገና ዛሬ በዐረብኛ ተጽፎ የሚገኘው ቁርዓን ከሰማይ ከተሰጠው ጋር ፍጹም አንድ እንደሆነ ይናገራሉ። እኛ የተሻለ እናውቃለን እንበል ይሆን?

## 4. የእስልምና ባህላዊ ወጎች


እስልምና ከተጀመረ እስከ ጥቂት መቶ ዓመታት ድረስ አዲስ ትእዛዛት፥ ሃይማኖታዊ አወቃቀርና እንዲሁም ቅርጽ ተበጀለት። ቁርዓንንም ለመተርጎም አደጋችነቱ እውን ሆነ። የሃይማኖቱም ሊቆች ቁርዓንን ከተገለጠለት ከዚያ ሰው በስተቀር ማንም በትክክል ሊተረጉመው እንደማይችል አዋጅ አስነገሩ። ያ ባለመብት ደግሞ በሕይወት አልነበረም - ሞቷል።

### ቁርዓንን ለመተርጎም የእስልምና ወጎች ያስፈልጉ ነበር

ስለዚህም በመቶ በሚቆጠሩ ሙስሊሞች ዘንድ ተጠብቀው በኖሩትና በሺህ በሚቆጠሩት ስለ መሐመድ የተነገሩ አፈ ታሪኮች ላይ ፍለጋ ተደረገ። «መሐመድ ምን ምን ተናግሮ ነበር? ... ምን ምን ያደርግ ነበር? ... የፈቀደውና አጥብቆ የከለከለውስ ምን ምን ነበር?» እየተባለ ወጎቹ ተሰባሰቡ።

ከዚህ በመንሣትም ቁርዓን እንዴት እንደሚተረጎም መላ ተፈጠረ። ይህን ሥርዓት ሙስሊሞች «ታፍሲር ማድረግ» ብለው ይጠሩታል። «ታፍሲር» በመሐመድ ንግግርና በተግባሩ ላይ የተመረኮዘ የቁርዓን አፈታት ነው። የመሐመድን ሕይወትና አኗኗሩን ማወቅ ማለት የቁርዓንን ፍች ማወቅ ማለት እንደ ሆነ ያህል ተቆጠረ።

## ወጎቹ እንዴት ተሰበሰቡ?




የተሰበሰቡት ወጎችና ታሪኮች ጥርቅም «ሐዲት» ይባላል። ከመሐመድ ሞት ከ250-300 ዓመታት በኋላ ወጎቹን የማሰባሰቡን ሥራ ትጉህ የሃይማኖቱ ምሁራን በግል ተያያዙት። ከእነርሱም መካከል በይበልጥ ታዋቂ የሆነው አል-ቡካሪ 600000 ያህል ሐዲት ሰብስቧል። በጥንቃቄም መርምሮ ከመረጣቸው በኋላ 7200ዎችን አጸደቀ። ቀሪዎቹ ግን አስተማማኝነታቸው ስለ አልተረጋገጠ ንቆ አለፋቸው። ከተቀበላቸው መካከል ከሌሎቹ ተባዝተው ነበር። ወጎቹን ለማንሣትም ሆነ ለመጣል የአል-ቡካሪ የራሱ ውሳኔ እንጂ፥ የሌሎች ምሁራን ጣልቃ ገብነት አልነበረበትም።

በአሁኑ ጊዜ በእነዚህ ስብስቦች መካከል ስድስቱ «ሲሃሁ ሲታህ» በመባል ተቀባይነትን አግኝተዋል። ትርጓሜውም «ትክክለኛ መጻሕፍት» ማለት ነው።

የሃዲስ ተአማኒነት የተመሠረተው አፈ-ታሪኩን የተናገሩትን ሰዎች የዘር ሐረግ በማረጋገጥ ነው። ሃዲስ የተባለውን መረጃ የያዙ ሰዎች ምን ያህል የሚታመኑ ናቸው? በመጀመሪያ ለእነርሱ የተናገሩት ሰዎች ከመሐመድ ተባባሪዎች የሚመደቡ ነበሩ? በመጨረሻ እስከ ተመዘገቡበት ጊዜ ድረስ እነዚህን አፈ-ታሪኮች ያስተላለፉ ወንዶችና ሴቶች እነማን ነበሩ?

በኋለኛው ዘመን ደግሞ «እውነተኞቹ የነቢዩ መሐመድ ዋና ዋና አባባሎችና ድርጊቶች ስብስብ» በሚል ርዕስ ከሐዲስ ሥነ ጽሑፎች መካከል የበለጠ አስተማማኝ የሆነው ተመርጦ በአል-ባጋዊ ተዘጋጀ። ይህም በአጭር ሲጠራ «ሚሽካት» ሲባል ሙሉ ስሙ ደግሞ «ሚሽካቱል ማሳቢህ» ተብሉ ይጠራል።

## የሐዲት ትምህርት

የሐዲት ስብስቦች ሁሉ የተወሰነ ቅደም ተከተል የተሰጣቸው ሲሆን፥ በርካታ የተለያዩ ዓይነት ትምህርቶችን ይዘዋል። ስለ እምነት፥ እውቀት፥ ጸሎት፥ የመታጠብ ሥርዓት (ዎዱ)፥ የቀብር ሥነ ሥርዓት፥ ምጽዋት፥ ስለ ተቀደሰው ጉዞ፥ ጾም፥ ንግድ፥ ባርነት፥ ኑዛዜ፥ ቅዱስ ጦርነት፥ ስለ መሐመድ መልካም ምግባሮች፥ ጋብቻ፥ ፍቺ፥ ምግብና አመጋገቡ፥ መድኃኒቶች፥ መሥዋዕቶች፥ አለባበስና የኑሮ ዘይቤ፥ ቀድሞውኑ ስለተወሰነ ዕድል፥ መሐላ፥ ወራሽነት፥ ለወንጀልና እስልምናን ለካደ ሰው ስለሚሰጡ ቅጣቶች፥ ሕልሞች፥ ንጽሕና፥ ስለ ዘላለማዊ ፍርድና ስለ ማስነጠስ፥ ማዛጋት፥ የጺምና የፀጉር አቆራረጥ፥ ስለ ሽቶ አጠቃቀም፥ ጥርስንና አፍንጫን ስለማጽዳትና ስለ ሌሎችም ቀላል ጉዳዮች ያትታል።

እነዚህ ሐዲቶች ጠለቅ እና ዘርዘር ያሉ ሲሆኑ፥ ሌሎቹ ግን በመጠኑ ፈገግ የሚያደርጉ ዓይነት ናቸው። ለምሳሌ ይህን አባባል አብረን እንታዘብ፡-

> «የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብሎአል፤ ከአንዳችም ምግብ ላይ ዝምብ ብታርፍ፥ እንዲያውም በደንብ አጥልቃት (ንከራት)፤ ምክንያቱም በክንፎችዋ በአንዱ በሽታና በሌላው ፈውስ ስላለበት ነው። መጀመሪያ የምታሳርፈው በሽታ ያለበትን ክንፍ ነውና ሙሉ በሙሉ ንከራት» (ሚሽካት 2 ገጽ 152)።

> «የአላህ መልእክተኛ (ሰላም በእርሱ ላይ ይውረድና) ‹አማኝ በአንድ አንጀት ሲበላ የማያምን ግን በሰባት አንጀት ይበላል ብሎአል› ብሎ ኢብን ኡማር ተናገረ» (ሶሂህ እስልማ 3 ገጽ 1137)።

> «ጃቢር እንደሚለው ያ የአላህ መልእክተኛ (ሰላም በእርሱ ላይ ይውረድና) ጣትና ወጪት ስለ መላስ የአዘዘው ነገር ይህ ነው፤

‹ከእናንተ ማንኛውም ሰው ምግብ በሚበላበት ጊዜ ጣቱን ራሱ ሳይልስ ወይንም ሌላው እንዲልስለት ሳያደርግ እንዳይጠርግ› ብሎአል» (ሚሽካት 3 ገጽ 1119-1120)።

አብዛኛዎቹ ሙስሊሞች ገና በሕፃንነታቸው መሐመድ የአደረገውን ሁሉ ስለ መለማመድና ስለ ሐዲት ብዙ ትምህርት ይሰጣቸዋል። ምክንያቱም የእስልምናው ነቢይ እንከን የማይወጣለትና ፍጹም ከሆነ፥ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት ቀናውና አቋራጩ መንገድ እርሱ እንዳደረገው ማድረግ ነው። ውጤቱ ግን እስልምናን ውጫዊ ሃይማኖት ያደርገዋል። ምክንያቱም ታማኝ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ በሚያመሰግን ልብ ከመኖር ይልቅ ክብደት የሚሰጠው በድርጊቶች ላይ ስለ ሆነ ነው።

> ሙስሊሞች የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓታቸውን ይፈጽማሉ። ክርስቲያኖች ግን ትክክለኛውን ነገር የሚያደርጉት ክርስቶስ ዕዳቸውን ስለ ከፈለላቸው ባለ ውለታ ስለ ሆኑ ነው።

## ሱና - የመሐመድ የአኗኗር ስልት

መሐመድ አንድ ጊዜ ይህን ተናግሮ ነበር፡-


«ሁለት ነገሮችን ትቼላችሁ እሄዳለሁ! እነዚህንም ሁለት ነገሮች አጥብቃችሁ እስከ ያዛችሁ ድረስ አትታለሉም። እነርሱም የአላህ መጽሐፍና የመልእክተኛው ሱና ናቸው» (ሚሽካት 1 ገጽ 159)።

«የአላህ መጽሐፍ» የሚለው ያለጥርጥር ቁርዓንን ነው። «ሱና» ማለት ግን መሐመድ ያደረገውን፥ የተናገረውን፥ የከለከለውን፥ ወይንም የፈቀደውን ነገር መለማመድ (መቅዳት) ማለት ነው። በሌላ አነጋገር እርሱ የኑሮ ሥርዓት ምሳሌአቸው (ሞዴላቸው) ነውና ሙስሊሞች ሁሉ የአኗኗር ስልቱን ለመከተልና በተቻለ መጠን እርሱን ለመምሰል ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል።

ማስታወሻ! በተጨማሪ መግለጫው ላይ ያሉትን የምዕራፍ 3 ና 4 የጥናት ጥያቄዎች አሁኑኑ እንድትሠራቸው እናስታውሳለን። (ይህንንም ከመጽሐፉ በስተ-ጀርባ ላይ ታገኘዋለህ።)

# 5. የእስልምና እምነትና ምግባሩ


የእስልምናን እምነት መሠረታዊ አሳብ በአምስት ዋና ዋና ነጥቦች ማጠቃለል ይቻላል። ሙስሊሞች በሚከተሉት ነጥቦች ያምናሉ:-




1. በአንድ አምላክ - አላህ (የአላህ አንድነት «ታው-ሂድ» የተባለውን በጣም ያጠብቃሉ)።
2. በመላእክት መኖር ያምናሉ።
3. በተገለጹት «መጻሕፍት» ሁሉ። እነርሱም-
   * ታውራት (አምስቱን የሙሴ መጻሕፍት ምናልባትም ብሉይ ኪዳንን በሙሉ)።
   * ዛቡር (የዳዊት መዝሙር)።
   * ኢንጂል (ወንጌል ወይም አዲስ ኪዳን)።
   * ቁርዓን።
4. በእግዚአብሔር በተላኩ ነቢያት ሁሉ። ሙስሊሞች 124000 ነቢያት ወደ ሁሉም ሕዝቦች እንደ ተላኩ ያምናሉ። ጥቂቶቹንም ብቻ በስማቸው ይጠቅሱአቸዋል። ከእነርሱም መሀል:- አዳም፥ ኖኅ፥ አብርሃም፥ ይስሐቅ፥ ያዕቆብ፥ ዮሴፍ፥ ሙሴ፥ ዳዊት፥ ኢየሱስና መሐመድ ይገኙባቸዋል።
5. ከሞት በኋላ ሕይወት እንዳለና አስቀድሞ በተወሰነ ዕጣ ፈንታ፥ ሙስሊሙ መንግሥተ ሰማይ ወይንም ገሃነመ እሳት እንደሚገባ የሚወሰንበት የፍርድ ቀን ስለ መኖሩ ያምናሉ። (ዘርዘር ባለ ሁኔታ በኋላ እንመለከተዋለን።)

የእስልምና ምግባርን ሙስሊሞች «የእስልምና ዓምድ (ምሰሶ)» ይሉታል። እነዚህም የዘወትር ተግባራት ቀጥሎ ያሉት ናቸው:-

1. እምነትን በይፋ መግለጽ (ማረጋገጥ) ወይም «ሸሃደ»
2. ዕለታዊው ሰላት - በቀን አምስት ጊዜ የሚፈጸም
3. በረመዳን ወር የሚደረገው የአንድ ወር ጾም። ሙስሊሞች ከፀሐይ መጥለቂያ እስከ መውጫ እንዲመገቡ ተፈቅዶላቸዋል።
4. ምጽዋት መስጠት ወይንም ዘካት ማውጣት




5. አቅሙ የፈቀደለት ከሆነ ቢያንስ በሕይወት ዘመኑ አንድ ጊዜ ቅዱስ ጉዞ ወደ መካ ማድረግ (ሐጂ-ዑምራ ጉዞ)።

# 6. የእስልምና ግንዛቤ

## አላህ

ሙስሊሞች አላህን በፍጹም ፍርሃት ይታዘዛሉ፤ አስደናቂ ክብርም ይሰጣሉ። በሙስሊሞች ግንዛቤ አላህ «ታውሂድ» ነው፤ ማለትም በገዛ ራሱ ውጉድ የሆነ ፍጹም አንድ አምላክ ነው በማለት ነው። ይህ እንግዲህ በዚያን ጊዜ በዐረቡ ዓለም የነበሩ አረመኔዎች የሚያመልኳቸውን ጣዖታት የሚቃወም ሲሆን፥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮታዊነትም ደግሞ ይቃረናል (ከገጽ 44-52 ተመልከቱ)።

አላህ ምንም አምሳያና የሚተካከለውም የሌለው ነው። እርሱም እጅግ ሩቅና በባሕርዩ፥ በፈቃዱ፥ በኃይሉና በእውቀቱ ፍጹም ነው። እርሱ የመልካምና የክፉ ነገሮች ሁሉ ፈጣሪ ነው። ምንም ነገር ከቶ ያለፈቃዱ አይሆንም። ይህም ኃጢአትን ጨምሮ ነው። ምንም እንኳን የሰው ልጅ

ባይገባውና አጕረምራሚ ቢሆንም፥ አላህ ግን በሥራው ሁሉ ቅን ፈራጅ ነው። አላህ ለመልካም ቢሆን ለክፋት፥ ለማልማት ቢሆን ለማጥፋት፥ ሥራው ከሰው ልጆች አእምሮ በላይ ነው። እርሱም ብቻ ሊመለክና ሊታዘዙለት የሚገባ ነው።

በቁርዓን አላህ «አል-ረኽማን» እና «አል-ረሂም» ተብሎ ይታወቃል። ትርጓሜውም እጅግ ሩኅሩኅና መሐሪ ማለት ነው። በእርግጥ ቁርዓንን ዘልቀን በተመራመርን መጠን አላህ ይህን ባህርዩን ሲቃረን እናገኘዋለን። በቁርዓን ውስጥ ለአላህ በጠቅላላው 99 ውብ ስሞች (መጠሪያዎች) ተሰጥተውታል። እነዚህን ስሞች በጸሎት መልክ መደጋገም እንደ ጽድቅ ይቆጠራል።



ለዚህ የተዘጋጀውን መቁጠሪያ (የአገራችን ሙስሊሞች ሙስባሃ ይሉታል) በክር በተያያዙ 99 ድብልብል ነገሮችና አንዱ በውኃ ጠብታ ቅርጽ የተሠራ ሲሆን ሙስሊሙ ሲጸልይ አንዷን በጣቱ በሳበ ቁጥር አንዷን የአላህ ውብ ስም ይጠራል። ያ በውኃ ጠብታ ቅርጽ የተሠራ አላህን ያመለክታል።

ለአላህ እኩያ (ሽርካ) ማበጀት (እንደ እግዚአብሔር ወልድ ያለ) ይቅር የማይባል ኃጢአት ነው። ለአላህ ሽርካ ለማበጀት የሚሞክረውም ሰው በቁርዓን አጠራር «ሙሽርክ» ተብሎ ይጠራል።

የአላህ ባሕርይ የበለጠ የሚገለጠው «ቀድሞ ስለ ተወሰነ ዕጣ ፈንታ» በሚያትተው የእስልምና የእምነት አቋም ውስጥ ነው።

## ቀድሞ ስለ ተወሰነ ዕጣ ፈንታ

«ቀደም ብሎ ስለ ተወሰነ ዕጣ ፈንታ» ጽንሰ-ሀሳብ ማወቅ ለሙስሊሞች እንቆቅልሽ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ ስለ ተወሰነ ዕድል ወይም ስለ መመረጥ ሲናገር «ጭፍን-እምነት» ማለቱ ሳይሆን፥ ነገር ሁሉ የሚፈጸመው እግዚአብሔር አስቀድሞ አውቆት እንደ ሆነ ለማመልከት ነው። «እግዚአብሔር አስቀድሞ እንደ አወቃቸው . . .» (1ኛ ጴጥ. 1፡2፤ ሮሜ 8፡29)። እግዚአብሔር ንስሐ እንደምንገባና ደኅንነትን ፈልገን ወደ እርሱ እንደምንመለስ ስለሚያውቅ፥

ይመርጠናል፤ የልጁንም ምሳሌ እንድንመስል አስቀድሞ ያቅዳል። የእስልምናው አመለካከት ግን ፈጽሞ ከዚህ የተለየ ነው። ሁሉም ነገር በአላህ የበላይነትና ተቆጣጣሪነት የሚፈጸም መሆኑን ያስገነዝባልና፤ ደግሞም የአላህ ፈቃድ ሊለዋወጥ እንደሚችል ያስገነዝባል።

«አላህ ለኛ የጻፈልን (ጥቅም) እንጂ ሌላ አይነካንም» (ሱረቱ 9፡51)።

አላህ ከወደደንና ለእኛ የሚበጀውን ሁሉ ቢያደርግልን ይህ መልካም በሆነ ነበር። ነገር ግን ሁኔታው ይህን አይመስልም፡-

«ይህቺ መገሠጫ ናት፤ የሻም ሰው ወደ ጌታው መንገድን ይይዛል። አላህም ካልሻ በስተቀር አትሹም፤ አላህ አዋቂ ጥበበኛ ነውና» (ሱረቱ 76፡29-30)።

አዳዲሶቹ የቁርዓን ትርጉሞች ይህንን እውነት ለመሸፋፈን ይሞክራሉ። የጥንት ዝግጅቶች ግን በግልጽ የሚከተለውን ይናገራሉ፡-

በቁርዓን ውስጥ እርሱ ከፈቀደ (ከሻ)፥ የፈቀደውን (የሻውን)፥ እንደ ፈቀደው (እንደ ሻው) የሚሉት ቃል ምን ጊዜም የትም ቦታ ይጠቅሳሉ።

«አላህም የሚሻውን ያጠማል፤ የሚሻውንም ያቀናል» (ሱረቱ 14፡4)። (በተጨማሪ ሱረቱ 5፡20፤ 4፡88፤ 32፡13 ተመልከት።)

ስለማያምኑት ደግሞ ቁርዓን እንዲህ ይላል፡-

«አላህ በልቦቻቸው ላይ፥ በመስሚያቸውም ላይ አትሞባቸዋል፤ በዓይኖቻቸውም ላይ መሸፈኛ አለ፤ ለነሱም ታላቅ ቅጣት አላቸው» (ሱረቱ 2፡7)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ግን የማያምኑትን ሰዎች ልብ እግዚአብሔር እንደሚያሳውር አይናገርም፤ የዚህ ዓለም አምላክ (ዲያብሎስ) የማያምኑትን ልብ እንደ አሳወረ እንጂ (2ኛ ቆሮ. 4፡4)።

«አስቀድሞ ስለ ተወሰነ ዕጣ ፈንታ» በቁርዓን ውስጥ ከምናነባቸው እጅግ አስደንጋጭ ምንባቦች አንዱ እንዲህ ይላል፡-

«አላህም በሻ ኖሮ አንዲት ሕዝብ ባደረጋችሁ ነበር፤ ግን የሚሻውን ሰው ያጠማል፥ የሚሻውንም ሰው ያቀናል፤ ትሠሩት ከነበራችሁም ሁሉ በእርግጥ ትጠየቃላችሁ» (ሱረቱ 16፡93)።

ወደ ሕዝቦች ተልከው ስለ ነበሩት ነቢያት ደግሞ ቁርዓን እንዲህ ይላል:- «. . . ከነሱም ውስጥ አላህ ያቀናው ሰው አለ፤ ከነሱም ውስጥ በርሱ ላይ ጥመትም የተረጋገጠበት ሰው አለ» (ሱረቱ 16:36)።

ዘመናዊዎቹ የቁርዓን ትርጉሞች ይህን ዓይነት አባባል ለማስወገድ ሞክረዋል።

መሐመድ ይህን የእምነት አቋም በምን ሁኔታ ይተረጉመው ይሆን? እስቲ ሐዲስን እንመልከት:-

> «ቅዱሱስ ነቢይ እንዲህ ይላል:- አላህ አዳምን ፈጠረ፤ ከዚያም ቀኝ ትከሻውን ዳሰሰና ልክ እንደ እህል ዘር ነጭ የሰው ዘርን አወጣ፤ ከዚያም ግራ ትከሻውን ዳሰሰና ልክ እንደ ከሰል ጥቁር የሰው ዘር አወጣ፤ ቀጥሎም በቀኙ ያሉትን እነዚያን:- እናንተ ወደ መንግሥተ ሰማይ ናችሁ! ምን አሻኝ . . . በግራ ትከሻ ያሉትን ደግሞ:- እናንተ ወደ ገሃነም ናችሁ! ምን አሻኝና! አላቸው» (ሚሽካት 3 ገጽ 117)።

መሐመድ ሌላም ማንኛውንም ሙስሊም የሚያስጨንቅ ነገር ተናግሯል። የተናገረውም አንድ ሙስሊም ወዳጁ ለጠየቀው ጥያቄ መልስ ሲሰጥ ነበር:-

> «የአላህ ነቢይ ሆይ! እኔ በአንተና አንተ ባመጣኸው አምናለሁ። (በአላህና በቁርዓን ማለቱ ነው) አሁንም ስለ እኛ ትሠጋለህን?»

መሐመድም ሲመልስ እንዲህ አለ:-

> «አዎን! የሰው ልጆች ልቦች በአላህ በሁለት ጣቶች መካከል ናቸው። እርሱም እንደ ፈለገ ይለውጣቸዋል» (ሚሽካት 3 ገጽ 111)።

እንዲህ ያለው አስተሳሰብ መሐመድን ስለ ዘላለማዊ ተስፋው እንዲጠራጠር አድርጎታል:-

> «በእውነቱ ግርማ ያለው ኃያል አላህ አንዱን በቀኝ እጁ ሌላውን በግራ እጁ ይዞ:- ይህ ለዚህ ነው፤ ይህም ለዚህ ነው፤ እኔን አይገደኝም ይላል። እኔም በየትኛው እጁ ውስጥ እንዳለሁ አላውቅም» (ሚሽካት 3 ገጽ 118)።

ከላይ የተነበበው ጥቅስ ምናልባት በጣም ግልጽ አይደለም ይሆናል። ነገር ግን ማንኛውም ተራ ሙስሊም ቀርቶ የአላህ ነቢይ እንኳን ራሱ

አላህ ስለ እርሱ ያለው ዓላማ ምን እንደ ሆነ አያውቅም። ሌላም ነጥብ አለ፤ አላህ የማያመልጡትን (መድኃኒት የሌለውን) የኃጢአት ድንጋጌ በውስጣቸው አድርጎ ይሆናል፡-

«የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አለ፡- በእውነት አላህ ለአዳም ልጆች (ለሰው ልጆች) አመንዝራነትን አስቀድሞ ወስኖባቸዋል። ይህም ያለ ጥርጥር ያሸንፋቸዋል» (ሚሽካት 3 ገጽ 103)።

አባባሉ በሌላ ሐዲስ ጥቅስ ይደገፋል፡-

«በእውነት ሰው ሊያመልጠው የማይችለው የዝሙት ክፍል አላህ አጣብቆበታል» (ሳሂህ ሙስሊም 4 ገጽ 1396)። ይህ ሁሉ እንግዲህ፡- ሰው ቀኝና ግራውን፥ መልካሙን ከመጥፎ ለመለየት ነጻ ፈቃድ የለውም ከሚል የተሳሳተ መሠረተ-እምነት የመነጨ ነው።

ከጀመርነው ርዕስ ጋር የሚስማማ አንድ የእስልምና ታሪክ አለ። እንዲህ ይላል፡-

«በአዳምና በሙሴ መካከል አንድ ጊዜ ውይይት ተደርጎ ነበርና ሙሴ አዳምን እንዲህ አለው፡- አንተ አባታችን ነህ፤ እኛን ግን ጎድተኸናል። ከገነት እንድንወጣም ምክንያት ሆነህብናል። አዳምም ሙሴን፡- ‹አንተ ሙሴ ነህ። አላህ አንተን መረጠና በገዛ እጁ መጽሐፉን ለአንተ ጻፈ። ይህም ሆኖ አላህ እኔን ከመፍጠሩ ከ40 ዓመታት በፊት እንዳደርገው በወሰነብን ነገር ትወቅሰኛለህ› አለ» (ሳሂህ ሙስሊም 4 ገጽ 1307)።

ይህንን ርዕስ በሌላ አንድ ጥቅስ ለማጠቃለል እንሞክር፡-

«ቅዱሱ ነቢይ እንዲህ አለ፡- ከአለበት ቦታ ራሱን ወደ ሌላ ስፍራ ስለ አነቃነቀው ተራራ ብትሰማ ነገሩን እመን። ነገር ግን የገዛ ተፈጥሮውን ስለ ለወጠ ሰው በሰማህ ጊዜ አትመን። መጀመሪያ ወደ ተነሣበት አፈጣጠሩ ይመለሳልና» (ሚሽካት 3 ገጽ 121)።

መጽሐፍ ቅዱስ ግን የዚህ ዓይነት አመለካከት የለውም። ይልቁንም «ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል» ይላል እንጂ (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17)።

«አስቀድሞ ስለ ተወሰነ ዕጣ ፈንታ» የሚያትተውን ይህን የተዛባ የእስልምና ዶክትሪን ስንመለከት ስለ ትምህርቱ አብዛኛዎቹ

ሙስሊሞች እንደማያውቁ መገንዘብ አለብን። ቢያውቁም እምነታቸው ገና ሕልም ዓይነት ነው። ለምሳሌ «አንበሳ ሥጋ እንደሚበላ ቀድሞ የተወሰነ ነው። የሜዳ አህያም ደግሞ ሣር ወይም ቅጠል እንዲበላ ተወስኖአል። ስለ ሆነም አላህ ሁሉም ፍጡር በአንድ ወይም በሌላ ነገር እንዲለይና እንዲወሰን ሥርዓትን አበጅቷል» ሊሉህም ይችላሉ። ይህ አመለካከት ለእኛ ምንም እንኳን የወንጌል በር መክፈቻ ቁልፍ ሆኖ ቢያገለግለንም አባባሉ ግን ለመቀበል የማይቻል ነው። ሙስሊሞችን በደንብ ስናውቃቸውና ሰው «ነጻ ፈቃድ» እንዳለው ወይንም እንደ ሌለው ብንጠይቃቸው «አዎን» በማለት ማረጋገጣቸውን ይሰጡን ይሆናል። ያን ጊዜም «ታዲያ ሙስሊም እንደ መሆንህ መጠን በእስልምና የሥነ-መለኮት ትምህርት ዘንድ የታወቁትን የ‹ታቅዲር› እና የ‹ቋዛ› ዶክትሪኖች እንዴት ልትቀበላቸው ቻልህ?» በማለት ስለ እነዚህ ትምህርቶች የአጠናኸውን ሁሉ ታካፍለዋለህ። ከዚህም በመነሣትም መጽሐፍ ቅዱስ በአንጻሩ ምን እንደሚል ስታስረዳቸው ሙስሊሞች ይረበሹ ይሆናል። ይሁን እንጂ አቋማቸውን መልሰው መላልሰው እንዲመረምሩ ያደርጋቸዋል። ምክንያቱም «አላህ የሚያደርገውን ቀደም ብሎ ለማወቅ ሳይቻለኝ፥ እርሱ ሁሉን ነገር እንደ ወደደ ስለሚያደርግ፥ ምናልባት ስለ ሲዖል ቢሆን . . .? ይኸንን ፍርድ አመልጥስ ዘንድ የእኔ አቅም እስከምን ድረስ ነው?» የማይል ማንም የለምና።

## ፍርድ በእስልምና እምነት

ይሁዲዎች፥ ሙስሊሞች፥ ክርስቲያኖች፥ ሁሉም ሊመጣ ያለውን የመጨረሻ የፍርድ ቀን ያምናሉ። ስለዚህም ይህ ርዕስ ለሙስሊሞች ለመመስከር ጥሩ የውይይት መነሻ ይሆንሃል። በዚህ ጉዳይ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል እርግጠኞች እንሁን። መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአት በማንኛውም ደረጃ ቢሆን (የኃጢአት ትንሽ የለውምና) ከእግዚአብሔር ይለየናል፤ ወደ ዘላለም ሞትም ይነዳናል። «ለምን?» ያልን እንደሆነ፥ ኃጢአት ከመሠረቱ በእግዚአብሔር፥ በፈቃዱ፥ በሕጉና በትዕዛዛቱ ላይ ማመፅ ስለ ሆነ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የምንታረቅበትን መንገድ አዘጋጅቶልናል። ምክንያቱም መልካምን በማድረግ የኃጢአትን ዋጋ መክፈል ስለማይቻል ነው። ምንም ቢሆን በጎ ሥራ ሁሉ ከእኛ ይጠበቅብናል። ኃጢአት ከቅዱስ አምላክ ባሕርይ

ጋር ፍጹም ተቃራኒ በመሆኑ፥ በችሎታ ሊያልፈው አይችልም፤ የሚያደርገውን መወሰን ግዴታው ነው። ኃጢአት የተጣበቀበት ሰው በእግዚአብሔር ማደሪያ መገኘት ከቶም አይቻለውም። መንግሥተ ሰማይ ይኸው ነው፤ ለዘለዓለም በእግዚአብሔር ዘንድ መኖር ነው።

ስለዚህም የኃጢአት ዕዳ በሞት ይከፈል ዘንድ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን ኃጢአትን በመሥዋዕቱ ላይ እጅ በመጫን ወይንም በማስተላለፍ ምሳሌነት ለዚህ የተዘጋጀው እንስሳ እንዲታረድ ይደረግ ነበር። መጥምቁ ዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ (ዮርዳኖስ የሞት ምሳሌ ነበር።) ሲያጠምቅ በነበረ ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» (ዮሐንስ 1፡29) በማለት ጮኸ።

እዚህ ላይ «ኃጢአት» እንጂ «ኃጢአቶች» አለማለቱን ልብ በል! ብዙ ልዩ ልዩ ኃጢአቶች መሥራት ማለት የእግዚአብሔርን ፈቃድና ሕግ ማፍረሳችን ነው። «ኃጢአት» ግን ሰይጣን ሰውን ሁሉ የሚገዛበት መንገድ ነው። ይህን የሰውን ሁሉ ኃጢአት ተሸክሞ የተሠዋው የእግዚአብሔር በግ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ስለዚህም ማንኛውም ኃጢአተኛ ቢሆን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ለመቀበል እና የሕይወቱ ጌታ አድርጎ ለማንገሥ ፈቃደኛ መሆን አለበት።

ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝና ጌታ አለመቀበል ደግሞ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከውን የኃጢአትን ይቅርታ አለመቀበል ነው። የክርስቶስን የማዳኑን ሥራ አለመቀበል ማለት በሌላ አነጋገር «በራሴ ብቁ ነኝ፤ ... መንግሥተ ሰማይን በጥረቴ ልወርሳት የተገባኝ ነኝ ፤ ... አንተ አታስፈልገኝም፤ ያለ አንተም ቢሆን ሕይወት ለእኔ የሰመረች ነች» ማለት ነው።

ባለማወቅም ሆነ አውቀው በእልከኝነት እግዚአብሔር ለኃጢአት ይቅርታ የአዘጋጀውን መንገድ የማይጠቀሙበት ሁሉ እግዚአብሔር በመጨረሻው ቀን የአዘጋጀውን ፍርድ እየተጠባበቁ ናቸው። በዚያን ጊዜ ሙታንና ሕያዋን እንደየሥራቸው ይከፈላቸዋል (ራእይ 20፡11-15)።

እነዚያም በሕይወት መጽሐፍ ተጽፈው የተገኙት ብቻ ከገሃነመ እሳት ፍርድ ይድናሉ። (ገሃነመ እሳት ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር ተለይተው የሚኖሩበት ሥፍራ ነው።) አንድ ሰው በመስቀል ላይ የተፈጸመው የክርስቶስ መሥዋዕትነት ለኃጢአቱ እንደ ተደረገ አምኖ፥ ኃጢአቱን ለመተውና ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል በእውነተኛ ልቡ የእግዚአብሔርን ይቅርታ በሚፈልግበት ቅጽበት ደኅንነትን አግኝቶ በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ «ተጽፎአል»።

እርግጥ ነው የሰው ልጅ ኃጢአት-አልባ ሆኖ አይኖርም። «ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም» (1ኛ ዮሐ. 1፡8)። ብርቱ አማኝ እንኳ ኃጢአት ሳይሠራ አይኖርም። ኩራት፥ ስስት፥ ቅንዓት፥ ወዘተ የመሳሰሉት ሁሉ በወጥመዳቸው ይይዙታል። ሆኖም በእግዚአብሔር ጸጋ ንጹህ ሆነን መኖር እንችላለን። «በኃጢአታችን ብንናዘዝ፥ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው» (1ኛ ዮሐንስ 1፡9)።

እንግዲህ እስልምና ስለ ፍርድ ያለው መረዳት ከዚህ የተለየ ነው። አንድ ሙስሊም ስለ ማንኛውም የሕይወት አቅጣጫ የተሰጡትን በሺህ የሚቆጠሩትን ሕግጋት ቃል በቃል መፈጸም አለበት። ብዙውን ጊዜ ሕግን መተላለፉ ግልጽ ነው። አያሌ ሙስሊሞች ቅኖችና ሕግጋቱን ለመጠበቅ በጣም የሚጥሩ ናቸው። እንዲያም ቢሆን ከወጥመዱ አያመልጡም።

> አዎ! ሙስሊሞች አንድ ግዙፍ ችግር አለባቸው። ይኸውም ስለ ኃጢአት የሚሰጡት የተሳሳተ ግንዛቤ ነው።

ለእነርሱ ከኃጢአት ሁሉ ይልቅ የከፋ ኃጢአት ለአላህ «ሽርካ» ወይንም «ደባል» ማበጀት ነው። እኛ ክርስቲያኖች እንኳን ኢየሱስን እንደ እግዚአብሔር ወልድ ማምለካችን በእነርሱ ዓይን ደባል አማልክ ፈጠርን ማለት ነው። ይህ በሙስሊሞች ዘንድ ክህደት ነው።

በተረፈ እስልምና ኃጢአቶችን ቀላልና ከባድ ብሎ ደረጃ ያወጣላቸዋል። ዓይነታቸውንም ይዘረዝራቸዋል። አንዳንዶቹ ከቁጥርም ላይገቡ ይችላሉ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ በሳ ነገር በመሥራት ይጸዳሉ፤

ለሌሎቹም ይቅርታ መጠየቅ ያስፈልጋል፤ ከበድ ላሉት ደግሞ ንስሐ መግባት እንኳ አስፈላጊ ነው።

ስለ ኃጢአት ከባድነት መረዳቱ የላቸውም። አንድ ሙስሊም የሚከተለውን ዓይነት ንግግር እንዲናገር አይጠበቅበትም፡-

«እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ። የማደርገውን አላውቅምና፤ የምጠላውን ያን አደርጋለሁና፤ ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም፤ ... በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፤ ... የማልወደውን ክፉ ነገር አደርጋለሁና፤ ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደረገውም። የማልወደውን የማደርግ ከሆንሁ ግን ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም በእኔ የሚኖር ኃጢአት ነው እንጂ» (ሮሜ 7፡14-20)።

ከላይ የተነበበውን አባባል የተናገረው አንድ ከእምነቱ እያፈገፈገ ያለ ደካማ ክርስቲያን አይደለም፤ ነገር ግን ኃጢአትንና የሚያስከትለውን መዘዝ የሚያውቅ ሰው እንጂ። ደግነቱ ጌታውንም በደንብ የሚያውቅ ሰው ነው። ተናጋሪው የእግዚአብሔርን ቅድስናና ንጽሕና ባወቀ መጠን ነው የራሱን ጉድለት ሊያይ የቻለው። ይህ ሰው ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት ሃይማኖቱን በጥብቅ ይከታተል የነበረው ጳውሎስ ሲሆን፥ በተጨማሪም ሲጽፍ

«ስለ ሕግ ብትጠይቁ ፈሪሳዊ ነበርሁ፤ ... በሕግ ስለሚገኝ ጽድቅ ብትጠይቁ ያለ ነቀፋ ነበርሁ» (ፊልጵስዩስ 3፡5-6) ይለናል።

---

**የእግዚአብሔርን ቅድስና ስንገነዘብ የኃጢአት ከባድነትና አስቀያሚነት፥ የእኛም ኃጢአተኛነት የበለጠ ይታየናል።**

---

በመሠረቱ ሙስሊሞች ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ሰው፥ ስለ ኃጢአትና ስለ እርቅ (ገጽ- 60 ይመልከቱ) ያላቸው ግንዛቤ የተሳሳተ ነው። በተለይም ደግሞ የኃጢአትን ከባድነት ያሳንሱታል። ስለዚህ ስለ ሰውም ያላቸው ግንዛቤ የተሳሳተ ነው። ሰው ኃጢአቱን በመልካም ሥራው ሊያካክስና እግዚአብሔርን ሊያስደስት እንደሚችል ያስባሉ። ሌላ ስሕተት! ይህን ያሰኛቸው ስለ እግዚአብሔር ያላቸው የተሳሳተ መረዳት ነው። እግዚአብሔር የኃጢአትን ዋጋ ሳያስከፍልና ሳያስወግድ

ዝም ብሎ ይቅርታን የሚያፈስ ይመስላቸዋል። ከኃጢአት ጋር መኖር የቅድስናው ባሕርይ እንዳልሆነ አልተረዱም።

የምሥራቹን ቃል በተለመደው መንገድ ከአንድ ሙስሊም ጋር ለመካፈል ብንሞክር ምላሹ ሊሆን የሚችለው እንዲህ ነው:- «እኔ ኃጢአተኛ አይደለሁም፤ እንዲያው እናንተ ክርስቲያኖች ሁልጊዜ ሰው ማስጨነቅና ከጭንቀታቸውም የተበላሸ ሕሊና መማረክ ትፈልጋላችሁ፤ አላህ ግን እጅግ መሐሪ፥ ቸርና ይቅር ባይ ነው። በተጨማሪም ሙስሊም እንደ መሆኔ በቀን አምስት ጊዜ እጸልያለሁ፤ በረመዳን ጊዜ እጾማለሁ፤ እመጸውታለሁ . . .»

አንድ ምሳሌ ትዝ አለኝ:-

> «ሁለት ሰዎች ሊጸልዩ ወደ መቅደስ ወጡ፥ አንዱ ፈሪሳዊ ሁለተኛውም ቀራጭ። ፈሪሳዊው ቆሞ በልቡ ይህን ሲጸልይ:- እግዚአብሔር ሆይ፥ እንደ ሌላ ሰው ሁሉ ቀማኞችና ዓመፀኞች፥ አመንዝሮችም፥ ወይም እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንሁ አመሰግንሃለሁ፤ በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጾማለሁ፤ ከማገኘው ሁሉ አሥራት አወጣለሁ አለ። ቀራጩ ግን በሩቅ ቆሞ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ሊያነሣ እንኳ አልወደደም፤ ነገር ግን:- አምላክ ሆይ፥ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ እያለ ደረቱን ይደቃ ነበር» (ሉቃስ 18:10-14)።

ክርስቶስም ፍርዱን በማያወላውሉ ቃላት ሰጠ - ወዲያውኑ፤ «እላችኋለሁ፤ ከዚያ ፈሪሳዊ ይልቅ ይህ ቀራጩ ጻድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ።»

ልዩነቱ እንግዲህ ፈሪሳዊው በሚያደርገው፥ ባደረገውም ነገር ሲተማመን፥ ኃጢአተኛው (ቀራጩ) ግን በእግዚአብሔርና በጸጋው ላይ ፍጹም መደገፉ ነበር። ፈሪሳዊው ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ራሱና ስለ ኃጢአት ያለው ግንዛቤ የተሳሳተ ነበር።

የቆምንበትን መሠረት ከአየን እስቲ ደግሞ አንድ ሙስሊም ስለ ፍርድና ስለ ዘላለም ሕይወት ያለውን ግምት እንመልከት።

## ከሞት በኋላ ሕይወት በእስልምና

እንደ እስልምና ግንዛቤ ከሆነ ሰው ከሞተ በኋላ ከሁሉም በፊት «የመቃብር ቅጣት» ይከተለዋል። በሚሞትበት ሰዓት

> «ዓይኖች ይወጣሉ፤ የደም ሥሮች ተመዝዘው ይወጣሉ፤ የጀርባ አጥንት ይሰባበራል፤ ተከለ-ሰውነት ምንም ዓይነት የሰው ቋንቋ ሊገልጸው በማይችል ሁኔታ ይሠቃያል። በአንድ ብልት ላይ ቁስል ካለ መላው አካል በሕመም ይመታል። እስቲ አስበው - እያንዳንዱ የሰውነት ብልት በሙሉ ተራ በተራ ሲንቃቀል የሚሆነውን! ሰው ከአንዱ ደረጃ ወደ ሌላው፥ ከሥጋዊ ሕይወት ወደ መንፈሳዊ ሕይወት የመለወጫው ሰዓት ይህች ናት» (ሚሽካት 4 ገጽ 83)።

በሌላ ስፍራም የሚከተለውን እናነባለን፡-

> «አማኝ ሲሞት በእያንዳንዱ የደም ሥሩ ሕመም ይሰማዋል። በሞት ጊዜ፡- የአላህ ጠላት የሆነው ሰይጣን በጣዕር ላይ ወዳለው ሰው በጣም ይቀርበዋልና» (አህመድ ሰኢድ ደህለዊ- «ከሞት በኋላ ምን አለ?» ገጽ 55 ሃዲስን በመጥቀስ)።

በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ በመቃብር ውስጥ ስላለው ሥቃይ ሌላም የምናነበው አለ፡-

> «በመጀመሪያ፡- የአስከሬኑ ደረት እንዲሰባበርና አጥንቶቹ አንዱ በሌላው ውስጥ እንዲጠራመሱ መቃብሩ ኩምትርትር ይላል። ሁለተኛ እሳት በመቃብሩ ውስጥ ይቀጣጠላል። ሦስተኛ እባብ አሽንር እንዲገዛው ይላክበታል። እባቡ የእሳት ኳሶች የመሳሰሉ ዓይኖች አሉት። ... እባቡም እንዲህ ይለዋል፡- ‹የማለዳ ጸሎትህን ስለ አቋረጥህ ፀሐይ እስከምትወጣ (ማለዳ) ድረስ ልነድፍህ ከጌታዬ ተሹሚአለሁ፤ ... እስከ ቀትርም ደግሞ የእኩለ ቀን ጸሎትህን ስላቋረጥህ እነድፍሃለሁ ... ወዘተ› በዚህ ዓይነት ሁኔታ እስከ ፍርድ ቀን ድረስ መሠቃየቱን ይቀጥላል።»

ይህ እንግዲህ ጸሎቶቹን ላቋረጠው ሰው የሚሰጥ ቅጣት ነው። ለመሆኑ ጸሎቱን ያላቋረጠ ይገኝ ይሆን? ሙስሊም እንደ ሥነ ሥርዓቱ በቀን አምስት ጊዜ በተወሰነው ሰዓት ጸሎት ማድረግ አለበት።


«ከሞት በኋላ ምን አለ?» በተባለው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የመቃብር ውስጥ ቅጣቶች ዓይነተኛ መንስዔዎችን እናነባለን!!

* ሽንት በመሽናት ጊዜ ግድየለሽ መሆን።
* የታዘዙትን ጸሎቶች ማቃለል፣ ከባድ ሸክም እንደማራገፍ ማየት ወይንም እንደ ጭነት መቁጠር።
* ሥራቸው ከተግባራቸው የማይገጥም ሰዎች የአፋቸው ጥግና ጥግ ይሰነጠቅባቸዋል።
* ያልተፈቀደውን ነገር ለማየትና ለመስማት በሞከሩ ሰዎች ዓይኖችና ጆሮዎች ውስጥ ምስማር ይሰደድባቸዋል።
* ሕፃናቻቸውን ለማጥባት ያልፈቀዱ እናቶች ጡቶች እባቦች እንዲነድፏቸው ይደረጋል።
* ጾምን ቀድመው የሚፈቱ ቁልቁል ተሰቅለው ጭቃ እንዲልሱ ይደረጋል።
* ገበጣ የሚጫወቱ በእሳት ዓምድ ይደበደባሉ።

እነዚህ ቅጣቶች የመጨረሻውን ፍርድ አስከትሎ እስከሚመጣው እስከ ዕለተ ትንሣኤ ድረስ የሚቀጥሉ ይሆናሉ። የፍርድን ነገር በተመለከተ የሐዲት ታሪኮችም እንዲሁ አስደንጋጭ ናቸው።

«አላህም ይላል:- እነዚህን ወደ እሳቱ (ገሃነመ) የሚጣሉትን አውጡአቸው። እርሱም (አዳምም):- ለመሆኑ ስንት ናቸው ወደ እሳቱ የሚወሰዱት? በማለት ይጠይቃል። አላህም ከአንድ ሺህዎቹ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኙ ናቸው!» ልብን አያርድም ይሆን!

## የደኅንነት ምሥጢር በእስልምና



ሙስሊሞች የሰው ክፉም ሆነ ደግ ተግባር ስለሚመዘገብበት የሰማይ ቤት መዝገብ፥ እንዲሁም የሰው መልካምና መጥፎ ተግባር ስለሚመዘንበት ሚዛን ያምናሉ። ከዚህም በተጨማሪ ከገሃነመ እሳት እስከ መንግሥተ ሰማይ በተዘረጋው ሰይፍ መሳይ ድልድይ ያምናሉ። ሁሉም ሰው በዚህ ድልድይ ላይ ተረማምዶ ከሲያል ወደ

ገነት እንዲያልፍ ይጠበቅበታል። ነገር ግን ጉዞውን መዝለቅ የሚቻላቸው እነዚያ በምግባራቸው ብቃት ያላቸው ብቻ ናቸው።

አባባሉ ለክርስቲያኖች እንግዳ ነው፤ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለምና። ለመሆኑ ይህ እውነትነት አለውን? ወይስ ሙስሊሞችን አስጨንቆ ገለልተኛ ሕይወት እንዳይመሩ ለማስፈራራት የተጻፈ ነው?

---

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናውቀው ያለ «ደኅንነት» በሙስሊሞች ዘንድ የታወቀ አይደለም

---

የአላህንና የመልእክተኛውን ትእዛዝ ማመን፥ አምስቱን የእስልምና አምዶች መፈጸምና መልካም ሥራ ተደማምረው የሙስሊሞች የመዳን ተስፋ ይሆናሉ። እርግጥ ነው፤ ማንኛውም ሙስሊም በግሉ አላህ መሐሪው እንደሚሆን ተስፋ ያደርጋል። እግዚአብሔርማ መሐሪ ነው! ምሕረቱ የተገለጠው ግን ሙስሊሞች በማይቀበሉት በክርስቶስ መስቀል ላይ ነው። እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት ደኅንነትን ሊያገኝ ወደ ኢየሱስ ካልቀረበ በስተቀር፥ ማንኛውም ሙስሊም ወደ መንግሥተ ሰማይ ሊገባ አይችልም። ስለዚህ እያንዳንዱ ክርስቲያን ለሙስሊሞች ለመመስከር ከባድ ኃላፊነት አለበት! የሙስሊሞች አእምሮ በእስልምና ትምህርት የታጠበ ስለ ሆነ ቶሎ አይገነዘቡትምና።

ስለ ርዕሱ የተጻፉትን ጥያቄዎችን እንድትመረምር ጊዜው አሁን ነው።

# 7. የእስልምና ተቃውሞ በክርስትና ላይ

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ቁርዓን እንደማይክድ በጥቂቱም ቢሆን አይተናል። እንዲያውም መሐመድ እስልምና ቀደም ብሎ «መጽሐፍ የነበራቸው ሃይማኖቶች» ማለትም የአይሁድና የክርስትና ተከታይ ወይም ቅጥያ እንደሆነ ሳያምን አልቀረም።

መሐመድ አዲስ ኪዳን ስለ ኢየሱስ ከሥላሴ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ፥ በመስቀል ላይ መሞቱ፥ ሥርየት መገኘቱ የሚያስተምረውን ትምህርት መርምሮታል። ቢሆንም ትምህርቱን እንደ ስድብና ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ጋር የማይስማማ የስሕተት ትምህርት አድርጎ ቆጥሮታል። በቁርዓን ይህ ግልጽ ነው፡-

«ክርስቲያኖች አልመሲሕ የአላህ ልጅ ነው አሉ፤ ይህ በአፋቸው (የሚናገሩት) ቃላቸው ነው፤ የነዚያን ከነሱ በፊት የካዱትን ሰዎች ቃል ያመሳስላሉ፤ አላህ ያጥፋቸው፤ (ከእውነት) እንዴት ይመለሳሉ!» (ሱረቱ 9፡30)።

ጠንካራ ቃላት ናቸው። አዎ! ሙስሊሞች ስለ ክርስቲያኖች ያላቸው ስሜት እንደዚህ ነው።

ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱሳችን ሕግን፥ መዝሙርንና ወንጌልን በትክክል የመዘገበ የመጀመሪያው መጽሐፍ አይደለም ብለው ያምናሉ። ክርስቲያኖችና አይሁዶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የኢየሱስን መለኮታዊነትና የእግዚአብሔር ልጅነት፥ የሥላሴን ጽንሰ ሀሳብ፥ እንዲሁም የስቅለትንና የሥርየትን ትምህርት በመጨመርና በመበከል የመጀመሪያውን መጽሐፍ ቅዱስ ለውጠውታል በማለት አጥብቀው ይሟገታሉ። በጸረ-ክርስቲያን ሥነ-ጽሑፎቻቸውም የእምነታችንን መሠረት ይኸው እያጠቁ ናቸው። ምላሻችን እንዴት መሆን አለበት? መጽሐፍ ቅዱስ ጎዳናውን ያሳየናል፡-

> «በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን» (1ኛ ጴጥሮስ 3፡15)።

እስቲ ከዚህ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ነጥቦችን ለይተን እንማር፡-

1. የክርስቶስ ጌትነት፡- በክርስቶስ ፊት ሆነን ለጌትነቱ እየታዘዝን ማንኛውንም ነገር እንናገራለን፤ እንሠራለን።

2. ዝግጅት፡- በማናውቃቸውና ባልገቡን ነገሮች ላይ አንከራከርም። ዳሩ ግን ትክክለኛ ነገር ፈልገን (ጠይቀን) ካገኘን በኋላ በብልሃት፥ በጥበብና በሚያሳምን መንገድ እንመልሳለን።

3. መልስ አለን፡- ብዙውን ጊዜ ክርስቲያኖች ከባህላቸውና ከሃይማኖታቸው ውጭ ወንጌልን ሲያካፍሉ፥ እነርሱ ይናራቸዋል ብለው የሚያስቡአቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ። ነገር ግን እነዚህ መልሶች ዋጋ የላቸውም። ምክንያቱም ሙስሊሙ ነገሮችን የሚያይበት አመለካከት ለየት ያለ ነውና።

4. አመለካከትህን መርምር፡- ለሙስሊሞች ስንናገር እንደ መስቀል ወታደር ሳይሆን እንደ መስካሪዎች ሆነን ነው። አንዋጋቸውም፤ ወይም በማስፈራራት አናስገድዳቸውም፤ ወይም ደግሞ አንሰብካቸውም፤ የክርስቶስ ፍቅር ስለሚመራን አንገፋቸውም፤ ነገር ግን ቅዱስ ቃሉን እናካፍላቸዋለን። ማወቅ የሚገባቸውን ነጥብ በነጥብ እናብራራላቸዋለን።

5. መውጊያ አይደሉም፡- በእነዚህ ማስታወሻዎች ስለ እስልምና የተሰጠው መረጃው እነርሱን እንድናጠቃበት የተዘጋጀ አይደለም። እስልምና ምን እንደ ሆነ ብቻ የሚያስገነዝቡህን አሳቦች ለማስጨበጥ ነው እንጂ። ስለዚህም እስልምና ለተከታዮቹ ከሚያቀርበው ዋስትና ከጎደለው ትምህርት አንጻር በክርስቶስ ሞት የተገኘውን አስተማማኝ የእግዚአብሔር ጸጋ ለሙስሊሞች ለማስረዳት ያስችልሃል።

---

ልብ በል! አንድ ሙስሊም የምንናገረውን ሊረዳን የሚችለው እኛ አስቀድመን እርሱን በተረዳነው ልክ ነው።

---

አንድን ሙስሊም በመስበክ ሊገኝ የሚችለው ፍሬ እጅግ አነስተኛ መሆኑን ልምዳችን አስተምሮናል። ሙስሊሞችን ወደ ቤተ ክርስቲያን መውሰድ ደግሞ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል!! እነርሱን ለመረዳት በአረፍታ የቆይታ ጊዜ መውሰድ አለብን። በምናስተምራቸው ጊዜ ከእነርሱም መማር አለብን። በውስጣቸው የአስማተኛ መንፈስ ያለባቸው ይመስል በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ዝም ብሎ መደብደብ የለብንም። አስፈላጊው ነገር የእግዚአብሔርን ቃል መረዳታቸው ነው። በእርግጥ ጊዜ ይወስዳል፤ እጅግ ብዙ ጊዜ ይወስዳል። ሙስሊሙ አስቀድሞ ስለ ክርስትና የሚያውቅ ከሆነ ወይም ደግሞ በልቡናውና በአእምሮው ለእስልምና የሰጠው ሥፍራ በጣም ጠባብ ካልሆነ በቀር፥ ወንጌል ከመሰከርህለት በኋላ ቅጽበታዊ ውጤት አትጠብቅ። ግን ውደደው። ሙስሊምን የመውደድ ትርጉም የሚኖረው ደግሞ አንተነትህን አሳልፈህ እስከምትሰጥ ድረስ የእርሱ ነገር ግድ ሲልህ ነው።

> «እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንን ደግሞ እናካፍላችሁ ዘንድ በጎ ፈቃዳችን ነበር፤ ለእኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበርና» (1ኛ ተሰሎንቄ 2፡8)።

## ለሙስሊሞች ተቃውሞ መልስ እንዴት ይሰጣል?

መጽሐፍ ቅዱስና ቁርዓን እርስ በርስ ስለሚቃረኑ፥ ሁለቱም ከአንድ ምንጭ የተቀዱ ናቸው ማለት አይቻልም፤ እንዳቸው ወይም ምናልባት ሁለቱም ሰው እንደ ፈለገው ያደረጋቸውና የለወጣቸው ካልሆኑ በቀር።

ስለሆነም ከሙስሊሞች ጋር ተቀምጠን እውነቱን በጋራ መፈለግ የእኛ ተግባር ይሆናል። ሙስሊሞች ቁርዓን ከአላህ መውረዱንና እውነተኛ መሆኑን ሲናገሩ፥ «የለም፤ እኛ ነን እንጂ እውነተኞች፤ መጽሐፍ ቅዱሳችን እውነተኛ ነውና» እያልን መሟገት ምንም ጥቅም የለውም። ዳሩ ግን እኛ «መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ነው» ያልነው በምን ምክንያት ነው? እነርሱስ «ቁርዓን እውነት ነው» ያሰኛቸው ምንድነው? በማለት መመርመር አለብን።

### ተደጋግመው የሚነሡት የእስልምና መከራከሪያዎች

### «መጽሐፍ ቅዱስ ተለውጧል፤ ተበላሽቷልም!»

በመጀመሪያ ነገር ለሰው ልጆች የተሰጡት ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ እንደ እስልምና መረዳት ከሆነ፥ የተውጣጡት ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቁርዓን ነው። ማንም ቢሆን «መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም» እያለ፥ «ሙስሊም ነኝ» ለማለት አይበቃም። የእስልምና «ኢማን» በግልጽ ይናገረዋል፦

> «በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርአን) ወደ ኢብራሂምም፥ ወደ ኢስማዒልና ወደ ኢስሐቅም፥ ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው፥ በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት፥ በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንኾን አመንን . . .» (ሱረቱ 2፡ 136)።

> «እላንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልክተኛው፥ በዚያም በመልክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ፥ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ፤ . . . በመጽሐፎቹም . . . የካደ ሰው (ከውነት) የራቀን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ» (ሱረቱ 4፡ 136)።

> «በዚያ ወደኛ በተወረደው ወደናንተም በተወረደው አመንን፤ አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው . . .» (ሱረቱ 29፡ 46)።

እርግጥ ነው ሙስሊሞች በመጽሐፍ ቅዱስ አያምኑም። ላለማመናቸው የሚሰጡት ምክንያት የአሁኑን መጽሐፍ ቅዱስ አይሁዶችና ክርስቲያኖች በርዘው አበላሽተውታል፤ የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ የለም በማለት ነው። ይኼ እንኳን የማይመስል ነው። ምክንያቱም የመጽሐፍ ቅዱስ መዛግብት ሁሉ መሐመድ ከመወለዱና ቁርዓን ከመጻፉ በፊት ስለ ተጠናቀቁ ነው። ይህንንም ቁርዓን ያረጋግጠዋል:-

«የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! እውነቱን በውሸት ለምን ትቀላቅላላችሁ? እውነቱንም እናንተ የምታውቁ ስትኾኑ ለምን ትደብቃላችሁ?» (ሱረቱ 3:71)።

መሐመድ «የመጽሐፉ ሰዎች» የሚላቸውን አይሁዶችና ክርስቲያኖች መጽሐፉን የአበላሹት በምላሳቸው (በአንደበታቸው) እንጂ በብዕራቸው አይደለም ሲል ይከሳቸዋል።

> «ከነሱም እርሱ ከመጽሐፉ ያይደለ ሲኾን ከመጽሐፉ መኾኑን እንድታስቡ በመጽሐፉ ምላሶቻቸውን የሚያጣምሙ ክፍሎች አሉ። እርሱ ከአላህ ዘንድ ያልኾነ ሲኾን እርሱ ከአላህ ዘንድ ነውም ይላሉ። እነርሱ የሚያውቁ ሲኾኑም በአላህ ላይ ውሸትን ይናገራሉ» (ሱረቱ 3:78)።

የመጀመሪያው መጽሐፍ በእጃቸው ከሌለ እንዴት ያውቃሉ? እነርሱ እያወቁ ይዋሻሉ፤ መጽሐፉን ያጣምማሉ ይላል። ይህ ማለት መጽሐፉ በእጃቸው ስላለ ያውቁታል ማለት ነው፤ ሌላ አይደለም። እንዲህ ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስን ለምን እንዳጣመሙትና በየትኛው ክፍል ላይ እንደ ተበላሸ ለራሳቸው ሆነ ለእኛም የማስረዳቱ ፈንታ የሙስሊሞች ነው።

በማስከተልም ሌሎች ጥያቄዎችን እንጠይቃቸዋለን:-

1. የሚጨምር ወይም የሚቀንስ ዘለዓለማዊ ቅጣት ይጠብቀዋል (የዮሐንስ ራእይ 22:18-19) የሚል ቃል የተጻፈበትን መጽሐፍ ማን ለምንስ ብሎ ይለውጣል?
2. መጽሐፍ ቅዱስን ሰው ለውጦት ቢሆን ኖሮ፥ መለወጡን የሚያውቁ የጥንት አይሁዶችና ክርስቲያኖች በተቃወሙት ነበር። ማንም ሰው

ቢሆን ሙሉውን ሆነ በከፊል መጽሐፍ ቅዱስን መለወጥ አይችልም ነበር።

3. ቁርዓን በማያወላውል አቋም ተውራት፥ ዘቡርና ኢንጂል በአላህ እንደ ተሰጡ ይናገራል።

4. ቁርዓን ማንም ሰው የአላህን ቃላት መለወጥ እንደማይቻል ይናገራል (ሱረቱ 6፡34፤ 10፡64)።

5. መጽሐፍ ቅዱስ መቼ ነበር የተለወጠው? መቼም ከመሐመድ በኋላ ሊሆን አይችልም፤ የመጽሐፍ ቅዱስ መዛግብት ሁሉ በዕድሜ ይቀድሙታልና። ከእርሱም በፊት ቢሆን ኖሮ ቁርዓን ክርስቲያኖችን ወይንም አይሁዶችን ስለ ድርጊታቸው በወቀሳቸው ነበር።

6. እሺ ይሁን፥ መጽሐፍ ቅዱስን ማን ለወጠው?

7. የቀደምው መጽሐፍ የት አለ? ወይም ስለ መኖሩ ምን ማስረጃ አለ? ከተገኘ ለማነጻጸር ይጠቅመናልና።

8. ከእነዚህ ጥያቄዎቻችን አንዳንዶች ካልተመለሱ በስተቀር መጽሐፍ ቅዱስ መለወጡን እንደምን እንቀበላለን?

ሙስሊሞች ከሚመልሱት መልስ መካከል «የመጀመሪያው ወንጌል የበርናባስ ወንጌል ነው» ይሉ ይሆናል። ይህ ግን በ14ኛው ክፍለ ዘመን በማስመሰል የተሠራ ቅጂ ለመሆኑ በቀላሉ ልናጋልጠው እንችላለን። በብዙ የጽሑፍ ማስረጃም ልናረጋግጥላቸው እንችላለን።

እንደገናም ደግሞ ሙስሊሞች ቁርዓንን በዋቤነት በመጥቀስ «ወንጌል የተሰጠው ለኢየሱስ ነው፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ግን በማቴዎስ፥ በማርቆስ፥ በሉቃስና በዮሐንስ ስለ ተጻፈ የመጀመሪያው ቅጂ አይደለም» ብለው ይከራከሩህ ይሆናል። ነገር ግን ለኢየሱስ የተሰጠ ወንጌል የለም። የምሥራቹ ቃል (የወንጌሉ) ማዕከላዊ ይዘት እርሱ ራሱ ኢየሱስ ነውና።

ስለ ሃይማኖታቸው የተማሩ ሙስሊሞች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ መለወጥ ብዙ ክርክሮችን ያነሡ ይሆናል፤ አለዚያም ይህን የተመለከተ ጽሑፍ ያቀርቡ ይሆናል። (ይህን ለመመለስ ጠለቅ ወደ አለ ጽሑፍ እንመራችኋለን፤ ጻፉልን ልንረዳችሁ ዝግጁ ነን።)

«በሦስት አምላክ እያመናችሁ እንዴት ‹አንድ ነው› ትላላችሁ? አይስማማም»

ቁርዓን ሥላሴን ይቃወማል፡-

«እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ (አይሁዶችና ክርስቲያኖች) በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ፤ በአላህም ላይ እውነትን እንጂ አትናገሩ፤ የመርየም ልጅ አልመሲህ ኢሳ ከአላህ መልእክተኛ ወደ መርየም የጣላት (የኹን) ቃሉም ከርሱ የሆነ መንፈስም ብቻ ነው፤ ... ሦስት ናቸው አትበሉም፤ ተከልከሉ፤ ለናንተ የተሻለ ይሆናልና፤ አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው። ለርሱ ልጅ ያለው ከመሆን የጠራ ነው ...» (ሱረቱ 4፡171)።

«እነዚያ አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ነው ያሉ በእርግጥ ካዱ፤ አልመሲሕም አለ፡- የእስራኤል ልጆች ሆይ! ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ፤ እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ፤ መኖሪያውም እሳት ናት፤ ... እነዚያ አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው ያሉ በእርግጥ ካዱ ...» (ሱረቱ 5፡72-73)።

መሐመድ ስለ ሥላሴ ያለውን ባዕድ ግንዛቤ የተረዳን ይመስለኛል። መሐመድ «ሥላሴ» የሚላቸው አላህና ማርያምን ኢየሱስንም ነው። ኢየሱስም የተወለደው በአላህና በማርያም ሥጋዊ ግንኙነት እንደ ሆነ አስመስሎ ያቀርበዋል። መሐመድ ይህን አስተሳሰብ መቃወሙ ሊደንቀን አይገባም። እኛም ደግሞ እንቃወመዋለን።

በጣም የሚያስደንቀው ነገር ደግሞ በሱረቱ 19 አላህ ለማርያም መጸነስ ዋናው ምክንያት (መንስዔ) ሆኖ መቅረቡ ነው። ይኼ ግን ከአካላዊ (ሥጋዊ) ግንኙነት በተለየ መንገድ ቢሆንም፥ የእግዚአብሔርን አባትነት ድርሻ ግን ያረጋግጣል።

«ለአላህ ልጅን መያዝ (መውለድ) አይገባውም፤ (ከጉድለት ሁሉ) ጠራ፤ ነገርን በሻ ጊዜ ለርሱ የሚለው ኹን ነው፤ ወዲያውም ይኾናል» (ሱረቱ 19፡35)።

## እኛስ ምን ብለን ነው የምንመልስላቸው?

ስለ እግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት ስንናገር ምን ማለታችን ነው? እርግጥ ነው፤ የሥላሴ አሳብ እንደ እግዚአብሔር ትልቅነትና ዘለዓለማዊነት ሩቅና የማይደረስበት ነው። ስለ እግዚአብሔር የምናውቀው እርሱ ከአደረገውና ከሚያደርገው፥ እንዲሁም በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ራሱ ከገለጸው ነገር ነው። በተጨማሪም እግዚአብሔር ራሱን በኢየሱስ ክርስቶስ ገልጧል፡-

«እኔን ያየ አብን አይቶአል» (ዮሐንስ 14፡9)።

«እኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐንስ 10፡30)።

የኢየሱስ ልጅነትና የእግዚአብሔር ሥላሴነት በትምህርት መልክ ሳይሆን በውስጠ ታዋቂነት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተገልጧል፤ ኤርምያስ 23፡5-6፤ 33፡15-16፤ ኢሳይያስ 7፡14፤ 9፡6፤ 63፡7-10 («አዳኝ» የሚለው ቃል ዩሹዋ ወይንም ኢየሱስ ነው!)። እንዲሁም ደግሞ ዘዳግም 6፡4 «አምላካችን እግዚአብሔር አንድ (በአንድነት) እግዚአብሔር ነው» የሚል ነው። «ኤሎሂም» የተባለው እግዚአብሔር የሚለው ቃል ራሱ የብዙ ቁጥር ነው። እንዲሁም በመዝሙር (110)፡1፤ 2፡1-7 ይህን አሳብ በሚገባ ተጠናክሮ እናገኘዋለን። በአዲስ ኪዳንም ደግሞ በማቴዎስ 28፡18-19፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 13፡14 በተጻፉት ምንባቦች ላይ በጉልህ እናገኘዋለን። አዎን! እግዚአብሔር ከአእምሮአችን ይልቅ ታላቅ፥ ከአስተሳሰባችንም ልዩ ስለ ሆነ ሙሉ በሙሉ ልናውቀው አንችልም። ነገር ግን እርሱ ስለ ራሱ የተናገረውን ሁሉ ማመን አለብን።

### «እርሱ ራሱን ከአደረገው በላይ ስለ ኢየሱስ እየካብህ አታውራ! እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ አላለም።»

በቁርዓን ውስጥ ይህን እናነባለን፡-

> «አይሁድ ዑዘይር የአላህ የአላህ ልጅ ነው አለች፤ ክርስቲያኖችም አልመሲሕ የአላህ ልጅ ነው አሉ፤ በአፎቻቸው (የሚናገሩት) ቃላቸው

ነው፤ የነዚያን ከነሱ በፊት የካዱትን ሰዎች ቃል ያመሳስላሉ፤ አላህ ያጥፋቸው፤ (ከእውነት) እንዴት ይመለሳሉ!» (ሱረቱ 9፡30)።

እዚህ ላይ አንድ ነገር ማስታወስ እንወዳለን። ይኸውም መሠረታዊውን መጽሐፍ ቅዱስ ለማክሸፍ እስልምና የሚያነሣው መከራከሪያ ሁሉ ደካማ መሆኑን ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቁርዓን ውስጥ ከፍተኛ ክብር እንደ ተሰጠው እንገነዘብ።

| | |
|---|---|
| . ከድንግል ተወለደ | (ሱረቱ 19፡20) |
| . ቅዱስና ኃጢአት የሌለበት ነበር | (ሱረቱ 19፡19) |
| . እርሱ መሢሕ ነው | (ሱረቱ 4፡171) |
| . የእግዚአብሔር ቃል ነው | (ሱረቱ 4፡171) |
| . ከእግዚአብሔር የመጣ መንፈስ ነው | (ሱረቱ 4፡171) |
| . እርሱ ሕይወትን ፈጥሯል | (ሱረቱ 5፡110) |
| . የታመሙትን ፈውሶአል | (ሱረቱ 5፡110) |
| . ሙታንን አስነሥቷል | (ሱረቱ 5፡110) |
| . አመጣጡም በምልክቶች የተገለጸ ነበር | (ሱረቱ 43፡63) |
| . እርሱ ለሰው ዘር ሁሉ ምልክት ነው | (ሱረቱ 19፡21፤ 21፡91) |
| . በዚህም ሆነ በሚመጣው ዓለም የተከበረ ነው | (ሱረቱ 3፡45) |
| . እርሱ ወደ ሰማይ አርጓል (አሁን ያለውም በዚያው ነው) | (ሱረቱ 4፡158) |
| . እንደገና ለፍርድ ይመጣል | (ሱረቱ 43፡61) |

እነዚህ 13 ነጥቦች ስለ ኢየሱስ የተነገሩ ሐቆች ናቸው። እስከ አሁን በዓለም ላይ ኖረው ከአለፉት ሰዎች ሁሉ (ምናልባት ከነቢዩ ኤልያስ በስተቀር) ከእነዚህ ሦስቱን ነጥቦች እንኳን በእርግጠኝነት «ይገባኛል» የሚል ሰው ልታስብ ትችላለህን? እነዚህ ከቁርዓን ውስጥ የተወሰዱ ማረጋገጫዎች ብቻ ኢየሱስን ከነቢይ በላይ ያደርጉታል። እነዚህ ባሕርያት መለኮታዊነትን ያጎናጽፉታልን?

ቁርዓንና ሙስሊሞች የክርስቶስን መለኮታዊነት እንደሚቃወሙ አየን። መጽሐፍ ቅዱስ ግን በማያሻማ ቃሉ የክርስቶስን መለኮታዊነት እንዴት እንደሚናገር እንመልከት:-

| | |
|---|---|
| - ኢየሱስ መንገድ፥ ሕይወት፥ እውነት ነው | (ዮሐንስ 14:6) |
| - ኢየሱስ ከአብ ጋር እኩል ነው፤ የዘላለምን ሕይወት ሰጪ ነው | (ዮሐንስ 10:25-33) |
| - ኃጢአትን ያስተሰርያል | (ሉቃስ 7:48-50) |
| - የእግዚአብሔር ልጅ ነው | (ማቴዎስ 14:32-33፤ 26:63-64፤ 1ኛ ዮሐንስ 5:20) |
| - ሙታንን ያስነሣል፤ ፈራጅም ነው | (ዮሐንስ 5:21-27) |
| - የእግዚአብሔር ምሳሌ ነው፤ ፈጣሪ ነው | (2ኛ ቆሮንቶስ 4:4፤ ቆላስይስ 1:15-20፤ ዕብራውያን 1:1-4) |
| - ግዛቱ የዘላለም ግዛት ነው | (ዳንኤል 7:13-14) |
| - ጌታ አምላክም ነው | (ዮሐንስ 20:26-29) |
| - ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም አምላክ ነው | (ሮሜ 9:4-5) |
| - አዳኛችን ነው፤ ሊቤዠን | (ቲቶ 2:11-14) |

ነፍሱን ሰጥቶአል

- የእግዚአብሔር መልክ (ፊልጵስዩስ 2፡5-11)

አለው፤ ጌታም ነው

- ሳይወለድ ነበር፤ ሥልጣን አለው (ዮሐንስ 1፡10-12)

ባነበብነው ምንባብ መሠረት እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክር፡-

1. «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለው መጠሪያ ምንና ምን ያመለክታል? ከስሙ ጋር የሚጣጣሙት ሥልጣኖች ምንድናቸው?
2. የጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅነት መቼ የጀመረ ነው?
3. «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለው መጠሪያ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ያመለክታልን?
4. ኢየሱስ «የእግዚአብሔር መልክ ምሳሌ ነው» ማለት ምን ማለት ነው?

ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነና መለኮታዊነቱንም የሚናገረው አዲስ ኪዳን ብቻ አይደለም። ብሉይ ኪዳንም ስለ መሲሑ መምጣት ሲተነብይ ይህንንም አብሮ ያስገነዝባል፡-

> «እነሆ ድንግል ትጸንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል (እግዚአብሔር ከእኛ ጋር) ብላ ትጠራዋለች» (ኢሳይያስ 7፡14)።

> «ሕፃን ተወልዶልናል፤ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል፤ ... ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል» (ኢሳይያስ 9፡6)።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ሁለት ባሕርያት ነበሩ፤ የእናቱ ሰብዓዊነትና የአባቱ መለኮታዊነት። ገጽታው ሙሉ በሙሉ የሰው ነበር። እንደ ሰው መብላት፥ መጠጣት፥ መተኛትም ነበረበት። እንደ ሰው ሕመም ተሰምቶታል፤ አዝኖአል፤ ደስታውንም ገልጿል፤ ጸልዮአልም። ነገር ግን በሁለት ዓሣና በአምስት እንጀራ 5000 ሰዎች መግቦ የአጠገበው ሰብዕናው አይደለም፤ የአምላክነት ባሕርዩ እንጂ። ለምጻሞችን ለማንጻት፥ አንካሶቹን ለመፈወስ፥ ሽባዎችን ለመተርተር፥ ዕውሮችን ለማብራት፥ ሙታንን ለማስነሣት፥ ማዕበሉን ጸጥ

ለማድረግ፥ ኃጢአትን ይቅር ለማለት፥ በውኃ ላይ ለመራመድና ከሙታን ለመነሣት የቻለው፥ አዎ! በመለኮታዊነቱ ነበር።

## «ኢየሱስ እንዳልተሰቀለ መጽሐፋችን ነግሮናል።»

እስልምና ከሁሉ በላይ አጥብቆ ከሚቃወመው ነገር የክርስቶስን ስቅለትና ሞት ነው፡-

> «እኛ የአላህን መልክተኛ የመርየምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን ገደልን በማለታቸው (ረገምናቸው)፤ አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትምም፤ ግን ለነሱ (የተገደለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ . . . በእርግጥም አልገደሉትም» (ሱረቱ 4፡157)።



በብዙ የእስልምና መጻሕፍት፥ በራሪ ወረቀቶች፥ ኦዲዮቪዠዋል አገልግሎቶች ሁሉ ይህን አባባል በጣም በማጠናከር ይናገራሉ። እንዲያውም በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈ ለማስመሰል ይሞክራሉ። አንዳንዶቹ ሙስሊሞች ደግሞ «በመስቀል ላይ ተቸንክሯል፤ ግን ሩጉን ሳተ እንጂ አልሞተም» ይላሉ። ራሱን በሳተ ጊዜ ተወስዶ በመቃብሩ ውስጥ በነበሩ ሴቶች እርዳታ ተደርጎለት አገገሟል ይላሉ። ይሁዳ ኢየሱስን መስሏቸው የሰቀሉት እርሱን ነው ብለው የሚያምኑ አሉ። «ተሰቀለ» የሚለው ቃል ከሁለት የላቲን ቃላት የተገኘ ቃል ነው። የአንደኛው ትርጉም መስቀል ማለት ሲሆን፥ ሁለተኛው ማንጠልጠል ወይም መቸንከር ማለት ነው። እናም ሙስሊሞች «ተሰቀለ» ማለት «ተንጠለጠለ» ማለት ነው እንጂ፥ «ሞተ» ማለት አይደለም በማለት ይከራከራሉ። ፋይዳ የሌለው ክርክር ነው።

## «የኢየሱስ መስቀል መሰናከያው ነው!»

> «መቼም አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ፤ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ፤ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው፤ ለተጠሩት ግን፥

አይሁድ ቢሆኑ የግሪክ ሰዎችም ቢሆኑ፥ የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው» (1ኛ ቆሮንቶስ 1፡22-24)።

ከዚህ በተጨማሪ በገላትያ 5፡11 «የመስቀሉ እንቅፋት» የሚል ሐረግ እናነባለን። እንቅፋቱ ምንድነው?

ሰው በመልካምነቱና በኃይሉ እግዚአብሔር ወደሚገኝበት ወደ መንግሥተ ሰማይ ሊገባ እንደማይችል በመስቀል ላይ የተፈጸመው የክርስቶስ መሥዋዕትነት ያሳየናል። ኢየሱስ «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» (ዮሐንስ 15፡5) ያለው ይህን አስቀድሞ ስለሚያውቅ ነው። ጳውሎስም «በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና» ሲል ተናግሮአል (ሮሜ 7፡19)።

ስለዚህም ኢየሱስ ስለ ሰው ኃጢአት ሊሠዋ ያስፈልገው ነበር። በእኛ ፈንታ እርሱ ሞቶ የመንግሥተ ሰማይን በር ይከፍትልን ዘንድ ያስፈልግ ነበር። ሰውማ በእግዚአብሔር ላይ ታብዮ ዓምፆአልና፥ እግዚአብሔር የእርሱን የጽድቅ ሥራ መቀበል ከቶ አይሆንለትም። የተነማው እንቅፋት ይህ ነው።

«እያንዳንዱ ሰው ኃጢአቱን ሊሸከም ስለሚገባው ስለ እኔ ኃጢአት ብሎ ሌላው ቢሠቃይበት ትክክል አይደለም።»

«ደም ሳይፈስ ስርየት የለም» ይላል የዕብራውያን ጸሐፊ (ዕብራውያን 9፡22)። ይህም በትክክል የመሥዋዕቱን ደም ሲያመለክት ነው። ብሉይ ኪዳንም ከዳር እስከ ዳር ስለ መሥዋዕት ያስተምራል! «ደሙ ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሰርይልናል» (ዘሌዋውያን 17፡11)። ማስተስረይ ሲባልም እርቅ ማውረድ ወይንም የፈረሰን ኅብረት ማደስ ማለት ነው።

ሰይጣን ደኅንነትን ሁሉ ዋጋ ቢስ ለማድረግ ከፈለገ የኢየሱስን የመስቀል ላይ ሞት መካድ ወይንም የማያስፈልግ አድርጎ ማቅረብ አለበት። ቁርዓንም ከዚህ ሌላ አልተናገረም።

ከሁሉ የሚበልጠው ዋና ነጥብ ስለሆነ፥ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀልና መሞት ለሙስሊም ወዳጆቻችን ለመናገር ስንነሣ በእርጋታና በትዕግሥት ማስረዳት አለብን፡-

* አንድ ሦስተኛ (ሢሶ) የሚሆነው የወንጌላት ክፍል የሚተርከው ስለ ኢየሱስ ሞትና ከመሞቱም ከአንድ ሳምንት በፊት ስለ ነበረው የኢየሱስ የሕይወት ታሪክ ነው።

* የኢየሱስ መሥዋዕትነት ትክክለኛው የብሉይ ኪዳን ትምህርት ማጠቃለያ ነው (ሉቃስ 24፡26፥ 44 ተመልከት)።

* የኢየሱስ የመስቀል ላይ ሞት በብሉይ ኪዳን ነቢያት በብዙ ሁናቴ ተተንብዮአል።

* እኛ የዓይን ምስክሮች አሉን። እነርሱ እንዲህ ያለውን ታሪክ ፈጥረው ቢያወሩ ኖሮ ምን ይጠቅማቸው ነበር?


* ክርስቶስ ራሱም ስለ ሞቱ ብዙውን ጊዜ ተንብዮአል።

* ስለ ኢየሱስ የመስቀል ላይ ሞት የተጣራ ተቀባይነት ያለው የታሪክ ማስረጃ አለ።

## የሐቁ ማረጋገጫ

የዓይን ምስክሮች የክርስቶስን የመስቀል ላይ ሞትና ትንሣኤ ያረጋግጣሉ።

ጳውሎስም በርካታዎችን ይጠቅሳቸዋል፡-




«እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ፡- መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፤ ተቀበረም፤ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፤ ለኬፋም ታየ፤ በኋላም ለአሥራ ሁለቱ፤ ከዚያም በኋላ ከ500 ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ ከእነርሱም የሚበዙት እስከ አሁን አሉ» (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡3-6)። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ የሚል ይመስላል፡- «እኔን ካላመናችሁኝ ከዚህ ከቆሮንቶስ ከተማ ወደ ኢዮጴ በጀልባ ተሻገሩ፤ ከዚያም በእግራችሁ ወደ ኢየሩሳሌም አቅኑና ሰዎቹን አፈላልጋችሁ ራሳችሁ አናግሩአቸው!» ጴጥሮስም የዓይን

ምስክሮችን መረጃ ያቀርባል። እስቲ አንድ ጊዜ አስባስቡት፤ በጴንጤ ቆስጤ ቀን ጴጥሮስ ይህንን ነገር እያነሣ ቆሞ በሰበከ ጊዜ እውነት ባይሆን ኖሮ ያ ሁሉ ሕዝብ ያምን ነበርን?

«ራሳችሁ እንደምታውቁ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበር፤ እርሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነው አሳቡና በቀደመው እውቀቱ ተሰጥቶ በዓመፀኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት» (የሐዋርያት ሥራ 2፡22-23)።

ጴጥሮስ ይህን የተናገረው ከጌታ ስቅለት ከሰባት ሳምንታት በኋላ ነው። ውሸት ቢሆን ኖሮ አድማጮቹ ሁሉ «ውድ ስምዖን ጴጥሮስ ሆይ! ተሰቅሎ የሞተው ማን ነው እባክህ? ወይስ ቅዠት ትቃዣለህ?» ባሉት ነበር።



የኢየሩሳሌም ሰዎች ሁሉ የወንጌልን ስርጭት ባዳፈኑት ነበር! ይህንን እያስታወስህ እንደገና የሐዋርያት ሥራ ታሪኮች ተመልከት።

## የታሪክ ባለ ሙያዎች አረጋግጠውታል

በጣም የታወቀውና በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበረው ታሪክ ጸሐፊ ታክቱስ እንዲህ ብሎ ዘግቧል፡-

«ክርስቲያን» የሚለውን ስያሜ የአገኙት፥ በጢባርዮስ ዘመነ መንግሥት አገረ ገዥ በነበረው በጴንጤናዊው ጲላጦስ ከተገደለው ከክርስቶስ ነው።» ታክቱስ ግን የክርስትና እምነትን አጥብቆ የሚቃወም ቢሆንም፥ በሮማዊው አገረ ገዥ ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞቱን አልካደም።

በዚያው ዘመን የነበረው አይሁዳዊ ታሪክ ጸሐፊ ፍላቪዩስ ጆሲፈስ ሲጽፍ፡-

«በዚያን ዘመን አካባቢ ኢየሱስ የሚባል ጠቢብ ሰው ነበር። እርሱን ሰው ብሎ መጥራቱ እንኳን ተገቢ ቢሆን - ምክንያቱም እርሱ የድንቅ ሥራዎች አድራጊ ነበር፤ እውነቱን በደስታ የተቀበሉለት ሰዎች መምህር ነበር። እርሱም ብዙ አይሁዶችንና አሕዛብን ወደ ራሱ ስቧቸዋል። መሢሕም ነበር። ከመካከላችን በነበሩ መሪዎች አሳብና ምክር ጲላጦስ ለመስቀል ሞት አሳልፎ ሲሰጠው በመጀመሪያ የወደዱት ወዳጆቹ አልተዉትም ነበር፤ እርሱም ቅዱሳን ነቢያት እንደ ተነበዩለት ሕያው ሆኖ በሦስተኛው ቀን ከሞት በመነሣት ታይቶአቸዋልና» (የፍላቪዩስ ጆሲፈስ ሥራዎች ቅጽ 2 ገጽ 412)። (ለበለጠ መረጃ - «ለሙስሊሞች ጥያቄዎች የክርስቲያኖች መልሶች» ተመልከት።)

ልብ እንበል፡-

| | |
|---|---|
| አይሁዶች የኢየሱስን ስቅለት ይቀበላሉ፤ በቦታው ነበሩና፤ ነገር ግን መሢሕ መሆኑን ይክዳሉ፤ | ሙስሊሞች መሢሕ መሆኑን እያመኑ ዳሩ ግን የመስቀል ላይ ሞቱን ይክዳሉ፤ በቦታው አልነበሩም። አባባላቸው የመጣው ከድርጊቱ 600 ዓመታት ዘግይቶ ነው። |

በብሉይ ኪዳን ስለ ኢየሱስ የተነገሩት ትንቢቶች መፈጸም ለመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት ትልቅ ማስረጃ ነው።

አለፍ አለፍ እያልን በአጫጭሩ ነቢያት ስለ መሢሑ ኢየሱስ የተነበዩትን ትንቢቶች ተመልክተናል። አሁን እነዚህን በዝርዝር እናገናዝብ፡-

| | የብሉይ ኪዳን ትንቢት | በአዲስ ኪዳን ፍጻሜ |
|---|---|---|
| 1. ኢየሩሳሌምን ለመገንባት ሕግ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ከ483 ዓመታት በኋላ እንደሚወለድ ተተነበየ | (445 ዓ.ዓ.) ዳንኤል 9፡ 24-26 | |
| 2. በቤተልሔ ም መወለድ ነበረበት | ሚክያስ 5፡2 | ሉቃስ 2፡4-7 |
| 3. ከድንግል መወለድ ነበረበት | ኢሳይያስ 7፡14 | ማቴዎስ 1፡18-25 |
| 4. ራሱ እግዚአብሔር ይሆናል | ኢሳይያስ 7፡14፤ 9፡6 | ማቴዎስ 1፡18-23 |
| 5. ስሙ አዳኝ ይባላል | ኢሳይያስ 49፡1-8፤ 63፡8 | ማቴዎስ 1፡21 |
| 6. ለማዳንና ለመፈወስ ይመጣል | ኢሳይያስ 35፡4-5 | ማቴዎስ 1፡21፤ ሉቃስ 19፡10 |
| 7. በአህያ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ይገባል | ዘካርያስ 9፡9 | ማቴዎስ21፡1-9 |
| 8. ወዳጁ አሳልፎ እንደሚሰጠው | መዝሙር (41)፡9 | ማርቆስ 14፡10-11 14፡43-44፤ ማቴዎስ 27፡3-8 |
| 9. በ30 ብር እንደሚሸጥ | ዘካርያስ 11፡12-13 | ማቴዎስ 26፡15 |
| 10. ለራሱ ሳይሆን ለሌሎች እንደሚሞት | ኢሳይያስ 50፡6፤ 53፡1-12 | ዮሐንስ 18 ና 19 |
| 11. እጆቹና እግሮቹ እንደሚቸነከሩ | መዝሙር (22)፡1፥ 7-17 | ዮሐንስ18 ና 19 |
| 12. ልብሶቹን እንደሚከፋፈሉትና በእጀ ጠባቡ ላይ ዕጣ እንደሚጣጣሉ | መዝሙር (22)፡18 | ዮሐንስ 18 ና 19 |
| 13. እንደማይበሰብስ (በመቃብር ውስጥ) | መዝሙር (16)፡10 | ሉቃስ 24፡1-11 |
| 14. ወደ ሰማይ ዓርጎ በአባቱ ቀኝ እንደሚቀመጥ | መዝሙር (110)፡1 | ማቴዎስ 26፡64፤ ዕብራውያን 1፡13 |
| 15. ተመልሶ እንደሚመጣ፥ የወጉትም እንደሚያዩት | ዘካርያስ 12፡10 | ገና ያልተፈጸመ |

እነዚህ ትንቢቶች የተነበዩት ከ1000 ዓመተ ዓለም እስከ 500 ዓመተ ዓለም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ነው። በዚያን ጊዜ ፈጽሞ ሊታሰብ የማይቻለውን ነገር ግን እያንዳንዱን ድርጊት ነጥብ እንኳን ሳይቀር በሚያስደንቅ ዝርዝር አብራርተውታል።

ስለ ኢየሱስ ሕይወት፥ ስለ ሞቱና ትንሣኤው ከዚህ የበለጠ ማስረጃ የሚፈልግ ሰው ይኖር ይሆን? በእርግጥ ነቢያቱን የእግዚአብሔር መንፈስ ይህንን እንዲተነብዩ መርቶአቸው ነበር። የትንቢቶቹም መፈጸም በመጽሐፍ ቅዱስ እውነትነት የበለጠ እንተማመናለን።

እስቲ ለማጠቃለል እንሞክር፡-

ከእነዚህ ከማያጠራጥሩ ምልክቶች የተነሣ በመጽሐፍ ቅዱስ ፈጽሞ እንደገፋለን።

በሌላ በኩል ግን ቁርዓን ከመለኮታዊ ምንጭ ስለ መገኘቱ በትንቢት ቢሆን ወይንም በሌላ ጥልቅ ይዘቱ ሊያረጋግጥልን አይችልም።

ሙስሊሞች ከሚያቀርቧቸው ምክንያቶች ጥቂቶቹ፡- የቁርዓን የዐረብኛው ቅጂ ውብ ሆኖ መጻፍ፥ እንደ መሐመድ ላለ ላልተማረ ሰው የማይቻል የሚመስለውን አደራረሱንና እንዲሁም ይዘቱ ፍጹም ነው በማለት ነው። የሰው መከራከሪያ ነጥቦች እንጂ እውነትነት የላቸውም።

እኛስ የምናምነውን ብቻ አይደለም የምናውቀው፤ ለምን እንደምናምንም እናውቃለን!

በስተ መጨረሻ ያሉትን ጥያቄዎች መሥራትን እንዳትዘነጋ። እርዳታ ከፈለግህ ወይንም ጥያቄ ካለህ በአድራሻችን ጻፍልን።

# 8. ለሙስሊሞች መመስከር

## የዛሬው ሁኔታ

ቤተ ክርስቲያን ለሙስሊሞች የወንጌል አገልግሎት ለመስጠት ትኩረት የሰጠችበት ጊዜ የለም። ትናንሽ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች ለመመስከር ጥረት አድርገዋል፤ ግን ይኼ አልፎ አልፎ የሚደረግ እንጂ የተቀናጀ አሠራር አልነበረም።

ለሙስሊሞች ለመመስከር ችላ የተባለበት ምክንያት አንድም በአላዋቂነት ወይንም በፍርሃት ነው።

እንደ እኔ ከሆነ ፍርሃቱ የመጣው ከአለማወቅ የተነሣ ነው። ሁሉም ሰው እባብን ይፈራል። ነገር ግን የእባብን ባሕርይና እንቅስቃሴ፥ ከነደፈም በኋላ ምን መደረግ እንዳለበት ባውቅ ፍርሃቴን አስወግዳለሁ። እውቀትና ልምድ ፍርሃትን በጣም ይቀንሰዋል።

አባባሉ ወንጌልን ለሙስሊሞች ለማዳረስ ከአለን ሀሳብ ጋር ይሄዳል። ስለ እስልምና ወይንም ስለ ሙስሊሞች ምንም እውቀት የሌለው ክርስቲያን ከሙስሊሞች ፀረ-ክርስትና እንቅስቃሴዎች ጋር ፊት ለፊት ቢጋጠም ምን ማድረግ እንዳለበት አያውቅም። አላዋቂ ክርስቲያን ለሙስሊም ለመመስከር አይደፍርም። ስለሆነም አለማወቁ ወደ ፍርሃት ያመጣዋል። ፍርሃትም ለወንጌል ሥራ እንቅፋት ነው።

ስለዚህም «ለሙስሊሞች እንዴት መመስከር አለብን?» ወደሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ከመጣን የእስልምናን ምንነትና ሙስሊሞችም ስለ ያዙት እምነት፥ እንዲሁም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያላቸውን አስተሳሰብ በሚገባ መመርመር አለብን። ለሙስሊም ወንጌልን በጥበብና በግልጽ ለማቅረብ ስለ እነዚህ ነገሮች ልናውቅ ያስፈልገናል። በእርግጥ እግዚአብሔር ከዚህ በተለየ መንገድ ሁኔታዎችን በቁጥጥሩ ሥር

ሊያደርገልን ይችላል። ስለዚህም እናመሰግነዋለን። ሆኖም የተዘጋጀን ሆነን መቅረብ ይጠበቅብናል።

## የተለመደ ሁኔታ የሚባል ነገር አለን?


**አለም! የለም!**

«የለም» የምንልበት ምክንያት፥ የዐረብ አገሩ ሙስሊም ከቱርኩ፥ ከማሌዢያው ወይንም ከታንዛኒያው የሚለይበት የእምነት ባሕርያት አሉት። በአንድ አገር ውስጥ እንኳን ሆነው ወግ አጥባቂ ሙስሊሞችና ባህላዊ ሙስሊሞች የሚለያዩ አሉ። ባህላዊ ሙስሊሞች ምናልባት ገና ከጥንት አባቶቻቸው ከወረሷቸው የመናፍስት አሠራርና የጥንቆላ ልምምዶች አልተላቀቁም ይሆናል። ሌሎችም ደግሞ በስም ብቻ «ሙስሊም» የሆኑ አሉ። ድሆችና ሀብታሞች፥ የተማሩና ያልተማሩ፥ የከተማና የገጠር ነዋሪዎች፥ ተግባቢና ዝምተኞች አሉ። እኛም እንዲሁ የተለያየን ነን።

በዚህ ሁሉ ግን «የተለመደ ሁኔታ የሚባል አለ» ለማለት እንችላለን። ዘመኑ የቴክኒዮሎጂ ነውና የሥነ-ጽሑፍ እውቀት ወይንም የመደበኛ ሥልጠና የማይገኝበት የለም። የሕንድ፥ የቱርክና የታንዛኒያ ሙስሊሞች በአንድ ዓይነት መንገድ ሊከራከሩና አንድ ዓይነት መሠረት ያለው እምነትና አመለካከት ሊያንጸባርቁ ይችላሉ። ጠንካራ የክርስትና እንቅስቃሴ በአለበት አካባቢ የሚኖሩ ሙስሊሞች የክርስትናን እምነት ለመቋቋም በብዙው ይሠለጥናሉ።

## የወንጌል ስርጭት ስንል ምን ማለታችን ነው?

የወንጌል ሥራ ማለት ከዚህ በታች ያሉ ነጥቦችን ተረድቶ ማስተላለፍ ማለት ነው። ነጥቦቹም፦



እነዚህን ነጥቦች ለተረዳልን ሰው ስለ መንፈሳዊ መረዳት ያልነገርነው ከሆነ፥ አሁን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንዲቀበል ለሰውየው ግብዣ መቅረብ አለበት፤ ይኸውም ስለ ንስሐውም ሙሉ የኃጢአት ይቅርታ እንዲቀበል ማለት ነው። ስለ ኃጢአቱ እግዚአብሔር በክርስቶስ ውስጥ ሆኖ በመስቀል ላይ ተሠቃይቶ ዕዳውን ከፍሎለታልና። በእግዚአብሔር ዘንድ፥ ለኃጢአታችን ይቅርታ አድርጎ የሰጠውን ስጦታ ተቀብለን ወደ ፊት ከኃጢአት ርቀን ለመኖር፥ እንዲሁም ከእርሱ ጋር በአንድነት ለመኖር በወሰንን ጊዜ፥ የኃጢአት ችግራችን መፍትሔ ተገኝቷል። በእግዚአብሔር ጸጋ አዲስ ሕይወትን በእምነት መቀበል፥ የኃጢአትን አስቀያሚነትና በኃጢአት ላይ የሚመጣውን ፍርድ እንድናይ ዓይኖቻችንን የገለጠልን መንፈስ ቅዱስ አሁን አሟኑን ወደ እውነት ሁሉ ይመራዋል ማለት ነው። ይህም የሚሆነው ለውጡ ከልብ የሆነ እንደሆነ ነው። ይህም ቢሆን፥ ኃጢአት የሌለበትን ሕይወት ለመኖር እንደማንችል አውቀን መቀበል አለብን። ስለሆነም ከጸጋ ሥር እንኖራለን (ሮሜ 5-8)።

ምናልባት ብዙውን ጊዜ የወንጌል አገልግሎት ሰዎች ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው እንዲቀበሉ የሚደረግ ጥሪ ብቻ እንደ ሆነ ልናስብ እንችላለን። ይህ በመሠረቱ ወንጌልን ሽባ ማድረግ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ወንጌል ከዚህም የሚበልጥ ነው።

## 1. የወንጌሉ እውነታዎች

እግዚአብሔር ዓለምን ይወዳል፤ ወይስ የዓለምን ሕዝብ ይወዳል ብንል ይሻል ይሆን? ኃጢአታቸውን ግን ይጠላል፤ ጉስቁልናቸውን ደግሞ በኃዘንና በርኅራኄ ይመለከታል። የሰዎች መባዘን፥ ዓላማ ቢስነትና ሕሊና-አልባነት ኑሮአቸውን በዋል-ፈሰስ ያደርገዋል። በውጫዊ ነገሮች ላይ እንዲመኩም ብዙ ምኞትን፥ በሌላው ላይ መሠልጠንና ቁሳቁስ ማከማቸት ላይ ያተኩራሉ። ነገር ግን በባዘኑበት በዚያው እንዳይጠፉ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከራሱ ጋር የሚያስታርቅበትን መንገድ አዘጋጅቷል።


ነቢዩ ኢሳይያስም እንደ ተነበየው «መድኃኒትም ሆነላቸው»፤ ሲተረጎምም «ኢየሱስ ሆነላቸው»። «በጭንቀታቸው ሁሉ እርሱ

ተጨነቀ፤ ... በፍቅሩና በርኅራኄውም ተቤዣቸው፤ .. አንሥቶ ተሸከማቸው» (ኢሳይያስ 63፡8-9)። «እነርሱ ግን ዓመፁ፤ ቅዱስ መንፈሱንም አስመረሩ» (ቁ. 10)። ይኼን ሁሉ እያደረጉት ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው ክፍል ውስጥ ኢየሱስ «እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ፥ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ» ሲል ይናገራል (ዮሐንስ ራእይ 3፡20)።

እግዚአብሔር ኢየሱሳችን (አዳኛችን) ሆነ። መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር በእርሱነቱ (በመንፈስነቱ) ሊያደርግ ያልተቻለውን ነገር ሰው በመሆን ሥጋ ለብሶ አደረገልን። እርሱ «ስለ በጎቹ ነፍሱን አኖረ (ሰጠ)» (ዮሐንስ 10፡15)። እኛን ወደ እርሱ ለማምጣት ሲል ለበደላችን፥ ለኃጢአታችንና ለአሳፋሪው ድርጊታችን ሁሉ ደሙን አፈሰሰ፤ ሕይወቱንም ከፈለ (ማቴዎስ 20፡28፤ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡6፤ ዕብራውያን 9፡15)። በኃጢአት ሞተው የነበሩ ሁሉ አዲስ ሕይወት፥ ይኸውም ዘለዓለማዊ ሕይወት ይሆንላቸው ዘንድ እርሱ ወደ ዓለም መጣ (ኤፌሶን 2፡1-2፥ 6-10፤ ሮሜ 6፡4፤ ይሁዳ 24-25፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 3፡9)። እግዚአብሔር እኛን ሊያድን የወደደበት መንገድ ሌላ ሳይሆን ለምን ይህንን እንደ መረጠ ማን ያውቃል? ማንም አያውቅም። ቁም ነገሩ ግን በእርሱ ሙሉ ለሙሉ ለመታመን ከመቻላችን ላይ ነው።

## 2. የወንጌሉ ማስረጃ

በእግዚአብሔር ታምነን በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘታችንን አሁንም እርሱ በወደደው መንገድ ያረጋግጥልናል። «የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል» (ሮሜ 8፡10)። በእርግጥ ይኼ በጣም ግላዊ የሆነ እውቀት ነው። ከዚህስ የበለጠ በመረጃ የተደገፈና አሳማኝ የሆነ ነገር ይኖር ይሆን? አዎን አለ! ቀደም ሲል ነካክተነዋል። የብሉይ ኪዳን ነቢያት በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው የጻፏቸው ዝርዝርና በጠቅላላውም የተፈጸሙ ትንቢቶች አሉ። የአይሁዶች መበተንና ከ1900 ዓመታት በኋላ የእስራኤልን መንግሥት ዳግም መመሥረት ጨምሮ ጠቅላላው




የእስራኤል ታሪክ ተተንብዮአል። ይህም በዓለም ታሪክ ውስጥ ልዩ ስፍራ የተሰጠው ነው። (ብዙ ማስረጃዎች አሉን። ጠይቅ!)

የበለጠ ደግሞ የሚያስገርሙት ስለ ክርስቶስ የተነገሩት ትንቢቶች ናቸው። በማቴዎስ ወንጌል ብቻ «ነቢያት እንደ ተናገሩ፥ ... የተባለው ይፈጸም ዘንድ፥ ...» ወዘተ በሚል ሐረግና አባባል የተደገፉ 24 ዓረፍተ ነገሮች እንዳሉ ታውቅ ይሆን?

የወንጌሉን እውነተኝነት ለማወቅ ለሚፈልግ ሁሉ እነዚህን ውስጣዊ መረጃዎች ለማሳየት በመቻላችን ደስ ይለናል። እባክህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶችንና አፈጻጸማቸውን ለማሳየት የተዘጋጀ ማስታወሻ በመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ ለመያዝ ሞክር!

ብዙ የተማረው መስካሪ ደግሞ መረጃዎችን ከከርሰ-ምድር ጥናት (አርኪዮሎጂ)፥ ከታሪክና ከዓይን ምስክሮች ሊጨምር ይችላል። መቼም እነዚህን ሁሉ ማስረጃዎች አይቶ መጽሐፍ ቅዱስ በሰው የተቀነባበረ ነው ለማለት አይደፍርም።

## 3. የወንጌሉ ተስፋዎች

«እኛ ሙስሊሞች ለመሆኑ ምን የተስፋ ቃል አለን?» ብሎ ሼኪውን እንደ አፋጠጣቸው አንድ ሙስሊም ወዳጃችን አጫውቶናል። በመቀጠልም «ከቁርዓን ይልቅ በእናንተ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ የተስፋ ቃሎች እንዳሉ አውቃለሁ» ብሏል።

> «ቃልህ ለጉሮሮዬ ጣፋጭ ነው፤ ከማርና ከወተት ይልቅ ለአፌ ጣፈጠኝ» [መዝሙር (119)፡103]

ከሚለው ከመዝሙር ጸሐፊ ጋር እንደሰት። አውቀናቸው ልክ እንደ ግል ሀብታችን ይዘናቸው ይሆን? ጥቂቶቹን ዛሬ እንመልከት።

እግዚአብሔርን ስለ እነዚህ ነገሮች ተስፋ እናደርገዋለን፡-

- ስለ ምሕረቱ ... መዝሙር (103)፡7
- ስለ ይቅርታው ... መዝሙር (103)፡12፤ ኢሳይያስ 59፡3፤ 43፡25፤ 44፡22፤ ኤርምያስ 31፡34፤
- ስለ ዘላለም ሕይወት ... ዮሐንስ 10፡22-28፤ ማቴዎስ 25፡34፥ 46ለ፤
- ስለ አዲስ ሕይወት ... 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17
- ስለሚሰጠን እረፍት ... ማቴዎስ 11፡28፤ የዮሐንስ ራእይ 14፡13
- ለዘላለም ስለማይለየን ... ማቴዎስ 28፡20
- ዓለም ሊሰጠን ስለማይቻለው ዮሐንስ 14፡27፤ 15፡9-11፤

ሰላም፥ ፍቅርና ደስታ ... ገላትያ 5፡22

- ከሁሉም በላይ መንግሥተ ሰማይን ... ዮሐንስ 14፡3፤ የዮሐንስ ራእይ 5፡10

- መልካም ስጦታዎችን (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡8-10፤ ኤፌሶን 4፡11፤ ሮሜ 12፡6-8፤ በተለይ ደግሞ የሐዋርያት ሥራ 2፡38።

## 4. የወንጌሉ ቅድመ-ሁኔታዎች

> «በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም» (ማቴዎስ 7፡21)።

አንድ ሰው የኃጢአት ይቅርታ ጠይቆ ወደ ጌታ ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት ቁጭ ብሎ ማመዛዘን አለበት (ሉቃስ 14፡28)። ንስሐ የኃጢአት ይቅርታን ማግኘት የሚቀድም ነው። ንስሐ ማለትም ኃጢአትን ለመተው ፈቃደኛ መሆንን ይጠይቃል (ሉቃስ 13፡3)፤ ነገር ግን እንዲሁም ከኃጢአት ለመላቀቅ እንደማይቻል ሁላችንም እናውቀዋለን። ለዚህም እግዚአብሔር መፍትሔ አዘጋጅቷል፤ «ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ። ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ፥ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፤ እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» (1ኛ ዮሐንስ 2፡1)። ለመታዘዝ ፈቅደኛ መሆናችን ሁሉን በሚያውቀው በእግዚአብሔር መታመናችንን ያሳያል (ዕብራውያን 5፡9)። የእግዚአብሔር ቃል «እስከ መጨረሻ የሚጸና እርሱ ይድናል» (ዕብራውያን 3፡6፤ የዮሐንስ ራእይ 2፡4፤ ማቴዎስ 24፡13) ስለሚል፥ መጽናትና መታመን ለደኅንነት እንደ ቅድመ-ሁኔታዎች ይታያሉ። እምነትና ታማኝነት ከቶም አይለያዩም። ክርስቶስን ለመከተል መወሰንና ደኅንነት በሚገኝበት በሕይወት ለውጥ ውስጥ ማለፍ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። አንድ አማኝ ለእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር የተለየ ዓላማ የተመረጠ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን መለየት ወይም መቀደስ ብሎ ይጠራዋል። «ያለ ቅድስና ማንም

እግዚአብሔርን ሊያይ አይችልም» (ዕብራውያን 12፡14፤ 1ኛ ጴጥሮስ 1፡13-19)።

ለሚመሰክርለት ሰው እነዚህን ነገሮች አለመግለጽ የወንጌሉን ግማሽ ብቻ መናገር ማለት ነው። ይህንን እንዳናደርግ እንጠንቀቅ! ዳሩ ግን ይህን ደግሞ ልብ እንበል፤ የእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚው እግዚአብሔር ነው (ፊልጵስዩስ 1፡6)። የክርስትናን ጉዞ መለኮታዊ የሚያደርገው ይህ ነው። የእግዚአብሔር እርዳታና ቀስቃሽነት ባይኖር ኖሮ እስከ መጨረሻው ሊጸና ቀርቶ ማንም ወደ ጌታ ባልመጣ ነበር።

ቅድመ-ወንጌል

በተለያየ መንገድ የምናገኛቸው ሙስሊሞች ስለ ክርስትና እምነት ያላቸው ግንዛቤ የተሳሳተ ነው። ስለ ሆነም የምንነግራቸውን ሁሉ እንዳይቀበሉት ግንዛቤአቸው ጋርዶአቸዋል። ስለዚህም የቅድመ-ወንጌል እርምጃዎች ለወንጌል ጥርጊያ መንገድ ይከፍታል። ክርስቶስ እንዳይታወቅ የተቀመጠ ጋሬጣ ሁሉ መነሣት አለበት። ጊዜ ይውሰድ እንጂ እንቅፋቱ ሳይነሣ ለማንም ቢሆን ክርስቶስን እንዲቀበል ጥያቄ መቅረብ የለበትም።

እዚህ ላይ መነሣት ያለበት አንድ ጥያቄ አለ። ይኸውም ኢየሱስ የአይሁድ ነቢይ እንደሆነና ያመጣውም መልእክት እንደ ተበላሸ፥ በኋላ ግን ባልተበላሸው (ባልተነካው) የመሐመድ መልእክት እንደ ተተካ እያመነ አንድ ሙስሊም ወደ ክርስቶስ ሊመጣ የሚፈልግ ለምንድነው? ወንጌልን በምንመሰክርበት ጊዜ እኛ ክርስቲያኖች ሞርሞንስ፥ ወይም የይሖዋ ምስክሮች ሃይማኖታቸውን ሊያካፍሉን ወደ እኛ ሲቀርቡ የሚሰማን ስሜት ዓይነት ነው ሙስሊሙም የሚሰማው። ለዚህ ነው ቅድመ-ወንጌል አቀራረብ ውሸተኛ አመለካከቶችንና አሳቦችን መመንጠር ያለበት።

«የወዳጅነት የወንጌል ስርጭት»

> በአጠቃላይ አነጋገር፥ ለሙስሊሞች የሚደረገው የወንጌል ስርጭት በግለሰብ ደረጃ የሚካሄድ ነው።

ሙስሊሞች በቡድን በሚሆኑበት ጊዜ የሚያስቀርቡ ዓይነቶች አይደሉም። በተቻለ መጠን ዘና ባለና አንድ ለአንድ ወይም ሁለት ለሁለት በሚደረግ ጭውውት ውስጥ መስካሪው ውይይቱን ቀስ በቀስ ወደ መንፈሳዊ ጉዳዮች ማምራት አለበት። ሙስሊሞች በአጠቃላይ ሃይማኖተኞች ናቸው። ስለ እምነታቸው አዘውትረው ይናገራሉ። እኛን በሃይማኖታቸው ለመማረክ ስለሚፈልጉ፥ እኛም እንዲሁ እንደምናደርግ ይገምታሉ። ስለ ሆነም ምንም እንኳን ቁርዓን በዚህ ጉዳይ ላይ ማስጠንቀቂያ ቢኖረውም ከሙስሊሞች ጋር ወዳጅነት ለመመሥረት ችል አንበል።

> «እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከነዚያ ከበፊታችሁ መጽሐፍን ከተሰጡት እነዚያ ሃይማኖታችሁን ማላገጫና መጫወቻ አድርገው የያዙትን ከሓዲዎችንም ረዳቶች አድርጋችሁ አትያዙ » (ሱረቱ 5፡57)።

> «አይሁዶችና ክርስቲያኖችም ሃይማኖታቸውን እስከምከተል ድረስ ካንተ ፈጽሞ አይወዱም፤ . . .» (ሱረቱ 2፡120)

> «ለሰዎች ከተገለጸች ሕዝብ ሁሉ በላጭ ሆናችሁ፤ በጽድቅ ነገር ታዛላችሁ፤ ከመጥፎም ነገር ትከለክላላችሁ፤ በአላህም (አንድነት) ታምናላችሁ» (ሱረቱ 3፡110)።

> «እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከእናንተ ሌላ ምስጢረኛን አትያዙ፤ ማበላሸትን አይገቱላችሁም፤ ጉዳታችሁን ይወዳሉ» (ሱረቱ 4፡118)።

የእኛ ወዳጅነት ግን ወደ ወንጌል ለመሳብ የተደረገ እንዳልሆነ እናስመስል? ቃሉ ግልጽ ምላሽ ይሰጠናል፡-

> «ነገር ግን የሚያሳፍረውን ስውር ነገር ጥለናልና በተንኰል አንመላለስም፤ የእግዚአብሔርንም ቃል በውሸት አንቀላቅልም፤ እውነትን በመግለጥ ግን በእግዚአብሔር ፊት ለሰው ሕሊና ሁሉ ራሳችንን እናመሰግናለን» (2ኛ ቆሮንቶስ 4፡2)።

ሙስሊሞች አቋማቸውን ለማሳወቅ ዙሪያ-ዙሪያውን የሚሉ ሰዎች አይደሉም። አቋማቸውን በግልጽ ይናገራሉ። እኛም እንደዚሁ ብናደርግ መልካም ነው! ነገር ግን በርኅራኄ፥ በፍቅር፥ በየዋህነት ስለ እምነት በአክብሮት መነጋገርና ዝም ብሎ በአፋችን ላይ የመጣውን ቃል ያለ

ጥበብ መለጠፍ እጅግ ይለያያሉ። እንዲህ ያለ አግባብ ቃል የሚለጥፉ «ራሳቸውን እንደ ሰማዕት» የሾሙ ተመጻዳቂዎች በሚያደርጉት ግፊት ለምቹና ለትክክለኛ ምስክርነት የሚከፈተውን በር ይዘጋሉ። ስለዚህ መልካሙንና ተገቢውን እናድርግ።

ለመስማማት ወይስ ለመጋፈጥ?

የምንነጋገረው በወዳጅነት ወንጌል እንዴት እንደሚሰራጭ ነው። «ወዳጅነት» የሚለውን ቃል «ግላዊ ግንኙነት» በሚለው ቃል መተካትን ወደድሁ። ምክንያቱም እግዚአብሔርን የማይወድ በክርስቶስም ያልተቤዠ ሰው ወዳጅ ሊሆነኝ አይችልምና፤ ወይንም ደግሞ አባባሉን እንዲያው «ከላይ ከላይ» ልጠቀምበት ካላልሁኝ በስተቀር መጽሐፍ ቅዱስ ከዓለም ጋር ስለሚሆነው ጓደኝነት ወይም ስለማይመች መጣመር ብዙ የሚናገረው አለው (2ኛ ቆሮንቶስ 6፡4)። ከዓለም ሰዎች (ከማያምኑት) ጋር ጠለቅ-ጠበቅ ያለ ግንኙነት እንዲኖረን መጽሐፋችን አይመክረንም።

ነገር ግን ወንጌሉን በሚገባ ለማሰራጨት በተወሰነ ደረጃ ግላዊ ግንኙነት ማድረጉ በጣም ይረዳል። በግል ግንኙነት ጊዜ እርስ በርስ መተማመንና መከባበር ስለሚኖር ቀጥሎ ለሚሆነው ነገር ጥሩ መሠረት ይጥላል።

ቢሆንም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የምናስተላልፈው መልእክት ውጤት ላይኖረው ወይንም ተቀባይነት ሊያጣ ይችላል። ማንም ሰው ቢሆን ደግሞ ተቀባይነትን ሲያጣ ደስ አይለውም፤ ይሰማዋልም። ወንጌልንም የሚያካፍልበትን በር ይዘጋል። ስለዚህም አድራጎታችን ሁሉ ሚዛን የጠበቀ መሆን አለበት። ሚዛን ስንጠብቅ ወንጌሉን በጥንቃቄና በፍቅር ብቻ በማካፈል፥ የማይወዱትን ነገር ላለመናገር መጠንቀቅ አለብን።

«መስማማት» ማለት ደግሞ ሙስሊሞች በሚሉት ነገር ለመግባባት መዘጋጀት ማለት ነው። ይህም ደግሞ ግንኙነትን ላልተወሰነ ጊዜ ያህል ለማራዘም ይጠቅማል። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ መስማት የማይፈልጉትን ባለመናገርና ስለ እስልምናም መስማት የሚፈልጉትን በመናገር፥ እንዲሁም ከእስልምናም ሆነ ወይም ከሌላ ሃይማኖት ጥቂት ጥቂት

በመውሰድና ከክርስትና መልእክት ጋር በማቀናጀት የበለጠ ለማሳመን በምንሞክርበት ጊዜ መመሳሰልን እየተለማመድን ነው ማለት ነው። መመሳሰልን ካልሞከርን ደግሞ ምናልባት ወደ ግፍ፥ አልፎም ተቃውሞን ያስከትልብን ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጉዳዩ የሚለው አለው፡-

«ወዳጆች ሆይ፥ በእናንተ መካከል እንደ እሳት ሊፈትናችሁ ስለሚሆነው መከራ ድንቅ ነገር እንደ መጣባችሁ አትደነቁ፤ ነገር ግን በክርስቶስ መከራ በምትካፈሉበት ልክ ደስ ይበላችሁ። ስለ ክርስቶስ ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ» (1ኛ ጴጥሮስ 4፡12-14)።

«ባሪያ ከጌታው አይበልጥም ብዬ የነገርኋችሁን ቃል አስቡ። እኔን አሳደውኝ እንደሆኑ እናንተን ደግሞ ያሳድዱአችኋል። . . . ዳሩ ግን የላከኝን አያውቁምና ይህን ሁሉ ስለ ስሜ ያደርጉባችኋል» (ዮሐንስ 15፡20-21)።

«ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ» (ማቴዎስ 5፡11)።

ርዕሱን እንደገና ለማብላላት እንዲመችህ ጥያቄዎችን ለመሥራት ሞክር።

# 9. እንደ እግዚአብሔር ኃይል መጠን መልእክቱን ማስተላለፍ

## እውነትና ኃይል በወንጌል አገልግሎት ውስጥ

በአንዲት በታወቀች የአፍሪካ ከተማ ውስጥ ትልቅ የአደባባይ ስብከት (ክሩሴድ) ከተደረገ በኋላ በመቶ የሚቆጠሩ ሙስሊሞች እንደ ዳኑና እንደ ተፈወሱ የሚያመለክት ዘገባ ወጣ። ከአንድ ዓመት በኋላ የተደረገው ጥናት ግን ውጤቱ አሳዛኝ ነበር። አንድም ሙስሊም ወደ ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ኅብረት በአባልነት አልተጨመረም ነበር፤ እንደዚሁም ማንም ሙስሊም እንደ ተፈወሰ የሚያውቅ እንኳን አልተገኘም። «ለሚያምኑ ሁሉ ለማዳን የሆነው የእግዚአብሔር ኃይል» እየተዘነጋ «በኃይል የተሞላ ወንጌል» ወይንም «የኃይል ስብከት»

ባብዛኛው «ሥነ ልቦናዊ ኃይል» ወይንም የማግባቢያ ዘዴ መስሎ ይታያል። (ሮሜ 1፡16)

## የእግዚአብሔር ወይስ የሰው ኃይል?

እውነተኛ የእግዚአብሔር ኃይል ሁልጊዜም ቢሆን በሰባኪው ትሕትና የተላበሰ ነው። ሰባኪው የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ ብሎ በድምፅ አወጣጡ ወይንም መድረክ ላይ በሚፈጥረው ትዕይንት (ድራማ) የሚገለጠው ኃይል የእግዚአብሔር ኃይል ሳይሆን «የሥጋ» ኃይል ነው። የሚያሳዝነው ግን ሰዎች በቀላሉ ስለሚያምኑና ስለሚታለሉ የዚህ ዓይነቱን ትዕይንት ስለ ተለማመዱትም በተናጋሪው ውስጥ የሚያልፈው ኃይል የእግዚአብሔር ይሁን የሰው ኃይል ለመለየት አይችሉም።

## ኃይል በድካም ውስጥ

ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች «በድካምና በፍርሃት፥ በብዙ መንቀጥቀጥ» እንደ መጣ እናነባለን (1ኛ ቆሮንቶስ 2፡3)። በተጨማሪም «ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና» (2ኛ ቆሮንቶስ 12፡9) እንደ ተባለለት ይናገራል። ነገር ግን «በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን፥ ቃሌም፥ ስብከቴም (የተነገረበት መንገድ) መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበረ እንጂ በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም» (1ኛ ቆሮንቶስ 2፡4-5)። ደግሞም «ወንጌላችን በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ፥ በብዙ መረዳትም እንጂ በቃል ብቻ ወደ እናንተ አልመጣምና» (1ኛ ተሰሎንቄ 1፡5) ተብሎ ተጽፏል። «የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ነው እንጂ በቃል አይደለምና» (1ኛ ቆሮንቶስ 4፡20)። እነዚህን ሁሉ ስናይ ኃይሉ ከድምፅ ማጉሊያው እንዳልሆነ እንረዳለን። ጳውሎስም ቢሆን እስከዚህ ድረስ «ድንቅ ተናጋሪ» የማይባል መሆኑን እናውቃለን። ታዲያ ይህ ኃይል ምንድነው? ቅዱሳት መጻሕፍትን ስንመረምር አንድ ነገር ይጠቁሙናል። ይኸውም የሰሚዎቹ ትኩረት በሰው ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ነው። መንፈስ ቅዱስ ሰዎቹ በእግዚአብሔርና በተናገረው ቃል እንዲያምኑ በሰው ይጠቀማል፤ «ብዙ መረዳት»ም ይኸው ነው። የሚተላለፍ መልእክት ከእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ሌላ

ሰው መንፈስ እንጂ ከሰው ወደ ሰው አእምሮ ወይም ልብ የሚተላለፍ አይደለም።

ትኩረትን ከራሳችን አንሥተን በእግዚአብሔር ላይ እንዴት ልናደርግ እንችላለን? የእግዚአብሔርን ኃይል ምንነት ከአወቅን ይቻላል።

> «በወንጌል አላፍርምና ... ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና» (ሮሜ 1፡16)።
>
> «የመስቀሉ ቃል ... የእግዚአብሔር ኃይል ነውና» (1ኛ ቆሮንቶስ 1፡18)።
>
> «እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ... የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው» (1ኛ ቆሮንቶስ 1፡23-24)።

**የመስቀሉ ቃል = የተሰቀለው ክርስቶስ = ወንጌሉ**

ይህ ሰው በ«መልካም ሥራዎች» ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ራሱን ለማዳን እንደማይችልና እግዚአብሔር አስቀድሞ ባደረገለት ነገር ላይ ሙሉ ለሙሉ እንደሚደገፍ እግዚአብሔር ያወጀበት ነው።

ይህ ከሁሉም በፊት ግልጽ ሊሆን ይገባል (ለዚህም ነው ማብራሪያ የምናቀርበው)። ከዚያም ሰውየው ኢየሱስ ክርስቶስን በእምነት ለመቀበል ወይም ለመተው ስለ መፈለጉ መወሰን አለበት።

**ይህ የመስቀሉ ቃል የሆነው ወንጌል ብቻ ለደኅንነት፥ ፈርሃ-እግዚአብሔር ላለበት ሕይወትና ለአገልግሎት ብቃት የእግዚአብሔርን ኃይል ያጎናጽፋል።**

ይህም «የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚገለጽበት» እንደሆነ እናምናለን።

«በሰው ልማድ ምንም እንኳን የምንመላለስ ብንሆን፥ እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም፤ የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፤ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤ የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔር እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ

እናፈርሳለን፤ ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮንም ሁሉ እንማርካለን»
(2ኛ ቆሮንቶስ 10፡3-5)።

## የሰይጣን ኃይል

ጠንቋዮች፥ አስማተኞች፥ የሶፊዝምና የህንዱኢዝም መናፍስት ጠሪዎች፥ ሼኪዎች፥ የቁርዓን ወይንም ሌሎች መንፈሳዊ ጽሑፎችን እንደ አስማት በመጠቀም በሌላ ሰው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩና መረገምን የሚያመጡ ሁሉ መንፈሳዊ ኃይልን ይጠቀማሉ። የሚደገፉት ግን «በጨለማው ገዥ ኃይል» ነው (ኤፌሶን 6፡12)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዲያብሎስ ቁጥጥር ሥር ስለ ነበሩት ሰዎች እናነባለን (የሐዋርያት 10፡38)። ሰይጣን በጣም ኃይለኛ በሆነው አንበሳ ተመስሏል (1ኛ ጴጥሮስ 5፡8)።

## ተገዳዳሪ ኃይል


መሐመድ ይህን ኃይል ተጠቅሞበታል። በደቡብ ዐረቢያ ከሚገኘው ከናጅራን የመጡ ክርስቲያኖች በጎበኙትና እስልምናን ለመቀበል እምቢ ባሉ ጊዜ መሐመድ በአደባባይ ስብሰባ ተፈታትኖአቸዋል። ሱረቱ 3፡61 እንዲህ ይላል፤ «... በዒሳ የተከራከሩህን ሰዎች፡- ኑ ልጆቻችንና ልጆቻችሁን፥ ሴቶቻችንና ሴቶቻችሁንም፥ ነፍሶቻችንንና ነፍሶቻችሁንም፥ እንጥራ፤ ከዚያም አጥብቀን አላህን እንለምን፤ የአላህንም ቁጣ በውሸታሞቹ ላይ እናድርግ በላቸው።»

መሐመድ ክርስቲያኖችን በአላህ ስም ለመርገም፥ ክርስቲያኖቹም በምላሹ በኢየሱስ ስም ሊረግሙትና ማንኛው ጠንካራ መሆኑን ለማወቅ ነበር የመሐመድ ዓላማ። ዛሬ ይህንን በሥነ-መለኮት ቋንቋ «የኃይል ተግዳሮት» እንለዋለን። እነዚያ ክርስቲያኖች «ታዲያ በስሙ የተጠራነው ለመባረክ እንጂ ለመርገም አይደለምና፤ አንረግምም» በማለት ተቃወሙ። እኔም ራሴ (የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ) በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ አልፌአለሁ። ከብዙ ዓመታት በፊት አንድ ሙስሊም ከረገመኝ በኋላ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ እንደምሞት ተነግሮኝ ነበር።

ብዙ አረመኔዎች ከመናፍስት ሁሉ ኃይለኛው የቱ እንደሆነ አውቀው ከሁሉም ወደሚበልጥ አስማተኛ ወይንም ጠንቋይ ራሳቸውን

ማስጠጋት፥ በሰሙም መጠለል ይፈልጋሉ። ብዙ ሙስሊሞችና የስም ክርስቲያኖችም እንዲህ ዓይነቱን ተግባር እያደረጉ በልባቸው አረመኔነታቸውን ይመሰክራሉ። ጌታ ኢየሱስ ዲያብሎስን አሸንፎታልና በእርግጥ የዳንን ሁሉ በእርሱ ኃይልና ጥበቃ ሥር እንገኛለን። በጠላት ኃይል ላይ ሙሉ ሥልጣን ስለ ተሰጠን ሊጎዳን የሚችል ምንም ነገር የለም (ሉቃስ 10፡ 19)። ከሆነስ፥ ለምን ወደ አረመኔ ፍርሃትና አጉል እምነት እንመለሳለን?

## ተገቢ የሆነ ግንኙነት



የወንጌል ስርጭት ሥራ በሁለት ነገሮች ላይ የተመረከዘ ነው። በሥዕሉ ላይ የሚታየውን ድልድይ ልብ በሉ! ከወንዙ ዳርና ዳር ድልድዩን የተሸከሙትን አምዶች የቆሙበትን መሠረት እኔ ከወንጌል ሥራ መሠረቶች ጋር አመሳስላቸዋለሁ።

የአድማጩን መሠረትና አቅጣጫ እያሰበ እውነቱን ግልጽና የሚረዳው ዓይነት ለማድረግ ሁሉም ነገር በመስካሪው ጥረት ላይ የአረፈ ቢሆንም፥ በተመጣጣኝ ደረጃ ደግሞ አድማጩን እንዲያሳምነውና እንዲለውጠው መንፈስ ቅዱስን በማድመጡ ወይም ባለማድመጡ ላይ ይመረኮዛል። ስለዚህም ምስክርነት ከሚከተሉት ሁለት ነጥቦች ጋር በጥብቅ ተያይዟል፡-

1. ግልጽ የሆነ፥ የሰሚውን ሁኔታ የሚገነዘብ፥ በቀላሉ የሚገባ መልእክት፥ እና
2. የአድማጩ መረዳት ከመንፈስ ቅዱስ ወደሚገኘው እምነትና ውሳኔ እንዲደርስ የምናቀርበው የጠበቀ ጸሎት።

አንድ ሰው የሰጠው አሳብ ምናልባት ትክክል ይሆናል! ወንጌሉን ለመመስከር፥ የክርስቶስ ተከታይ ለማድረግና ለማስተማር ነገሮችን ግልጽ የማድረጉ ሥራ ሁሉ የእኛ ድርሻ ብቻ እንደሆነ አድርገን

መሥራት አለብን። እንደገናም ጥረታችን ሁሉ ከንቱ እንደሆነና የሥራው ባለቤት እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ አድርገን እንጸልይ። እኛ መቶ በመቶ እንደ ጣርን ከተሰማን፥ እንግዲያውስ ቀሪው የእግዚአብሔር ድርሻ እንደሆነ አምነን በጸሎት አሳልፈን እንስጥ። ጌታ ኢየሱስም «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» ብሎናል (ዮሐንስ 15፡5)።

## መንፈሳዊ ውጊያ

> «ለእነርሱም ... የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ» (2ኛ ቆሮንቶስ 4፡4)።

> መንፈሳዊ ውጊያ የሚደረገው እግዚአብሔርና ሰይጣን ጠላቶች ስለ ሆኑ ነው (የዮሐንስ ራእይ 12፡7)። የምንዋጋውም ሰዎችን የሚያሳውረውንና የሚያስረውን የጠላትን ኃይል ለመስባበር ነው።

ዓይነ ስውር ሰው ሊያይ አይችልም! ለእርሱም ሰማይ ምን እንደሚመስል ወይም የርዝ አበባን ውበት ለማስረዳት ቢሞከር ከንቱ ድካም ብቻ ነው ትርፉ። ምንም ያህል ጊዜ ብናስረዳውም፥ ዕውር ሰው የሰማያዊና የርዝ ቀለም ውበት ሊገባው፥ በዓይነ - ሕሊናውም ሊሣል፥ ሊያደንቅም ከቶ አይችልም። ደኅንነትን እንዳላገኙት እንደ ሌሎቹ ሁሉ ሙስሊምም እንዲሁ በኃጢአቱ ምክንያት መንፈሳዊ ነገር አይታየውም፤ ለመዳን የአዳኙ ኢየሱስ አስፈላጊነት አይገባውም። እንዲያይ እንዴት አድርገን ልንረዳው እንችላለን? እርሱን ከአሰሩትና ከአሳወሩት መንፈሳዊ ኃይሎች ጋር በመዋጋት ነው። ይህም ደግሞ በጸሎት ብቻ አይሆንም። ዲያብሎስንና አጋንንቱን ለምነን አናስለቅቃቸውም። ለቀው እንዲሄዱ በጌታ በኢየሱስ ስም እናዛቸዋለን እንጂ! በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና ሥልጣን እናዛቸዋለን - ለቀው እንዲሄዱ! የተሰጠን ሥልጣን ይህ ነው። የተጠቀምነው ቃል አይደለም በዲያብሎስና በአጋንንቱ ላይ አስማታዊ ኃይል የሚያሳድረው! እንደዚህ ማሰብ የለብንም። ነገር ግን እኛ የምናዘው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰጠን ሥልጣን ነው። (ሁልጊዜም ደግሞ «በጌታ በኢየሱስ

ክርስቶስ ስም» በሉ፤ ምክንያቱም አንዳንድ አጋንንት እንኳን «ኢየሱስ» ስለሚባሉ!)

> «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ፤ እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ . . . ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» (ማቴዎስ 28፡18-19)።
>
> «በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፤ የሚጎዳችሁ ምንም የለም» (ሉቃስ 10፡19)።

ከመንግሥት አንድ ጊዜ ሹመት የተቀበለ የፖሊስ መኮንን ወንጀለኛን ሁሉ ለማሰር ሥልጣን አለው። ሁልጊዜም ቢሆን መንግሥት ከመኮንኑ ጎን ይቆማል። ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የመንግሥት ኃይሎች ሁሉ ይደግፉታል። መንግሥትን ወክሎ ነው የሚሠራ።

እኛም ደግሞ የእግዚአብሔር የጽድቁ መጣሪያዎች እንድንሆን ሥልጣን ተሰጥቶናል። በሥልጣናችንም መንፈሳዊ ወንጀለኞችን ለማሰር ኃይል ተሰጥቶኛል።

> «መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፤ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር፥ ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዥዎች ጋር፥ በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ» (ኤፌሶን 6፡12)።

ሰይጣንም እንዲሁ ውስን ኃይል አለው፤ ነገር ግን መውጊያው የጦር ዕቃው ተነጥቋል፡-

> ክርስቶስ «እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል፤ አለቅነትንና ሥልጣኑን ገፎ፥ ድል በመንሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው» (ቆላስይስ 2፡14-15)።

እርሱም መላእክትና ሥልጣናት፥ ኃይላትም ከተገዙለት በኋላ ወደ ሰማይ ሄዶ በእግዚአብሔር ቀኝ አለ» (1ኛ ጴጥሮስ 3፡22)።

እንዲህም ሆኖ ሰይጣንና አጋንንቱ መጠነኛ ኃይልና ሥልጣን አላቸው፤ ሆኖም ለእኛ ከተሰጠን ኃይልና ሥልጣን በልጦ አያውቅም። «አለቅነትንም ሁሉና ሥልጣንን ሁሉ በሻረ ጊዜ ፍጻሜ ይሆናል» (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡24)።


እነዚህ የጽድቅ ጠላቶች (ወንጀለኞች) ማለትም አጋንንት ሁልጊዜም ባይሆን ሥልጣናችንን የሚቃወሙበት አጋጣሚ አለ። በሐዋርያት ሥራ 19፡ 13-16 የተገለጸውን ታሪክ መመርመሩ መልካም ነው።

በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን በርኩሳን መናፍስት ላይ የስሙ ሥልጣን ተሰጥቶታል ብለናል። በእምነት ይህን ሥልጣን እንጠቀማለን። ቅጽበታዊ ውጤት በማናይበት ጊዜ ተስፋ ቆርጠን አንተውም! ሰይጣን ሁልጊዜ ግራ ሊያጋባንና ሊያታልለን ይጥራል። ነገር ግን በእምነት የጠየቅነውን በእምነት እንደ ተቀበልን እንቁጠር።

አሁንም ሚዛን የምንጠብቅበት ሌላ ጉዳይ አለ። በተሰጠን ሥልጣን ስንጸልይ የማያምነውን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እናስገባዋለን ማለት አይደለም። ሰው ማንን እንደሚያገለግል እንዲመርጥ ነጻ ምርጫ ተሰጥቶታልና (ዘዳግም 30፡19፤ ኢያሱ 24፡15፤)። የእኛ ድርሻ መመስከር ነው። ለመናፍስት የሚገዛ ከሆነ፥ ከተያዘበት እሥራት እንዲፈታ የአሰሩት ክፉ መናፍስት እንዲለቁት ሳናቋርጥ በክርስቶስ ስም ማዘዝም ነው። ያ ማለት ግን ግለሰቡ ወዲያው ክርስቶስን እንደ አዳኙና እንደ ጌታው አድርጎ ይቀበለዋል ማለት አይደለም። የመጀመሪያው ሰማዕት እስጢፋኖስ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ነበር። ነገር ግን ስለ ክርስቶስ በተናገራቸው ጊዜ አድማጮቹ እጅግ ተቆጥተው «ጥርሳቸውን አፋጩበት። በታላቅ ድምፅም እየጮኹ ጆሮአቸውን ደፈኑ» (የሐዋርያት ሥራ 7፡54-57)። መልእክቱን ጠልተው «አንቀበልም» አሉ። ስላልተቀበሉት እስጢፋኖስ ሊነቀፍ ይገባዋልን?

በእስልምና ያለው ዕውርነትና እስራት ምናልባት ከማንኛውም ሃይማኖት ይልቅ የከፋ ይሆናል። የእስራቱ ጽናት አንድም ከሙስሊሙ የሕይወት ዘይቤ፥ በሌላ በኩልም ደግሞ በእስልምና መንፈስ፥ «በዚህ ቤት ጌታ» (መካ ባለው ካባ) መንፈስ እንደ ተተበተበ ጥርጥር የለውም። ስለዚህም ከወንጌል ምስክርነት ጎን የአገልግሎታችን መነሻና መድረሻ እግዚአብሔር የዕውሩን ዓይኖች እንዲከፍት መጸለይ ይሆናል ማለት ነው።

እንዲህ ያለ አገልግሎት በመሠረቱ ሰፊ የጸሎት አንዳንዴም የጾም፥ (ማቴዎስ 17፡21)፥ እና ክፉ መናፍስት እንዲለቁ የግሣጼ ጊዜ ይጠይቃል። ይህም ረዘም ያለ ጊዜ ለመውሰድ ይችላል።



«ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤ . . . በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት» (1ኛ ጴጥሮስ 5፡8-9)።

አንበሳ በይበልጥ የሚያጠቃው ከእርሱ ለማምለጥ የሚሸሸውን ሰው ነው። «ጸንታችሁ ተቃወሙት!» አንበሳ በድፍረት ከፊቱ ቆሞ የሚቃወመውን ሰው ይፈራል። እኛም ደግሞ የመሰከርንላቸውን ሰዎች የአሳወረውንና የተበተበውን ክፉ መንፈሳዊውን ኃይል ሁሉ ፊት ለፊት ልንቃወመው ይገባል። ሰይጣን የጣለውን ግዳይ ማስጣል አለብን፤ በድፍረት ልናጠቃው ይገባል።

ጌታ ኢየሱስ ማንም «አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ እቃውን ሊነጥቀው እንዴት ይችላል?» (ማቴዎስ 12፡29) ሲል ጠይቋል።

«ኃይለኛው» ሰይጣን ከነአጋንንቱ ነው። «ዕቃዎቹ» ደግሞ የማያምኑት ሰዎች ናቸው። ሊፈቱና ሊያዩ የሚችሉት «ኃይለኛው» አስቀድሞ ቢታሰር ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያንኑን አድርጎአል፤ ነገር ግን ለጴጥሮስ ደግሞ «በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል» (ማቴዎስ 16፡19) ብሎታል። በኋላም ይህንኑ ቃል ለደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ነግሮአቸዋል (ማቴዎስ 18፡18)።

ይህ እንግዲህ የወንጌል ሥራ አካል የሆነው «ታላቁ ተልእኮ» ነው። እንደ ምን አድርገን ስናከናውነው ቆይተን ይሆን?

የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ የመጣው ሰዎችን ስለ ኃጢአታቸው ለመውቀስ፥ የቃሉን እውነት ለማሳየትና መልእክቱን ወደ መረዳት ለመምራት ነው። የእርሱ ተቃዋሚዎች የሆኑት ለዲያብሎስ የሚገዙት አጋንንት ናቸው። እነርሱም የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ለማደናቀፍ ይታገላሉ። ስለ ሆነም ለወንጌሉ እውነት እንቅፋት እንዳይፈጥሩ ሁልጊዜም ልንቃወማቸው በስሙ ኃይልም ልናስራቸው ይገባል።

እስቲ እናጠቃልለው:-

* ሰይጣን በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ተሸንፏል።
* ሰይጣን አሁንም ቢሆን በማያምኑት ሰዎች ላይ ውስን ሥልጣን አለው። ለእርሱ የሚገዙት አጋንንት ያሳውሩአቸዋል፤ ባሪያዎች አድርገው ያስሩአቸዋል።
* ምርኮኞችን ለማስፈታት «ማራኪው - ኃይለኛው» መታሰር አለበት፤ ኢየሱስ ቀድሞ አስሮታል፤ እኛም በጸሎትና በግሣጼ ክፉውን ለማሰርና ለማስወጣት ተጠርተናል።
* ክርስቶስ በአጋንንትና በክፉ መናፍስት ላይ መንፈሳዊ ሥልጣን ሰጥቶናል (ማርቆስ 3:15)።
* ግለሰቡ በክርስቶስ በኩል የተሰጠውን የእግዚአብሔር ይቅርታ አልቀበልም ሊል ይችላል።
* መንፈሳዊ ውጊያ ለጥሩና ታማኝ የወንጌል አገልግሎት ማካካሻ አይሆንም፤ ጥሩና ታማኝ ወንጌልም ለመንፈሳዊ ውጊያ መተኪያ አይሆንም።
* የእግዚአብሔር ወኪሎች ነን እንጂ የራሳችን የሆነ ኃይል ወይም ሥልጣን እንደሌለን ልንገነዘብ ይገባል። ይህም እውነት ትሑት ልብ እንዲኖረን ያደርገናል። ስንጸልይም የእኛን ባዶነትና የእግዚአብሔርን ምሉዕነት በማድመቅ መሆን አለበት።
* ክርስትናን የሚቃረን የእስልምና መዋቅር ፈራርሶ ሙስሊሞች ከእስራቱ እንዲፈቱ ጸሎታችን ነው።

በተጨማሪ መግለጫው ላይ በምዕራፍ 9 ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎች ለመሥራት ጊዜ ብትወስድ እጅግ ታተርፋለህ። መንፈስ ቅዱስ በልብህ እየሠራ ሳለ፥ አሁኑኑ ለመሥራት ቸል አትበል።